# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# የ2002/2003

## የልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች ኦዲት

## ዓመታዊ ሪፖርት

ጥረዝ 1

ግንቦት 2003

አዲስ አበባ

## ማውጫ

1. መግቢያ ........................................................................1
2. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት (Summery Report).........4
3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ዝርዝር ኦዲት ሪፖርት ................................36
3.1 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች....................................................36
3.1.1 ልዩ ልዩ መ/ቤቶች ......................................................................36
3.1.2 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ....................................60
3.1.3 የሴቶች ጉዳይ ሚ/ር የ2002 ዓመት ሂሣብ ኦዲት ............................97
3.2 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች.......................................................... 102
3.3 የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች....................................... 117
3.4 የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች ..................................................... 141
3.5 ልዩ ኦዲት.............................................................................. 167
3.5.1 የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ፕሮጀክት ............................................................................. 167
3.5.2 በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም ለድሬዳዋ እና ገጠር ከተሞች የኤሌክትሪክ ማስፋፊያ ትራንስፎርመሮችና አሉሙኒየም ግዥ ......... 172
3.5.3 የቀድሞ አዲስ አባ የማገዶ እንጨት ተሸካሚ ሴቶች ማኅበር........................................................................... 179

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
# የ2002/2003 ኦዲት ዓመት የልዩ ልዩ መ/ቤቶች
# የፋይናንሻል ኦዲት ዓመታዊ ሪፖርት

## I. መግቢያ

የዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 669/2002 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራሉን መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በወጡት ሕጎች፣ በአስፈጻሚው አካል በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁንና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ለማረጋገጥና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፣
- በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች የፋይናንስ፤ የክዋኔ የአካባቢ ጥበቃ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩ ለክልልና ለፌዴራል መንግሥት ሠራተኞችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሂሳብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ /ስታንዳርድ/ ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት ለክልል መንግስታት የሚሰጠውን የበጀት ድጋፍና ልዩ ድጎማዎች ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣

- የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ወይም ያስደርጋል፣
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፤
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን ኦዲት ያደርጋል ወይም ያስደርጋል፤
- ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት መ/ቤት እና ድርጅት የውስጥ ኦዲተር ከመመደቡ በፊት ተመዳቢው አስፈላጊው የሙያ ብቃት ያለው መሆኑን አረጋግጦ ምስክርነት ይሰጣል፣
- ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል አስፈላጊውንም ቁጥጥር ያደርጋል፣
- ከክልል መንግሥታት የኦዲት መ/ቤቶች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፣
- ለግል ኦዲተሮችና የሂሳብ አያያዝ ሥራ ለሚያከናውኑ የሂሳብ አዋቂዎች በሥራው መስክ ለማሰማራት የሚያስችላቸውን የምስክር ወረቀት ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፣

በሪፖርቱ ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፤ ኦዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍን በተመለከተ በተለያዩ ክልሎች ሥር ባሉ የወረዳና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶችን የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም በተከታታይ ኦዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው::

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የኦዲት ሥራ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በኦዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የኦዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ ኦዲት ተደራጊ የፌዴራል መ/ቤትና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን መልስና አስተያየት ያገናዘበ ነው::

የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ተከታታይ ኦዲት ደግሞ ኦዲቱ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የኦዲት ተደራጊ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶችና የሴክተር ጽ/ቤቶች ኃላፊዎች ጋር የመውጫ ውይይት የተደረገበትና የኦዲት ሪፖርቱም በየሩብ ዓመቱ ተጠቃሎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር እየተላከ ውይይት የተደረገበትና አጠቃላይ ሂሳቡም ላይ የኦዲት አስተያየት ተሰጥቶበታል፡፡

ኦዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና ኦዲት ስልት በመከተል እንዲሁም አንዳንዴም እንደ ኦዲቱ አስፈላጊነት እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

ለኦዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ ሂሳብ ኦዲት ደረጃዎች እና ኦዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው::

ከመንግሥት በሚመደብላቸው በጀት በሚተዳደሩ የፌዴራል መ/ቤቶች በተደረገው የፋይናንስ ኦዲት የተገኙ ውጤቶች በBPR ጥናት መሰረት በኦዲት የእንጌጅሜነት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ4 ዘርፍ በተደረጁ መ/ቤቶች፡- የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፤ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤ የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች እና የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች እንድሁም በክልል መንግስታት የተከናወነው የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲት በተሻሻለው የኢትዮጵያ መንግሥትና ዓለም ባንክ የኦዲት ሥራ ስምምነት መሠረት በህጋዊነት (Fiduciary Responsibility) ላይ ኦዲቱ በማትኮር የፕሮጀክቱ ሂሣብ ዓመታዊ ኦዲት አካል እንዲሆን ተደርጓል፡፡

II. መ/ቤታችን በ2002/2003 አዲስ በዘረጋው የኦዲት ጊዜ አቆጣጠር ከጥር 1/ 2002 እስከ ታህሣሥ 30/ 2003 ዓ.ም የ129 በፌዴራል መ/ቤቶች የ2002 በጀት ዓመት ሂሳብ መደበኛ ኦዲት እና በ276 የወረዳና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶች የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ ኦዲትና ከተጠቃለለው የ PBS ሂሣብ ኦዲት አስተያየት ጋር እና አምስት ልዩ ኦዲቶችን አከናውኗል፡፡ በመደበኛና በልዩ ኦዲት የተከናወኑትን ኦዲቶች ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ሪፖርት የላከ ሲሆን፤ የመሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ድጋፍ ተከታታይ ኦዲትን በተመለከተ ደግሞ በየሩብ ዓመቱ እና የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተልኳል፡

## III. አዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

አዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት በርካታ የጥሬ የገንዘብና የአሠራር ጉድለቶች እና አፈፃፀማቸው ከደንብና መመሪያ ውጭ የሆኑ ሁኔታዎች ከገጽ 37 ጀምሮ በየአዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች እና በክልላዊ መንግሥት የወረዳና የከተማ አስተዳደር ፋይናንስ ጽ/ቤቶች የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ተከታታይ ኦዲት ደግሞ በተጠቃለለ መልኩ የቀረቡ ሲሆን፣ የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡

### 1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት

#### 1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ትክክለኛነት አያያዝና አጠባበቅ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የውስጥ ኦዲተሮች ባደረጉት ምርመራ በ3መ/ቤቶች ብር 113,266.41 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 6 ተመልክቷል/

በጉድለት ከታየው ገንዘብ ብር 309.09 መተካቱ የታወቀ ሲሆን፤ ቀሪውም ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

#### 1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፤ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ24 መ/ቤቶች የተለያዩ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ጉድለቶች እንዳሉ ተረጋግጧል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝሩ በአባሪ 7 ተመልክቷል/

ከታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያየዝ ጉድለቶች፤

- የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር የማይመሳከር መሆኑ፤

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ ከተገኘው ጥሬ ገንዘብ በማነስ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፤
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ /የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ መሆኑ፤
- በባንክ ሂሣብ ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች፣ የገቢ ደረሰኝ አለማዘጋጀትና ያለመመዝገቡ፤
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ መሆኑ፤
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ ሂሣብ መግለጫ ዜሮ ከወጪ ቀሪ እየታየ አላግባብ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የሚደረግ መሆኑ፤
- በውጭ ምንዛሪ ባንክ ያለ ገንዘብ /4102/ ተብሎ ሪፖርት የተደረገውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የባንክ ሂሣብ መግለጫ ያልቀረበለት መገኘቱ፤

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያገለጥ በመሆኑ፤ የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወቅቱ ተቆጥሮ ከመዝገብ ጋር እንዲመሳከርና በሂሣብ ማመዛዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ እንዲሁም የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ በየወሩ እንዲዘጋጅ አሳስበናል፡፡

## 2. ውዝፍ የሰነድ /ተሰብሳቢ/ ሂሳብ

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል፣ ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ43 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ብር 887,495,154.98 የሰነድ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 8 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 28,737,611.01 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 473,213,825.24 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 148,525,041.70 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 237,018,676.93 |
| ድምር | 887,495,154.98 |

ውዝፍ ሠነድ /ተሰብሳቢ/ የተገኘ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት የትምህርት ሚኒስቴር ብር 340.9 ሚሊዮን፤ ግብርና ቴክኒክ ሙያና ትምህርት ስልጣና ብር 121.70 ሚሊዮን፤ የመከላከያ ሚ/ር ብር 117.06 ሚሊዮን፤ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ 114.31 ሚሊዮን፤ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ 78.63 ሚሊዮን፤ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 25.03 ሚሊዮን፤ ግብርናና ገጠር ልማት ሚ/ር የምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት ብር 12.32 ሚሊዮን እና ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ብር 12.16 ሚሊዮን ይገኙበታል።

ስለተሰብሳቢው ሂሳቦች ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ከሰጡት ምላሽ በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ በተሰብሳቢ ሂሣብ ከታየው ከውጭ ጉዞ አበል ጋር ተያይዞ ሰነድ ያለባቸው ከደመወዛቸው 1/3 እየተቀነሰ እንደሚገኝ፤ እንዲሁም ለሶሰት የሚ/ር መ/ቤቱ ድርጅቶች ከሠራዊቱ ደመወዝ ተመላሽ ብድር መሰጠቱ አግባብ እንዳልሆነና እንደሚያስተካክሉት፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሠነድ ያለባቸው እንዲያወራርዱ እና ይህን ካልፈጸሙ በሕግ ለመጠየቅ በዝግጅት ላይ መሆኑን፤ በሂሣብ ክፍል ለማወራረድ የቀረበ በርካታ ሠነዶች መቅረባቸውንና ይህም በአጭር ጊዜ ለመጨረስ በጽ/ቤቱ የፋይናንስ መምሪያ ካለው የሰው ኃይል በላይ መሆኑን በመጥቀስ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር በቂ ባለሙያ በዘመቻ መልክ እንደሚያሰማራ፤ የማዕከላዊ ስታስቲክስ ሂሳቡ የሚወራረድበትን መፍትሄ ለመፈለግ ከኤጀንሲው እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተውጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ባደረገው ጥረት የብር 659,314.92 ሰነድ የሚወራረድበት መንገድ በመመቻቸት ላይ መሆኑንና ሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጡት መልስ ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ

የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

## 3. <u>የገቢ ሂሳብ</u>

### 3.1 <u>በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ሳይሰበሰብ የተገኘ የገቢ ሂሳብ</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

በ10 መ/ቤቶች ውስጥ ብር 4,381,208.42 በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 11 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 3,677,245.39 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 633,838.03 |
| ድምር | 4,381,208.42 |

ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (Harmonized System Code) እና (Custom Procedure Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ መቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

## 3.2 በወቅቱ ገቢ ያልደተረገ ውዝፍ ሂሳብ

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ህግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደገረግ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ ስድስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው ብር 212,683,707.39፤ በጉምሩክ የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ብር 67,862,205.83 ከአስመጪዎች ሊሰበሰብ የሚገባው የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 4,823,683.36 ከ6 ወር በላይ የቆየ ውዝፍ ሂሣብ የተገኘ ሲሆን፣ በአዲስ አበባ የወጪ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የተወሰነላቸውን የጊዜ ገደብ ጠብቀው ባለማጓጓዛቸው ቅጣት ከተወሰነባቸው ሾፌሮች እና ወኪሎች ያልተሰበሰበ ብር 15,000.00 በድምሩ ብር 285,384,595.58 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ ተገኝቷል፡፡ /ለዝርዝሩ አባሪ 10 ይመልከቱ/

በመሆኑም ስለሁኔታው ትኩረት ተሰጥቶት የመንግሥት ገንዘብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

## 3.3 ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ስር ባሉ ሶሰት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች ሶስት መ/ቤቶች በድምሩ ብር 58,642,597.86 የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፤ ከማን እንደተሰበሰበ ሳይገለጽ በኮድ በመሰብሰቡ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን በበቂ ማስረጃ ባለመደገፉ የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ 9 ተመልክቷል፡፡/

ስለሆነም ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙ ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 3.4 የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሳብ

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ በተደነገገው መሠረት ማንኛውም የመንግሥት ገቢ በሕጋዊ ደረሰኝ መሰብሰብና መመዝገብ ያለበት ቢሆንም በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ የተሰበሰበው ብር 10,000.00 ተገቢው የገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት በገቢ ተይዞ ተገኝቷል፡፡

ስለዚህ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሳብ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት እንዲያዝ በሪፖርት አሳስበናል፡፡

### 3.5 በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ 9 መ/ቤቶች የሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ብር 543,295,969.70 ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር በአባሪ 12 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 38,381,131.68 |
| ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 504,914,838.02 |
| ድምር | 543,295,969.70 |

በተጨማሪም በሚዛን ቴፒ፣ በሠመራ፣ ድሬዳዋ፣ በመደወላቡና በወሎ ዩኒቨርስቲዎች ምዝገባ ባለመከናወኑ የገንዘቡ መጠኑ የማይታወቅ የውስጥ ገቢ ሂሳብ ሪፖርት አለመደረጉ ተውቋል፡፡ ከንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች በስማቸው አንጻር የተገለጸውን ገንዘብ ድሬዳዋ ከሚገኙት የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የሰበሰቡት ገቢ አዲስ አበባ በሚገኙት ሁለት ፍ/ቤቶች

የወጪ በጀት የሚሳከላቸው ሲሆን፣ የወጪ ሂሣብ ሪፖርት እየተደረገ ገቢው ግን ለድሬዳዋ ገቢዎች ቢሮ እንደሚገባ መታወቁን በመግለጽ አሠራሩ እንዲስተካከል፤ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚዘጋጁት ሂሣብ መግለጫዎች ከተለያዩ ምንጮች የተገኙትን ገቢዎች አካቶ መያዝ እንዳለበት የሰጠነው አስተያየት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የተቀበሉት መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

## 3.6 በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

### 3.6.1 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩባለሥልጣን

#### 3.6.1.1 ጉምሩክን በተመለከተ

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በድምሩ ብር 5,094,327.00 በወቅቱ ባንክ ገቢ ሳይሆን ከ 1-11 ቀን በገንዘብ ያዥ እጅ የቆየ መሆኑ፤
- በሞጆ መቅረጫ ጣቢያ ከግል ባንኮች በቼክ በየእለቱ የሚሰበሰበዉ ገቢ ሳይመነዘር እስከ 15 ቀን የሚቆይ መሆኑ፤
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ ደረሰኞች የተሰበሰበ ቀረጥ ሳይመዘገብ ማስረጃው በገንዘብ ያዥ እጅ እስከ 15 ቀን የሚዘገይ መሆኑ፤
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በዲክራሲዮን ቁጥር C-26028/2009 ለገባው እቃ የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ሳይታወቅ ጥቅል ዋጋውን Cost Insurance Freight (CIF Value) በመውሰድ በአንድ የታሪፍ ቁጥር ላይ በመመደብ በ20% የጉምሩክ ቀረጥ ምጣኔ ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን ከነዚህ

ዕቃዎች ውስጥ በ30% እና በ35% የቀረጥ ምጣኔ መሰረት ሊስተናገዱ የሚገባቸው እቃዎችም መገኘታቸው፤

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በዲክራሲዮን ቁጥር C-7581,29/10/2009 እና C-24159,15/07/2009 በዋጋ ሠነድ ላይ የእያንዳንዱ ዕቃ ዝርዝር እና የእያንዳንዱም ዕቃ ዋጋ ሳይገለጽ በዝርዝር የዕቃውን ዋጋ የሚያሳይ የዋጋ ሰነድ እንደቀረበ ተደርጎ ቀረጥና ታክስ ተሰብስቦ መገኘቱ፤
- በአዲስ አበባ ኤርፖርትና በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብዙ ዕቃዎችን የያዙ የዋጋ ሰነዶች ላይ እያንዳንዱ ዕቃ የተመደበበት ታሪፍ ቁጥር በተሟላ ሁኔታ በዕቃዎች መረጃ መስጫ ዲክላራሲዮን ላይ ሳይሞላ ቀረጥና ታክስ ተሰብስቦ በመገኘቱ እያንዳንዱ እቃ የተመደበበት የታሪፍ ቁጥር ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉ፤
- በአዲስ አበባ ኤርፖርትና በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የእቃውን ዋጋና ታሪፍ ቁጥር ለመወሰን አሻሚ የሆኑ አንዳንድ የዋጋ ሰነዶች በፍተሻም ይሁን በመረጃ መስጫ ዲክላራሲዮን ላይ ስለእቃው ሁኔታ ተጨማሪ መረጃ ሳይቀርብ ዲክላራሲዮኑ ተቀባይነት ማግኘቱ፡፡

<u>በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት</u>

- ለማስጫኛ ከተከፈለዉ ወጪ ውስጥ 1/3ኛውን ብቻ በመውሰድ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ (Cost Insurance Freight Value) ውስጥ የሚካተት መሆኑ፣
- የማስጫኛ እና ኢንሹራንስ ደረሰኝ በአስመጪዎች በማይቀርብበት ጊዜ ለማስጫኛ ዋጋ የFOB ዋጋውን 10%፣ ለኢንሹራንስ ደግሞ የFOB ዋጋና የማስጫኛውን ድምር 5% በመውሰድ ቀረጥና ታክሱ የሚሰላ መሆኑ አሰራሩም ለረዢም ጊዜ የቆየ ከመሆኑም በላይ በመመሪያ ያልተደገፈ እና በልምድ ሲሰራበት የቆየ መሆኑን፣

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል ድሬ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ድርጅት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ በተሰጠ ተመሳሳይ የባንክ ፈቃድ ቁጥር ሁለት ጊዜ እቃ ወደ ውጭ አገር ልኮ መገኘቱ፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት የውጭ ምንዛሪ በUSD 3,723,716.75 እና በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በ18 ዲክላራሲዮኖች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ እቃዎች፣ የእቃው ዋጋ በባንክ ከተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ በUSD 610,907.27 በድምሩ በUSD 4,334,624.02 ብልጫ ሚያሳይ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል በE-2912, 30/01/2010 እና በ E-3475 , 02/04/2010 የተመዘገቡት ዕቃዎች አሴስ ሳይደረጉ ወደ ውጭ የተላኩ መሆኑ፣ እንዲሁም ተመዝግበው ቀጣዩን የጉምሩክ ስነስርአት ሳይፈጽሙ ለረገርም ጊዜ ሳይሰረዙ የቆዩ 4 የወጪ ዲክላራሲዮኖች መገኘታቸው፣
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት 40 ዲክላራሲዮኖች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሳይፈጸምባቸው ከተከፈቱ ከአመት በላይ የሆናቸው ዲክላራሲዮኖች በትራንዚት ቡድን ክፍል ተከማችተው መገኘታቸው፣
- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ ግልጽ የሆነ ጥፋት በፈጸሙ አንዳንድ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ላይ በአፈፃፀም መመሪያ መሠረት አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፣ በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት፣ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ለገባ ዕቃ በዋስትና የተያዘ ሂሣብ እንዲሁም በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዋስትና የተያዘ ሂሳብ፣ ቦንድ ጊዜ ያለፈበትና በባለስልጣኑ ፈቃድ ጊዜያቸው ያልተራዘመላቸው፤ በድምሩ ብር 302,972,929.66 በመመሪያው መሰረት የዋስትና ጊዜ ገደቡ ቢያልፍም ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተላለፈ መሆኑ፣
- የቫውቸር ተጠቃሚዎች ወደ አገር ውስጥ ያስገቡት የጥሬ እቃም ሆነ ወደ ውጭ የተላከውን ምርት መከታተያ ስርአት ቢኖርም ያልተተገበረ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ከጠቅላላው

የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚዎች ውስጥ 27 ድርጅቶች የተፈቀደላቸው የቫውቸር መጠን በድምሩ ብር 68,769,394.97 ቀረጥና ታክስ አለማወራረዳቸውና ቫውቸራቸውንም ያላሳደሱ መሆኑ፣

- በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር E-4051/2010 አባሪ ሰነዶች ውስጥ በኖቫ ስታር ጋርመንት ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ወደውጭ የተላኩ ተመሳሳይ ዕቃዎች በአንድ ኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ ሁለት አይነት ዋጋ ተጠቅሶ ተገኝቷል፡፡ ከተላኩት 1988 ኪሎ ግራም ተመሳሳይ እቃዎች ውስጥ፡-
  - ክብደቱ 1896 ኪሎ ግራም ለሆነ እቃ የአንዱ ዋጋ በዶላር 0.85፣
  - ቀሪው 92 ኪሎ ግራም ደግሞ የአንዱ ዋጋ በዶላር 4.285፣

በመሰላቱ በአነስተኛ የነጠላ ዋጋ የተስተናገዱት እቃዎች አገራችን ልታገኝ የምትችለውን የውጭ ምንዛሪ ያሳነሰ መሆኑ፡

<u>የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት</u>

- የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሣቦች አያያዝ ቡድን ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ ለክትትል እንዲያመች በየ15 ቀኑ ለደንበኞች አገልግሎት የሥራ ሂደት ሪፖርት ማድረግ የሚጠበቅበት ቢሆንም የደንበኞች አገልግሎት ሪፖርት የማይደርሰው መሆኑ፣
- የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሣቦች አያያዝ ቡድን ተሰብሳቢ (ቀሪ) ሂሣብን አስመልክቶ የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃ የማይዝ በመሆኑ፣ የውዝፍ አሰባሰብ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት እና የተዘረጋው የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት አስተማማኝ መረጃን ሊሰጥ የማይችል መሆኑ፣

<u>የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- ተሰብሳቢ ሂሳብ በሂሳብ ክፍሉ ተቀጽላ መዝገብ ተከፍቶ በየድርጅቶቹ ስም ተመዝግቦ ያልተያዘ በመሆኑ የቅ/ጽ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሒሳብ ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ መሆኑ እና ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆኑ ድርጅቶች ተለይተው ህጋዊ እርምጃ ለሚወስደው የስራ ክፍል ያልተላለፈ መሆኑ፣

## የአገር ውስጥ ገቢን በተመለከተ

- በሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,592,966.44 የተሰበሰበው ገቢ በወቅቱ ለትሬዠሪ ዝውውር አለመደረጉ፣
- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ዘግይቶ በተሰበሰበ የደመወዝ ገቢ ግብር እና የቅድመ ታክስ በድምሩ ብር 3,033,014.15 በወቅቱ ገቢ ባላደረጉ ግብር ከፋዮች ላይ ቅጣትም ሆነ ወለድ ያልተጣለባቸው መሆኑ፡
- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ግብር ከፋዮች በግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ማስታወቂያ ሳያቀርቡ ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ላይ ተቀናሽ የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች መገኘታቸው፡
- በምሥራቅ አዲስ አባባ ቅ/ጽ/ቤት 12 ግብር ከፋች የኤክሣይዝ ታክስ፣ በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት 4 ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋዮች በአዋጁ መሰረት ሪፖርት ያላደረጉ መሆናቸው ፡
- በምእራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ሁለት ድርጅቶች ካለፈው ዓመት የዞረውን የክምችት ሂሳብ ከወጪ ቀሪ በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ላይ  አስበልጠው በመያዛቸው ምክንያት ታክስ የሚሰላበት ገቢ በብር 581,753.86 ዝቅ ያለ በመሆኑ ሊሰበሰብ የሚገባው የንግድ ትርፍ ገቢ በዚሁ መሰረት ዝቅ የሚል መሆኑን፡

## የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት

- በፍሊራንስ ዜና አንባቢነትና ዘጋቢነት በኮንትራት ቅጥር ለሚያሰራቸው ሠራተኞች የሚቀንሰው የሥራ ግብር  በኮንትራት ውሉ መሰረት ድርጅቱ በሚከፍላቸው ደመወዝ ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ በአዋጁ መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባው ግብር ሳይሰበሰብ ሊቀር እንደሚችል፣

- በመሀል ከተማ ቢሮ በኩል በየወሩ ተጠናቅሮ የሚቀርበው የክልሎች፣ የአዲስ አበባና አካባቢው የቴሌቬዥን ፈቃድ ክፍያ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛነቱ እየተረጋገጠ ድርጅቱ በሚያቀርበው ወርሀዊ የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት የማይደረግ መሆኑ፤

__የጎንደር የሕክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ__

- ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን የውስጥ ገቢ፣ የልዩ ፋርማሲ የመድኃኒት ሽያጭ ገቢና የፕሮጀክት ፈንድ ለይቶ መዝግቦ አልያዘም፡፡ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈቃድ ሣያገኝ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝና ሌሎች ቫውቸሮችን አሣትሞ በመጠቀም ላይ መሆኑ፡

__የጎንደር ዩኒቨርስቲ__

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ማኒስቴርን ሣያሣውቅና ፈቃድ ሣያገኝ ብዛቱ 5000 ጥራዝ የውስጥ ገቢ የገንዘብ መቀበያ ደረሠኝ አሣትሞ እየተጠቀመበት መሆኑ፡

__በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ__

- የባንክ ሂሣብ ውስጥ ገቢ ተደርጎ የተገኘው ብር 789,611.92 የገቢውን ዝርዝር ሁኔታ የሚያስረዳ ማስረጃ ማግኘት አለመቻሉ፤

ታውቋል፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 4. __የወጪ ሂሳብ__

### 4.1 __የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ__

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በወሎ ዩኒቨርስቲ ለሥልጠና ወጪ ተብሎ ብር 2,365,730.00 እና በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት በቼክ ወጪ ለሆነ ብር 4,726.00 በድምሩ 2,370,456.00 ማስረጃ ሣይኖረው በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሣብ በቂ ማስረጃ እንድቀርብለት አለበለዚያ ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ አሳስበናል፡፡

## 4.2 የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ16 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 1,456,245,196.24 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 13 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---:|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 667,376.95 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 1,423,656,452.19 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 17,322,493.67 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 14,598,873.43 |
| ድምር | 1,456,245,196.24 |

ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል ፣ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር መረጃ ሳይደገፍ፤ በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ ተመዝገቦ የተገኘ ሲሆን፤ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር መረጃ አገልግሎት ወጪ የተደረገ መሆኑን የውጭ መልዕክተኞች ለተጠቀሱት ሚሲዮኖች ያለበቂ ማስረጃ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን፤ እንድሁም የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝን እንደወጪ ሂሣብ ማስረጃ በመያዝ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጎላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

## 4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ22 መ/ቤቶች ብር 584,611,188.04 ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 15 ተመልክቷል/

ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 582,229.09 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 441,159,161.46 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 141,048,725.9 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 1,821,071.52 |
| ድምር | 584,611,188.04 |

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣ የትምህርት ሚኒስቴር አሥራ ሦስት ዩኒቨርስቲዎችን ለማስገንባት በተገባው ውልና ከ1998 እስከ 2002 በጀት ዓመት ድረስ በተፈፀመው ክፍያ መካከል ብር 441,155,353.46 ከውሉ በላይ ክፍያ የተፈጸመ፣ በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር የተሠራው ሥራ መጠን በምስክር ወረቀት ሳይረጋገጥ 112.5 ሚሊዮን እንዲሁም ከክፍያ መቀነስ የነበረበት ብር 20.2 ሚሊዮን በድምሩ ብር 132.7 ሚሊዮን ከደንቡ ውጪ የተከፈለ እና ሌሎችም ከገቡት ውል ውጭ ክፍያ በመፈጸም፣ ሂሳቡን ሁለት ጊዜ በመያዝ ወጪ የተደረገ ፣ በሂሳብ ስሌትና በስምምነቱ ከተቀመጠው ዋጋ በማስበለጥ የተከፈለ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ በመሆኑ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት መመሪያ የተከተለ እንዲሆን፣ ያለአግባብ የተፈከለውም ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲሆን አሳስበናል፡፡

## 4.4 ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዢዎች

የዕቃና አገልግሎት ግዢ በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ33 መ/ቤቶች ብር 83,383,007.31 የመንግሥትን የግዢ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 14 ተመልክቷል፡፡/

ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 7,755,120.46 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 63,391,735.16 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 7,368,950.24 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 4,867,201.45 |
| ድምር | 83,383,007.31 |

ሆኖ ተገኝቷል።

ከደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ትምህርት ሚ/ር ብር 27.80 ሚሊዮን(ለአምቦ ዩኒቨርስቲ ማስፋፊያ ግንባታና የኮምፒዩተር ግዥ)፣ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ብር 11.94 ሚሊዮን (ለሠራተኞችና መምህራን መኖሪያ ሕንፃ ግንባታ)፣ የወሎ ዩኒቨርስቲ ብር 8.92 ሚሊዮን (ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት)፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 5.51 ሚሊዮን ለጄኔሬተር ግዥና የምግብ አቅርቦት እና የኢትዮጵያ ካርታ ስራ ድርጅት ብር 5.61 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

መ/ቤቶቹ ካልተከተሏቸው የግዥ ደንብና መመሪያዎች ውስጥ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሊፈጸሙ የሚገባቸውን ግዥዎች ያለጨረታ ማስታወቂያ መግዛት፣ በዋጋ ማወዳደሪያ /ፕሮፎርማ/ አማካኝነት መፈጸም ያለበትን ግዥ የዋጋ ውድድር ሳይደረግ ግዥ መፈጸም የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዢ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣መ/ቤቶቹም አስተያየቱን ተቀብለውታል፡፡

## 4.5 በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መሠረት በተገቢው ባለሥልጣን እየተፈቀዱ መከናወናቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ4 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 2,024,136.44 በተገቢው ባለሥልጣን ሳይታዘዝ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከዚህም ዋነኛው የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ለተፈፀመው ክፍያ ብር 1,682,850.00 በኃላፊ ሣይፀድቅ በወጪ የተመዘገበ ሲሆን በወቅቱ የኃላፊነት ዝውውር በመደረጉ ሳይፈረም መቅረቱን ኮሌጁ በሰጠው ምላሽ ገልጿል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 18 ተመልክቷል።/

ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---:|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 132,996.70 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 1,682,850.00 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 208,289.74 |
| ድምር | 2,024,136.44 |

ስለሆነም ማንኛውም ወጪ በሚመለከተው ባለሥልጣን እየተፈቀደ መከፈል እንዳለበት አሳስበናል፡፡

## 4.6 የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ

በበጀት ዓመቱ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በተለያየ ምክንያት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ብር 1,940,811,592.24 ተገኝተቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 9 ተመልክቷል/

ሒሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

| | | |
|---|---|---|
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | | 1,938,971,659.01 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | | 1,839,933.23 |
| በድምሩ | ብር | 1,940,811,592.24 |

የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ካልተቻለው ሂሣብ ውስጥ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ለሠራዊቱ ደመወዝ፣አበልና ማበረታቻ ወጪ ያደረገው ብር 1,708,115,690.49 እና በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰሜን እና ማዕከላዊ ዕዝ ጠቅላይ መምሪያዎች ወጪ የተደረገውን የሥራ ማስኬጃ ለማጣራት የፈራሚዎች ስምና የፊርማ ናሙና ባለመቅረቡ ብር 165,686,455.58፤ እንዲሁም የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ ብር 24,167,053.26 እና የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ ብር 38,575,487.91 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሶስቱ የደህንነት መ/ቤቶች ለደመወዝ ለነዳጅና ለስልክ ወዘተ… ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ለማረጋገጥ በኮድ የተከፈለውን ደመወዝ የሠራተኞቹ ኮድ፤ የመኪኖች ታርጋና የስልክ ዝርዝሮች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ መ/ቤቶቹ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት መልስ አልሰጡም፡፡ ሆኖም በመውጫ ስብሰባ ወቅት የደህንነት መ/ቤቶቹ ከመ/ቤታቸው የሥራ ፀባይ አኳያ መረጃዎቹን ለመስጠት እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር ዘግይቶ በላከው መልስ ከመረጃው ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰዉ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት በመሆኑ፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ሚስጥራዊ ሰነዶችን አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ሆኖም ለወደፊቱ የሂሣብ ማስረጃዎቹ ተሟልተው መያዝ እንዳለባቸውና ለኦዲት ሲፈለጉ ሊቀርቡ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

## 4.7 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆረጠለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች በብር 11,043,820.01 የተገዙ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል:: /ዝርዝሩም በአባሪ 17 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 468,376.95 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 1,340,219.93 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 8,877,063.64 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 358,159.49 |
| ድምር | 11,043,820.01 |

ሆኖ ተገኝቷል::

ከዚህ ውስጥ በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል በብር 8,868,553.64 የተገዛ ቋሚ ዕቃና የጅማ ዩኒቨርሲቲ በብር 1,340,219.93 የገዛውን ቋሚ ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሲሆኑ፣ የዚህ ዓይነት አሠራር ለንብረት ብክነት ስለሚያጋልጥ አሠራሩ ተገቢ ሆኖ ባለመገኘቱ ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ ሊደረግና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበላቸው ንብረቶች ለየመ/ቤተቶቹ አገልግሎት ለመዋላቸው በማስረጃ እንዲረጋገጥ ለመ/ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 4.8 አላግባብ በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ8 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች የተከፈለ ቅድሚያ ክፍያ ብር 274,651,211.51 በወጪ የተመዘገቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 15.1 ተመልክቷል/

ሂሣቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 65,000.00 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 151,051,400.04 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 123,534,811.47 |
| ድምር | 274,651,211.51 |

ቅድሚያ ክፍያን በወጪ ከመዘገቡት መ/ቤቶች ውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 115.69 ሚሊዮን፣ አርባ ምንጭ ዩንቨርሲቲ 112.06 ሚሊዮን ለቋሚ ዕቃዎች ግዥ እና ጂማ ዩንቨርሲቲ 37.53 ሚሊዮን ለሕንፃ ግንባታ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፤ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብለት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ ለመ/ቤቶቹ አሳስበናል፡፡

## 4.9 የወጪ የሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ22 መ/ቤቶች ብር 74,834,786.42 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ 21 ተመልክቷል/

ሂሣቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፡-

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 25,347,039.03 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 17,111,230.38 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 32,023,436.09 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 353,080.92 |
| ድምር | 74,834,786.42 |

የወጪ ሂሣብ መደብ ሣይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የውሃና ኢነርጂ ሚ/ር ብር 31.80 ሚሊዮን፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ 23.6 ሚሊዮን ና የአማኑኤል ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 13.53 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ ከበጀት አጠቃቀም አንፃር ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡
በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

## 5. የተከፋይ ሂሣብ

### 5.1 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ20 መ/ቤቶች ብር 247,202,349.65 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ 22 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 9,553.79 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 125,659,984.57 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 121,342,761.14 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 190,095.15 |
| ድምር | 247,202,349.65 |

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 117.31ሚሊዮን፣ በጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 56.99 ሚሊዮን፣ ትምህርት ሚ/ር ብር 28.15 እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 26.99 ሚሊዮን ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2002 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 117,314,864.62 የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በመጥቀስ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት፣ ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈልና ሌሎችም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

## 6. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር በርካታ ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 6.1 ከበጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ22 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ብር 763980084.01 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 19 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 1,814,721.65 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 755,123,434.69 |
| የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች | 5,283,333.18 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 1,758,594.49 |
| ድምር | 763,980,084.01 |

ሆኗል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ እንደማይቻል በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተጠቀሰ በመሆኑ፤ ለወደፊቱም መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙም የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

### 6.2 ያልተሠራበት በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣በ33 መ/ቤቶች ብር 652262874.59 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 20 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

| | |
|---|---|
| የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች | 38,431,121.98 |
| የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች | 115,660,504.63 |
| የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች | 498,171,247.98 |
| ድምር | 652,262,874.59 |

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው ውስጥ ሳይሰራበት የተገኘ ሲሆን በጀትን ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም ሌሎች መ/ቤቶች ሊጠቀሙበት የሚችሉትን በጀት እንዳይጠቀሙ ከማድረጉም በላይ የብቃት ማነስን (inefficiency) የሚያመለክት በመሆኑ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 7. የንብረት አያያዝና አጠባበቅ

### 7.1 የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው የዕቃና ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም:: በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው:: መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች ተገኝተል፡፡

- ለቋሚ ዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ — 2 መ/ቤቶች
- ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ — 3 መ/ቤቶች
- የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ — 22 መ/ቤቶች
- የቋሚ ዕቃ መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም ምዝገባ ያላከናወኑ — 16 መ/ቤቶች

እና የቋሚ ዕቃ ቆጠራ ተደርጎ ከመዝገብ ጋር ሲመሳከር በታየው ልዩነት ላይ እርምጃ ያልተወሰደ አንድ መ/ቤት መሆናቸው በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ 23 ተመልክቷል፡፡/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያከናውኑ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 7.2 ልዩ ልዩ የንብረት አያያዝና አስተዳደር ችግሮች

### የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች

#### በፌደሬሽን ምክር ቤት

- ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረጉ 445 CDዎች ሆነው በንብረት መዝገብ ላይ የተመዘገቡት ግን 328 CDዎች ብቻ በመሆናቸው 117 CDዎች በመዝገብ ሳይመዘገቡ መገኘቱ፡፡
- ቶነር 49-A የተባለ ዕቃ የዕቃ ወጪ መጠየቂያ (ሞ/20) እንዲሁም የዕቃ ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ሣይዘጋጅለትና በኃላፊ ሳይፈቀድ በመዝገብ ላይ በወጪ መገኘቱ፤

#### በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

- የተለያዩ ከትምህረት ሚኒስቴር የመጡ አዳዲስ ጠረጴዛዎች እና ወንበሮች ያለምንም አገልግሎት ጥበቃው አስተማማኝ ባልሆነ ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤

#### በተወካዮች ምክር ቤት

- ከ1995 በጀት ዓመት ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጠ የጥርስ ህክምና መሣሪያ እና ሌሎች ለዚሁ የሚያገለግሉ ዕቃዎች እንዲሁም ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ኮምፒዩተሮች መገኘታቸው፤

### የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

#### በአገር ውስጥ ገቢ አዳማ ቅ/ጽ/ቤት

- አንድ ፎርክሊፍት መኪና፣ የሞተር ቁልፍ እና የጎማ መፍቻ፣ ለበከልቻ ትራንስፖርት በነፃ የተሰጠ መሆኑ፣

**ጉምሩክን በተመለከተ**

**የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት**

- ተሽከርካሪዎቹ የሚገኙበት ቦታ አጥር የሌለው በመሆኑ የተሽከርካሪዎቹ የተለያዩ አካሎች ለስርቆት የተጋለጡ መሆናቸው፣
- የአንድ ተሽከርካሪ ሞተር ከሻንሲው (ቦዲው) ተለያይቶ ለብቻው የሚገኝ መሆኑ፣
- ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ውርስ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ቢኖሩም እስከአሁን ግን ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑና አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች እየተበላሹ ያሉበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ብዙ ተሽከርካሪዎች በሞ/265 ውርስ በሚደረጉበት ጊዜ የተሽከርካሪዎቹ ዋና አካል የሆኑ የሞተር እና ሻንሲ ቁጥራቸው ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ ፤

**አዳማ ቅ/ጽ/ቤት**

- በኬላ ላይ ከግለሰቦች የተወረሰው ንብረት (በሞዴል 270) ሙሉ በሙሉ ወደ መጋዘን (የእቃ መረከቢያ ሞዴል 265) ገቢ መደረጉ ሲጣራ በሞዴል 270 ቁጥር 887555 ኬላ ላይ የተወረሰ ንብረት በሞዴል 265 ቁጥር 317716 ወደ መጋዘን ገቢ ሲደረግ ከፊሉ ገቢ ሳይደረግ የቀረ መሆኑ፣
- በሽያጭ የተወገደና ወደመጋዘን የገባ እቃ የተለያየ ሆኖ መገኘቱ፣
- ንብረቱ ገቢ የተደረገበት እና በሽያጭ ሲወገድ ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረገበት ደረሰኝ ቁጥር የማይጠቃቀስ መሆኑ፣
- እቃዎች ተይዘው ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ፣
- የእቃ መመዝገቢያ ቢን ካርድ ስርዝ ድልዝ የበዛበት መሆኑ፣
- የእቃዎች አቀማመጥ የተዘበራረቀ ሆኖ መገኘቱ፤

**ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት**

- በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ያልተወረሱ ወይም በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ዕቃዎች ወይም ንብረቶች ለመንገደኞች በሚሰጥ ደረሰኝ (ሞዴል 270) የሚያዙ

ሲሆን፣ ጉዳዩ ተጣርቶ እቃው እንዲወረስ ሲደረግ በውርስ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 265) በቅድሚያ ከተያዘበት የመንገደኛ ደረሰኝ እና እንዲወረስ ከታዘዘበት ደብዳቤ ጋር የማይጠቃቀስ በመሆኑ ከመንገደኞች የተወረሱት በሙሉ በውርስ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 265) ገቢ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለመቻሉ፤

<u>**አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት**</u>

- በውርስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ እቃዎች አያያዝ በናሙና ሲታይ የተለያዩ ንብረቶችና እና ኬሚካሎች ሳይወገዱ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በውርስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

<u>**የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት**</u>

- የምግብ ውጤቶች እና መድሐኒቶች ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ውስጥ የቆዩና በአዋጁ መሰረት ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድ ከስድስት ወር እስከ አራት አመት የቆዩ መሆኑ፣

<u>**በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ**</u>

- መ/ቤቱን የለቀቁ ሠራተኞች በውሰት የወሰዱትን ንብረት ተመላሽ አለመደረጉ፣

<u>**በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል**</u>

- በመ/ቤቱ በብር 25,313.13 የተገዛ ዩኒፎርምና በብር 40,560. የተገዛ ነዳጅ በንብረት መዝገብ ያልተመዘገበ መሆኑ ፤
- መ/ቤቱን የለቀቁ ሠራተኞች በውሰት የወሰዱትን ንብረት ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ፤

<u>**የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም**</u>

- በዕቃ መጋዘን ውስጥ ከተቀመጡ አንድ ዓመት የሆናቸው ከዩ.ኤን.ዲፒ በእርዳታ ተገኝተው ርክክብ ያልተፈጸመባቸውና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው በርካታ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ መደርደሪያዎች፣ ሳፋዎችና የመሳሰሉት ንብረቶች መኖራቸው፡

- የቋሚና የአላቂ ንብረቶች ገቢና ወጪ በሞዴል 70/ሐ ካርዱን ኮፒ በማድረግ ብቻ የሚመዘግብ መሆኑና አልፎ አልፎ ወዲያው ገብተው ወዲያው ለሚወጡ የማይመዘገብ መሆኑ፣
- አሮጌ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች የመመዝገቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶላቸው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ንብረት ክፍሉ ተረክቦ በማስቀመጥ በሽያጭ እንዲወገዱ አለመደረጉ፣

<u>የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት</u>

- በግ/ቤት የዕቃ መደርደሪያ ባለመዘጋጀቱ ተደራርበው እና ለአያያዝ በማያመች ሁኔታ መቀመጣቸው፣

<u>የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር</u>

- በዋናው መ/ቤት በሚገኘው የወዳደቁ መጋዘን ክፍል ውስጥ ያሉ ዕቃዎች የዕቃ መደርደሪያ የሌላቸውና ዓይነት በዓይነት ሳይለዩ በመሬት ላይ የተቀመጡ መሆኑ፣

<u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ</u>

- በክምችት ክፍል ብር 881,846.17 በድልድል ክፍል ብር 692,288.71 በድምሩ ብር 1,574,134.88 የሚገመቱ ቁሳቁሶች /ንብረት/ በጉድለት የተገኘ መሆኑና በዚሁ መሠረት ጽ/ቤቱ የወሰደው እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱት ችግሮች እንዲስተካከሉ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

## 7.3 <u>አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ያልተወገዱ የተለያዩ ንብረቶች</u>

መጠገን ወይም ለሌላ አገልግሎት መዋል የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ፤ በ14 መ/ቤቶች የተገኙ ሲሆን፤ ንብረቶቹም ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ወንበሮች፣ የመኪና መለዋወጫዎች እንዲሁም የተለያዩ ዕቃዎች ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ፤አገልግሎት የማይሰጡና ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት፤ ተለይተው እርምጃ ያልተወሰደባቸው

የተለያዩ ንብረቶች ለረዥም ዓመታት ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ ተውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ 23 ተመልክቷል/

በመሆኑም ንብረቶቹ የበለጠ ሳይበላሹ በመንግሥት መመሪያ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንዳሚገባ አሳስበናል፡፡

7.4 <u>ተሽከርካሪ</u>

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

| | | |
|---|---|---|
| • ሊብሬ ያልቀረበላቸው | በ8 መ/ቤቶች | 271 ተሽከርካሪዎች፤ |
| • በብልሽት ምክንያት የቆሙ | በ13 መ/ቤቶች | 186 ተሽከርካሪዎች፤ |
| • የሻንሲና ሞተር ቁጥር ከሊብሬ ጋር ተቀያይሮ ተመዝግቦ የተገኘ | በ1 መ/ቤት | 2 ተሽከርካሪዎች፣ |
| • የቻሲና የሞተር ቁጥራቸው የማይታወቅ | በ2 መ/ቤቶች | 10 ተሽከርካሪዎች |
| • ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ | 1 መ/ቤት | 3 ተሽከርካሪዎች |

መኖራቸው ታውቋል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ 24 ተመልክቷል/

መ/ቤቶቹም በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ መኪናዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዳለባቸው፤ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ፤ የቻሲና የሞተር ቁጥራቸው የማይታወቅ እና ሊብሬ ያልቀረበላቸው ደግሞ ጉዳዩ ተጣርቶ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

7.5 <u>የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም</u>

<u>የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም</u>

- ለነዳጅና ቅባቶች ግዥ ቅጽ ያልተዘጋጀና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

ለነዳጅና ቅባቶች ግዥ ቅጽ እንዲያዘጋጅ፤ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

8. <u>ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ</u>

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:–

<u>በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት</u>

በ2000 በጀት አመት በቀረበው የኦዲት ውጤት እና የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት እንዲስተካከል አስተያየት የሰጠበት የሳጥን ሂሳብ ብር 216,256.11 ሳይስተካከል የተገኘ በመሆኑ፣ እንዲስተካከል ለድርጅቱ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

<u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲፕሎማቲክ ሚሲዮን</u>

<u>የተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

| | |
|---|---|
| በ2000 በጀት ዓመት | |
| ኮፒ ደጋፊ ማስረጃ የቀረበለት | ብር 5,845,294.98 |
| ደጋፊ ማስረጃ የሌለው | 9,445,831.56 |
| በድምሩ | 15,291,226.54 |

መገኘቱን በመግለጽ፣ ኮፒ ማስረጃ ለቀረበለት ዋናው፣ ምንም ማስረጃ ሳይኖረው ለተመዘገበው ማስረጃ እንዲቀርብለት እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በ2002 በጀት ዓመት ኦዲትም ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑን፣ በመግለጽ ለሂሣቦቹ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

<u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

በ2000 በጀት ዓመት

| | |
|---|---|
| • ኮፒ ደጋፊ ማስረጃ የቀረበለት በከፊል ማስረጃ የቀረበለት | ብር 4,979,694.56 |
| • ምንም አይነት ማስረጃ ያልቀረበለት | 2,196,959.70 |
| ድምር | 7,176,654.26 |

በዚህ ኦዲትም ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑን በመግለጽ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

## የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

- የተቋሙ ሠራተኛ አቶ ምኒሊክ አለማየሁ የሠሌዳ ቁጥር 412187 ሲያሽከረክሩ በራሳቸው ጥፋት በደረሰው አደጋ ከተቋሙ ሥራ ማስኬጃ በ2001 በጀት ዓመት ብር 32,816.88 ለካሣ ተከፍሎ በመገኘቱ ከሠራተኛው ሊተካ ስለሚባ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በ2002 በጀት ዓመትም ገንዘቡ እንዳልተተካ በመግለጽ በድጋሚ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡
- በ2001 በጀት ዓመት በተቋሙ በተደረገ ኦዲት 2 ሞተር ብስክሌቶች የጠፉ በመሆኑ ክትትል ተደርጐ የንብረቶቹ ሁኔታ እንዲጣራ አሳስበናል፡፡ ሆኖም በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ እንዲታወቅ በመግለጽ በድጋሚ ክትትል ተደርጐ ሁኔታው እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

ተቋሙ በላከው መልስ በሠራተኞች መቀያየር ምክንያት ክትትሉ ጠንካራ እንዳልነበረ ጠቅሶ ጉዳዩ  እልባት እስኪያገኝ በቋሚነት የሕግ ባለሙያ መድቦ ክትትል እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ በተሰጠው የኦዲት የማሻሻያ ሃሳብ መሠረት እርምጃ አለመውሰድ አግባብ አለመሆኑን ገልፀን የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች በኦዲት አስተያየቶች መሠረት እርምጃ መወሰዱን በቅርብ ክትትል እንዲያደርጉ አስገንዝበናል፡፡

## 9. የ 'PBS' ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲቶች ውስጥ የተሰጡ የኦዲት አስተያየቶችና ጉልህ የሆኑ የኦዲት ግኝቶች ማጠቃለያ ሪፖርት

በአሁኑ ወቅት የሚያከናውነው የ'PBS' ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት የኢትዮጵያ መንግሥትና የዓለም ባንክ ባደረጉት ስምምነት መሠረት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS) ፕሮጀክት ተከታታይ (Continuous) ኦዲት ሲሆን፣ ይህም ኦዲት በየሩብ ዓመቱ እየተከናወነ በስምምነቱ መሠረት ሪፖርቱ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር እና ለዓለም ባንክ በወቅቱ እንዲደርስ ይደረጋል፡፡ ይህ ኦዲት የሚሸፍናቸው ሴክተሮች የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ የሆኑትን በወረዳና በክልል ደረጃ የሚገኙ የጤና፣ የትምህርት፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት፣ የንጹህ ውሃ አቅርቦትና የገጠር መንገድ ሴክቶሮችን  ነው፡፡

በመጀመሪያው የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBSI) ፕሮጀክት ወቅት (ከሚያዝያ/98 - ግንቦት/01)ድረስ በነበረው የኦዲት ስምምነት (ToR) መሠረት ተከታታይ ኦዲቱ አራት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን፣ እነዚህም የበጀት ድልድል ቀመርን (Fairness)፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን (Transparency and Accountability)፣ የበጀት ዕድገትን (Additionality) እና ህጋዊነትን (Fiduciary Responsibility) በተመለከተ እንደ ነበር ይታወቃል፡፡

ይሁንና ይህ የመጀመሪያው ዙር ፕሮጀክት (PBS I) ግንቦት/2001 የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ሁለተኛው ዙር የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ (PBS II) ፕሮጀክት ደግሞ ከግንቦት/2001 መጨረሻ ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ በተገባው የውል ስምምነት መሠረት የተከታታይ ኦዲቱም ስምምነት (ToR) በተመሣሣይ ሁኔታ የተሻሻለ ሲሆን፣ በተሻሻለው የኦዲት ስምምነት መሠረት በመጀመሪያው ፕሮጀክት ውስጥ ይቀርቡ ከነበሩት አራት ክፍሎች ውስጥ የሁለተኛው ፕሮጀክት የመጀመሪያዎቹን ሦስት ክፍሎች ከተከታታይ ኦዲቱ ውስጥ በማስወጣት በአራተኛው ክፍል ላይ ማለትም በህጋዊነት (Fiduciary Responsibility) ላይ ብቻ ተከታታይ ኦዲቱ እንዲያተኩር ተደርጓል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ተከታታይ ኦዲቱ የፕሮጀክቱ ሂሣብ ዓመታዊ ኦዲት አካል እንዲሆን በመፈለጉ ነው፡፡

ስለሆነም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሁለተኛ ዙር (PBS II) ፕሮጀክት ተከታታይ ኦዲት ዋና ትኩረት በእነዚህ መሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ( በወረዳና በክልል ደረጃ) የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ላይ በመሆኑ፣ በየሩብ ዓመቱ እየተጠቃለለ የሚላከው የተከታታይ ኦዲት ሪፖርት ግኝቶች የሚያተኩረው በገንዘብ መጠን (quantitative amount) ላይ ሳይሆን፣ በዓይነት ላይ (Qualitative) በመሆኑ፣ ዋና ዋና ግኝቶች የሚባሉት በዓይነት እንጂ በመጠን አለመሆናቸውን እንገልፃለን፡፡

በመሆኑም በ2002/3 የኦዲት ዘመን ለተከናወኑት ተከታታይ ኦዲቶች የተሰጡት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት የኦዲት አስተያየቶችና በየመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች የሚታዩት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በአብዛኛው ተመሣሣይነት ያላቸው በመሆኑ፣ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶቹ በአንድ ላይ ተጠቃለው በሚከተለው ሁኔታ ለዓይነት ቀርበዋል፡፡

ሀ/ <u>በ2002/3 የኦዲት ዘመን የታዩ ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች</u>

በአሁኑ ወቅት የተወሰነ መሻሻል ቢታይም፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ዋና ዋና የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች በበርካታ የመሠረታዊ አገልግሎት አቅራቢ መ/ቤቶች ውስጥ በመታየት ላይ ናቸው፡፡ እነሱም፣

- በየወቅቱ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ (ሌጀር) ከወጪ ቀሪ ጋር የማይመሳከር መሆኑ፣
- የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ በየወሩ የማይዘጋጅ መሆኑ፣
- የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች መቆጣጠሪያ የሚረዱ ደጋፊ ሌጀሮች (Subsidiary ledgers) አለመቋቋማቸውና በወቅቱ አለመወራረዳቸው፣
- ለቅድሚያ ሂሣብ ክፍያዎች የተወሰኑ ክፍያዎች በበቂና አግባብ ባላቸው ማስረጃዎች አለመደገፋቸው፣
- የሂሣብ እንቅስቃሴዎች (Transportations) በወቅቱ አለመመዝገባቸው፣
- ወርሃዊ የሂሣብ መግለጫዎች በአብዛኛው በወቅቱ እየተዘጋጁ ለሚመለከተው ክፍል አለመላካቸው፣
- የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ መዝገብ በአብዛኛው መ/ቤት አለመቋቋም፣
- ቋሚ ዕቃዎች በአብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እየተደረገ ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር በአብዛኛው የማይመዛዘኑ መሆኑ፣ እና
- ለኦዲት ሥራ ድጋሚ በሚኬድበት ወቅት፣ ባለፈው ኦዲት ወቅት በታዩ ድክመቶች ላይ በአብዛኛው የማሻሻያ እርምጃ አለመወሰዱ፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ድክመቶች አለመሻሻልና በወቅቱም እርምጃ ላለመወሰዱ

ኦዲት ተደራጊዎች ሲጠየቁ የሚሰጧቸው መልሶች (Management Responses) ሲጠቃለሉ የሚከተለውን ይመስላሉ፡-

- ከፍተኛ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና የበጀት እጥረት መኖር፣
- ከፍተኛ የሥራ ጫና መኖርና የግንዛቤ ማነስ፣ እና
- የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለጉዳዩ በቂ ትኩረት አለመስጠት፣

ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ለ/ <u>የተሰጡት የኦዲት አስተያየት</u>

| | |
|---|---|
| አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት( Clean ) | 4 |
| ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for ) | 266 |
| የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት ( Adverse ) | 3 |
| በተለያዩ ምክንያቶች የመ/ቤቶቹ ን ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ባለመቻሉ አቋም ለመውሰድ (Disclaimer) ያልተቻለባቸው | 3 |
| በድምሩ | 276 |

10. ልዩ ኦዲት

የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን፣

- በቁጥር-/መመ-መ9 1935 በ30/4/2002 በፃፈው ደብዳቤ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ኘሮጀክት፣ የመስኖ ኘሮጀክቱ ከተጀመረበት ጥቅምት 1997 እስከ ነሐሴ 2001
- በቁ.ድሬ 1266/07/03 በ11/01/2003 በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም ለድሬዳዋ ገጠር ከተሞች ለሚከናወነው የኤሌክትሪክ ማስፋፊያ ሥራ ከሕንድና ከሌሎች ውጭ ሀገራት ተገዝተው ድሬዳዋ UEAP ስቶር የተራገፉ ትራንስፎርመሮችና አሉሚኒየም ግኘር በተመለከተ፣

የሴቶች ፤ሕጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚ/ር የቀድሞው የአዲስ አበባ የማገዶ እንጨት ተሸካሚ ሴቶች ማሕበር የማሕበሩን ከJuly 8/2009 —July 7/2010 ያለውን ሂሳብ

የትግራይ ክልል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሂሳብ፣እና

የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሂሳብ

ኦዲት ተደርጎ እንዲቀርብላቸው ተጠይቆ፣ በመ/ቤታችን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ልዩ ኦዲት አከናውኖ የተገኘውን ውጤት ለኮሚሽኑና ለሚመለከታቸው እንዲሁም ለጠያቂዎቹ ሪፖርት የላከ ሲሆን ፤በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ዋናዋና ግኝቶች ዝርዝር በዘሁ ጥራዝ ገጽ 176 ቀርቧል፡፡

# የ2002/2003 በጀት ዓመት የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን

# መ/ቤቶች ኦዲት አመታዊ ሪፖርት

## የፋይናንሻልና ሕጋዊነት ኦዲት ዕቅድ አፈፃፀም

በፋይናንስና ኮሚኒኬሽን ዳይሬክቶሬት በ2002 በጀት አመት 31 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችን ሂሳብ ኦዲት ለማድረግ አቅዶ የ31 መ/ቤቶችን ኦዲት አከናውኗል፡፡ ይህም 100% እንደተከናወነ ያሳያል፡፡ የኦዲቱ ሥራ የተከናወነው በ1 ዳይሬክቶሬትና በ2 የኦዲት ማናጀሮች ነው፡፡

ዳይሬክቶሬቱ በ2002 በጀት ዓመት በፌዴራል መ/ቤቶች ላይ በመደበኛ ኦዲት ያከናወነው የፋይናንስ ኦዲት የመንግስት አጠቃላይ ገቢና ወጪ ሂሳብን ጨምሮ 31 የኦዲት ሪፖርቶችን ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች የላከ ሲሆን፤ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር ሲተነተኑ፣

- አልፎ አልፎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion) 15 መ/ቤቶች፣
- የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse opinion) የተሰጠባቸው 2 መ/ቤቶች፣
- አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean opinion) የተሰጠባቸው 10 መ/ቤቶች እንዲሁም
- ሂሳባቸውን ባለመዝጋታቸው የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠባቸው 4 መ/ቤቶች ሲሆኑ ዝርዝርሁኔታው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ 1-5 ተመልክቷል፡፡/

## በኦዲት ሥራው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

በኦዲት ሥራው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 1. የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ

### 1.1 የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ጉድለት

የተሰበሰበው ገቢ ሁሉ በወቅቱ ወደ ባንክ ገቢ መደረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የወለጋ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ባደረገው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ረዳት ገንዘብ ያዥ ከነበሩት ከአቶ አብርሃም በሊና ብር 91,178.43 እና ረዳት ገንዘብ ያዥ ከነበሩት ከአቶ ደጀኔ መርጋ ብር 309.63 በድምሩ ብር 91,488.06 መጉደሉ ታውቋል፡፡

በየእለቱ የተሰበሰው ሂሳብ በወቅቱ ባንክ ገቢ የማይደረግና ገቢ መደረጉም በየእለቱ ቁጥጥር የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡

የተሰበሰበ ገቢ በእለቱ ወደ ባንክ እንዲገባና ሂሳቡም በትክክል የገባ መሆኑ እየተረጋገጠ በእለቱ መመዝገብ እንዳለበት አስተያየታችንን የሰጠን ሲሆን ዩኒቨርሲቲውም ይህን ሊያረጋግጥ የሚችልበትን የቁጥጥር ስርአት ሊዘረጋና በጉድለት የተመለከተውም ሂሳብ እንዲተካ ተገቢው ክትትል መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

አቶ አብረሃም በሊና ያጎደሉትን ገንዘብ በተመለከተ ጉዳዩ በስነምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና በፍርድ ቤት የተያዘ መሆኑን እና አቶ ደጀኔ መርጋ ያጎደሉት ብር 309.63 በደረሰኝ ቁጥር 371634 ገቢ መደረጉን ዩኒቨርሲቲው በላከው ምላሽ ተገልጿል፡፡

## 2. የገቢ ሂሣብ

### 2.1 የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ

ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ መሰብሰቡንና የተሰበሰበውም ገንዘብ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገቢው ከየትኛው የማስተወቂያ አይነት እንደተሰበሰበ ለመለየት ባለመቻሉ በተመኑ መሰረት መሰብሰቡን ማረጋገጥ ያልተቻለ የማስታወቂያ ሽያጭ ብር 5484.00 እንዲሁም አጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ድርጅትም በተመሳሳይ መልኩ ከአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ማጠናቀሪያና የከፍተኛ የትምህርት መግቢያ ፈተና እንዲሁም ከተለያዩ የፈተና ጣቢያዎች ከተመዘገቡ ተፈታኞች የተሰበሰበው ሂሳብ በኤጀንሲው የገቢ አሰባሰብ አፈፃፀም መመሪያና ደንብ ላይ በተገለጸው ታሪፍ መሠረት የተሰበሰበ መሆኑንና ከየክልል ጣቢዎች

የተሰበሰበውም ገቢ በአግባቡ ተሰብስቦ ለኤጀንሲው ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የተፈታኞች ዝርዝር ከክሬዲት አድቫይሱና ከገቢ ቫውቸር ጋር እንዲሁም የክልል ጣቢያዎች ከሚልኩት ዴቢት አደቫይስ ጋር የማይያያዝ ወይም የማይጣቀስ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የተሰበሰበው ገቢ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማጣራት አይቻልም ይህም የገቢውን ትክክለኛነት አጠራጣሪ ያደርገዋል፡፡

ገቢው ከየትኛው የማስታወቂያ አይነት እንደተሰበሰበ ለመለየት እንዲቻል በሂሳብ ማስረጃዎች ላይ የማስታወቂያው አይነት መጠቀስ እንዳለበት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያሳሰብን ሲሆን፣አጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲም የተፈታኞችን ዝርዝር ከክሬዲት አድቫይስ፣ ከገቢ ቫውቸር፣ እንዲሁም የፈተና ጣቢያዎች ከሚልኩት ዴቢት አድቫይስ እንዳመጣጡ ከምዝገባው ጋር በማጠቃቀስ ለኦዲት በሚመች መልኩ ማስረጃውን አጠናቅሮ መያዝ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የሁለቱም መ/ቤቶች የስራ አመራሮች የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብለውታል፡፡

## 2.2 ያልተሰበሰበ የገቢ ግብር

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 ክፍል 2 ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ ስለመወሰን በአንቀጽ 12.ተ.ቁ.1 በተጠቀሰው መሠረት የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በፍሊራንስ ዜና አንባቢነትና ዘጋቢነት በኮንትራት ቅጥር ለሚያሰራቸው ሠራተኞች የሚቀንሰው የሥራ ግብር በቋሚነት ከሚሰሩበት መ/ቤት የሚከፈላቸውን ደመወዝ መሰረት አድርጎ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የስራ ግብሩ የሚቀነሰው በኮንትራት ውሉ መሰረት ድርጅቱ በሚከፍላቸው ደመወዝ ላይ ብቻ የተመሰረተ በመሆኑ ሰራተኞች ሊከፍሉ የሚገባቸውን የተቀጣሪነት ገቢ ግብር የከፈሉ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት አሰራር አለመኖሩና በዚህም ምክንያት በአዋጁ መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባው ግብር ሳይሰበሰብ ሊቀር እንደሚችል ታውቋል፡፡

መንግሥት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ ያደርጋል፡፡

ድርጅቱ ማንኛውም በኮንትራት ቀጥሮ የሚያሰራቸው ሠራተኞች ከሌላ ቦታ የሚያገኙትን ገቢ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሊከፍሉት የሚገባውን የሥራ ግብር በመቀነስ ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ገቢ ማድረግ ያለበት ሲሆን፣ የኮንትራት ሰራተኞችን መረጃ በማሰባሰብ ያልከፈሉት ግብር ታስቦ እንዲከፍሉ መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የማሻሻያ ሀሳቡን ተቀብሎታል፡፡

2.3 <u>በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ</u>

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ መሠረት ማናቸውም ከገንዘብ ሰብሳቢ ወይም ከማናቸውም ሌላ ሰው የመንግሥት ገንዘብ የሚሰበስብ ወይም የሚቀበል ሰው በየቀኑ የሰበሰበውን ገንዘብ ወደ ባንክ ገቢ ማድረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ባንክ ገቢ ሳይሆን ከ7 ቀን በላይ የሚቆይ ሂሣብ እንዳለ ታውቋል፡፡

የሚሰበሰበው ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ገቢ ካልሆነ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት እንዲጋለጥ ይገፋፋል፡፡

በገንዘብ ያዥ እጅ ገንዘብ ከተጠራቀመ ላልተፈለገ ብክነት የሚገፋፋ በመሆኑ የተሰበሰበ የመንግሥት ገንዘብ በደንቡ መሠረት በየቀኑ ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በዕለቱ ለማስገባት ያልተቻለበት ምክንያት የድርጅቱ የሥራ ሰዓት እስከ 11:30 በመሆኑ ባንክ የሚዘጋው በ10:00 ሰዓት በመሆኑና በማግስቱ ለማስገባት ደንበኞች በጠዋት ሲመጡ እነሱን ለማስተናገድ ሲባል የተሰበሰበው ገንዘብ ባንክ ሳይገባ የሚዘገይ መሆኑ የተገለጸ ቢሆንም የተሰጠው ምላሽ ህጉን ተከትሎ ላለመስራት የሚያግድ ባለመሆኑ አሰራሩ በደንቡ መሰረት መታረም ይኖርበታል በማለት አሳስበናል፡፡

## 2.4 ወደ ሂሳብ ሪፖርት ያልተላለፈ ሂሳብ

በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በመሀል ከተማ ቢሮ በኩል በየወሩ ተጠናቅሮ የሚቀርበው የክልሎች፣ የአዲስ አበባና አካባቢው የቴሌቪዥን ፈቃድ ክፍያ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛነቱ እየተረጋገጠ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት በሚያቀርበው ወርሀዊ የሂሳብ ሪፖርት ውስጥ እንዲካተት የማይደረግ መሆኑ እንዲሁም የድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የማያሳውቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

የዘመኑን የመንግስት ገቢ እቅድ አፈጻጸም እና የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል በተጨማሪም የመ/ቤቱን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችለል፡፡

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገው መሠረት የውስጥ ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፐፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስናል፡፡

በቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ የሚደረጉት የቴሌቪዥን አገልግሎት ክፍያ ገቢ በስልክ ሪፖርት ቢደረግም፣ ለሥራ አመራሩም ሆነ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ሪፖርት የሚቀርበው ወደ ድርጅቱ የሂሣብ ቁጥር ገቢ የተደረገው ብቻ በመሆኑ የተሰጠው አስተያየት ተገቢነቱ አልታየንም በማለት መልስ የሰጡ ቢሆንም የሪፖርት ልውውጡ በመረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ የድርጅቱን ትክክለኛ የፋይናንስ አፈፃፀም የማያሳይ ነው፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶች የማያቀርቡት ሪፖርት በመረጃ የተደገፈ ሆኖ ባንክ ከሚገባው ሂሣብ ጋር ሊታረቅና ትክክለኛውን የድርጅቱን ሁኔታ ሊያሳይ በሚችል መልኩ የሂሳብ ሪፖርቶች መዘጋጀት እንደሚኖርባቸው አሳስበናል፡፡

የድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ የውስጥ ገቢውን በየጊዜው ለገ/ኢ/ል/ሚኒስቴር ሪፖርት ባይቀርብም ዓመታዊ የገቢ ዕቅድ በትምህርት ሚ/ር በኩል ስናሳውቅ ነበር፡፡ አጠቃቀሙን በተመለከተ ደግሞ በየሩብ ዓመት ለቦርዱ ሪፖርት ሲያደርግ የነበረ መሆኑን፤ ለወደፊቱም በተሰጠው አስተያየት መሰረት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የሚደርግ መሆኑን በላከው ምላሽ ገልጿል፡፡

## 2.5 <u>የውስጥ ገቢ ከወጪ ቀሪ ፈሰስ ያለመደረጉ</u>

ማናቸውንም የመንግሥት ገንዘብ እንዲቀበል ወይም እንዲሰበስብ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የተቀበለውን ወይም የሰበሰበውን የመንግሥት ገንዘብ ወደተጠቃለለው ፈንድ ገቢ ማድረግ እንዳለበት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገው መሰረት ከውስጥ ገቢ ስራ ላይ እንዲውል ከተፈቀደው በላይ የሰበሰበውን ገንዘብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ገቢ ማድረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የወለጋ ዩኒቨርስቲ ከተቋቋመበት ከ1999 በጀት አመት ጀምሮ የሰበሰበውን ገቢ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ እንዳላደረገ ታውቋል፡፡

ዩኒቨርስቲው ከተፈቀደለት በጀት በላይ የውስጥ ገቢውን ስራ ላይ ሊያውል ይችላል ይህም የፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ እንዲጣስ ያደርጋል፡፡

የውስጥ ገቢ የፋይናንስ አዋጁ በሚያዘው መሰረት አስፈቅዶ መጠቀም የሚቻል ሲሆን፣ ከዚህ ውጪ በብልጫ የተሰበሰበውን ደግሞ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ እንደሚኖርበት በላክነው ስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

# 3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

## 3.1 <u>ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበቂ ማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

| | | |
|---|---|---|
| የደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት | ብር | 2,152.45 |
| የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር | ” | 36,224.50 |
| የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን | ” | 629,000.00 |
| የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ | ” | <u>457,777.20</u> |
| በድምሩ | ” | <u>1,125,153.95</u> |

በባንክ በኩል የተላከና ለባለጥቅሞቹ ለመድረሱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

በባንክ የተላከው ገንዘብ ለተጠቃሚዎቹ ላይደርስ ይችላል፡፡ ይህም የመንግስትን ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ይችላል፡፡

ክፍያዎች በባንክ በኩል ሲፈፀሙ ገንዘቡ ለባለጥቅሙ መድረሱ ሳይረጋገጥ እና ባለጥቅሙም ገንዘቡ የደረሰው ስለመሆኑ በደብዳቤም ሆነ በደረሰኝ

ማረጋገጫ ሳይሰጥ ሂሳቡ በወጪ መመዝገብ እንደሌለበትና አሰራሩም ሊታረም እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የሁሉም የስራ አመራሮች የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብለውታል፡፡

3.2 <u>አላግባብ የተመዘገበ ወጪ</u>

ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተጠይቆ የመጣ የደመወዝ ሂሳብ በድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ ለባለጥቅሙ መከፈሉ ሳይረጋገጥ በወጪ በመመዝገቡ ምክንያት ብር 251,189.81 በብልጫ የተመዘገበና የማስተካከያ ምዝገባ ያልተሰራለት መሆኑ ታውቋል፡፡

በወጪ የተመዘገበው የደመወዝ ሂሳብ ትክክለኛውን ክፍያ አያሳይም ፡፡ይህም ያልተከፈለ ደመወዝ በወጪ ሊያዝና ተመላሽ ሳይደረግ ሊታለፍ ይችላል፡፡በዚህ ምክንያት የመንግስት ገንዘብ እንዲባክን መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

ለሂሳቡ ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡ ለወደፊቱም የሂሳብ ምዝገባ መከናወን ያለበት የክፍያ ማስረጃ ከቀረበ በኋላ መሆን እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብሎታል፡፡

3.3 <u>ያላአግባብ የተፈፀመ ክፍያ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ እንዲሁም ክፍያው መ/ቤቱ ላገኘው አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ:

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | በአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲ | 208,174.66 |
| 2 | በደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጄክት | 7,123.00 |
| 3 | በድሬድዋ ዩኒቨርስቲ | 234,482.00 |
| 4 | በወለጋ ዩኒቨርሲቲ | 96,223.32 |
| 5 | በመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ | 25,156.11 |
| 6 | በድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ | 11,070.00 |
| | በድምሩ | 582,229.09 |

በድምሩ ብር 582229.09 ያላአግባብ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ ያላግባብ የተፈፀመው ክፍያ በዝርዝር ሲታይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ከመመሪያ ውጪ የተፈፀመ የትርፍ ሰዓት ክፍያ፣የደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጄክት በስራ ገበታቸው ላይ ላልተገኙ ሁለት ሰራተኞች የተከፈለ ደመወዝ፣የድሬድዋ ዩኒቨርስቲ ሥራው ለማይመለከታቸው ሰራተኞች የተከፈለ የኃላፊነት አበልና ወደ ውጭ ሀገር ለሄዱ 13 መምህራን የግማሽ ወር ደመወዝ መከፈል ሲገባው የሙሉ ወር ደመወዝ የተከፈለ፣የወለጋ ዩኒቨርሲቲም በተመሳሳይ መልኩየግማሽ ወር ደመወዝ መከፈል ሲገባው የሙሉ ወር ደመወዝ በመከፈሉ፣ የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ለተማሪዎች የምረቃ በዓል የእንግዶችና የወላጅ የጥሪ ካርድ ህትመት ማሰሪያ ወጪ ሲደረግ አላግባብ በብልጫ የተከፈለ እንዲሁም የቤተመንግስት አስተዳደር ለአስተዳደሩ ሰራተኞች (የመስተንግዶ ክፍል ሰራተኞች፣ ሾፌሮች እንዲሁም ሌሎች ሠራተኞች) በትርፍ ሰዓት ለሰሩበት ተብሎ የትርፍ ሰዓት ክፍያ በምሳ አበል እየታሰበ የሚከፈል መሆኑ ታውቋል፡፡

አሰራሩ ለመንግስት ገንዘብ መባከን ክፍተት ይፈጥራል በተጨማሪም ስራዎች በመደበኛ የስራ ሰዓት እንዳይሰሩ የሚገፋፉ እና መ/ቤቶቹን ለተጨማሪ ወጪ የሚዳርግ ነው፡፡

ከመመሪያ ውጭ የተፈፀመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ የሥራ ባህሪያቸው የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሚያስፈልገው መሆኑ ከታመነበት ጉዳዩ ለሚመለከተው መ/ቤት ቀርቦ መፈቀድ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ የሁሉም መ/ቤቶች የሥራ አመራሮች ተቀብለውታል፡፡

## 3.4 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት

በበጀት ዓመቱ የተገዙ እቃዎች ለመ/ቤቱ ገቢ የተደረጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በሃገር መከላከያ ሚኒስቴር የኮንስትራክሽን ኢንጅነሪንግ ለሚያሰራው የማሰራጫ ጣቢያ ግንባታ ሲሚንቶ የተገዛበት ብር 68,750.00፣እንዲሁም በአጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲ SQL Server Visual Studio Net ከዋስትና ትሬዲንግ በብር 86,984.35፤ በቤተመንግስት አስተዳደር ብር 220879.37 ለአካል ብቃት ማሳደጊያ መሳሪያ ተገዝቶ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ሳይረጋገጥ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ንብረቱ ገቢ ላይሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ድርጅቱ ላልተረከበው ንብረት ክፍያ ሊፈፀም ይችላል፡፡

ለወደፊቱ ሂሳቡ በወጪ ከመመዝገቡ በፊት ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ መረጋገጥ እንደሚኖርበት አሳስበናል ፡፡

የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የመከላከያ ባለሙያዎች ንብረቱን በሥራ ላይ ስላዋሉት ወጪ እንዲያደርጉላቸው በመነጋገር ላይ መሆናቸውን የገለፁ ሲሆን ዕቃው ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉ ሳይረጋገጥ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ አግባብነት ስለሌለው ሞ/19 ሊቆረጥለት እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡አጠቃላይ የትምህርት ጥራት ማረጋገጫና የፈተናዎች ኤጀንሲና የቤተመንግስት አስተዳደር የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብለወታል፡፡

## 3.5 የሂሳብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ ሂሳብ

የተመዘገቡት የበጀት ዓመቱ ወጪዎች በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት የሂሳብ መደቡን ጠብቆ መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

| | | |
|---|---|---|
| በደብረማርቆስ | ብር | 737,906.93 |
| በቤተመንግስት አስዳደር | ” | 939,003.16 |
| በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ | ” | 23,670,128.94 |
| በድምሩ | ” | 25,347,039.03 |

የሂሣብ መደቡን ሳይጠብቅ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
የመ/ቤቱን ትክክለኛ የበጀት አፈጻጸም ለመለካት አያስችልም፡፡ በተጨማሪም የመንግስት አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ያደርጋል፡፡

የበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ትክክለኛ የሂሣብ መደቡን ጠብቆ መመዝገብ ያለበት ሲሆን ሂሣቡም በትክክል ስለመመዝገቡ የሚረጋገጥበት ሥርዓትም መዘርጋት አለበት፡፡ በመሆኑም ከላይ የተመለከቱት የምዝገባ ስህተቶች የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ የተስተካከለ የሂሳብ ሪፖርት ሊዘጋጅ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በኢንፎርሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ህንፃዎች ሲስተም እና ለመሰረተ ልማት አውታሮች ግንባታ የሚያስፈልገውን በጀት በወጪ መደብ 6323 እና 6324 በተጨማሪ በጀት የተፈቀደ ሲሆን፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በወጪ መደብ በ6244 ደልድሎ በመላኩ የተፈጠረ ስህተት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ የስራ አመራር የተሰጠውን አስተያየት ተቀብሎታል፡፡

## 3.6 ያልተቀነሰ የተከፋይና የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳብ

መ/ቤቱ በበጀት አመቱ ውስጥ ለፈጸመው ግዥ ክፍያ በሚፈጽምበት ወቅት የተከፋይ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈስስ ማድረጉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የቀድሞ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ለምህንድስና የብቃት ማዕከል ወርክሾፕ ማጠናቀሪያ የሚያገለግል 1500 ኩንታል ሲሚንቶ ሲገዛ ከኘጩ ድርጅት ቀንሶ ማስቀረት የነበረበት ተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 61,875.00 ያለመቀነሱ እና ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ (withholding) ታክስ ደግሞ ብር 8,250.00 በድምሩ ብር 70,125 ከኘጩ ድርጅት ያለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ያልተሰበሰበው ሂሳብ ከድርጅቱ ተሰባስቦ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ መደረግ እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

መንግስት የሲሚንቶ እጥረት ለማስወገድ ባደረገው እገዛ ከውጭ ካስመጣው ሲሚንቶ ቅድሚያ የተሰጠን በመሆኑ ሳይሰበሰብ ቀርቷል ተብሎ የተገለጸ ቢሆንም፣ ቅድሚያ ማግኘት ህግን ላለማክበር በቂ ምክንያት ባለመሆኑ ያልተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 3.7 በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ተከፍሎ የተገኘ የከባድ ሥራ (Hardship allowance) አበል፣

በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ መ/ቤቶች የፋይናንስና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ በሚያወጡት መመሪያ፣ መሠረት እንደሚተዳደሩ ይታወቃል። ይሁን እንጂ የባለአደራ ቦርድ በአዋጅ ከተሰጠው ሥልጣን ውጪ የከባድ ሥራ አበል /Hardship allowance / ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ሥራው ለሚመለከታቸው ሠራተኞች ሲከፈል የቆየና በ2002 በጀት ዓመት ብር 56,428.00 የከባድ ስራ አበል ከፍሎ ተገኝቷል።

የከባድ ሥራ አበል በሚል ለሠራተኞች የሚከፈለው ሂሣብ በሚመለከተው የበላይ አካል ያልተፈቀደ በመሆኑ የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

የመ/ቤቱ የሥራ ባህሪ የከባድ ሥራ አበል የሚያስፈልገው መሆኑ ከታመነበት ለሚመለከተው መ/ቤት ጉዳዩን በማቅረብ አስፈቅዶ ክፍያውን መፈፀም ሲገባ በመ/ቤቱ የሥራ አመራር ውሳኔ ክፍያውን መፈፀም አግባብነት የሌለው በመሆኑ አሰሩሩ መታረም እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የመ/ቤቱ የሥራ ባህሪይ በመደበኛነት ከሚሠራው ሥራ ለየት ያለ በተለይም የሠነድና የሂሳብ ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች የሚረከቧቸውና ለሥራ የሚጠቀሙባቸው ሰነዶች ከ20 ዓመታት በላይ በመቆየታቸው ለከፍተኛ ሽታና የጤና ጠንቅ በመሆናቸው ለዚህ ችግር መፍትሔ ሆኖ በወቅቱ የቀረበው የሣሙናና የወተት ማካካሻ በገንዘብ ተተምኖ ሠራተኞቹ በሠሩባቸው ቀናቶች ለሂሣብ ሠራተኞች በቀን ብር 12.00 ለሰነድ ሠራተኞች በቀን ብር 10.00 በማስወሰን መከፈሉንና ለወደፊቱም የችግሩን አሳሳቢነት ከሚመለከተው አካላት (መ/ቤት) ጋር ተነጋግረው በችግሩ ዙሪያ መፍትሔ ለማምጣት ጥረት እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

3.8 <u>ጨረታ ሣይወጣ የተፈፀመ ግዥ</u>

በግዥ አዋጅ መሰረት በጨረታ ሊገዛ የሚገባው እቃ በጨረታ መገዛቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

| | | |
|---|---|---|
| በደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ | | |
| ፕሮጀክት ጽ/ቤት | ብር | 87,505.80 |
| በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት | ” | 144,358.93 |
| በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት | ” | 378,400.00 |
| በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር | ” | 111,999.00 |
| በተወካዮች ምክር ቤት | ” | 994,928.58 |
| በድምሩ | ” | 1,717,192.31 |

የጨረታ ማስታወቂያ ሳይወጣ ግዥ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

የደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ለተለያዩ የጽህፈት መሣሪያዎች ግዥ፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለጥገና፣የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ለሬድዮ ማስፋፊያና ማሻሻያ ስራ፣ የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር ስምንት ኮምፒውተሮች በመቆራረጥ ግዥ የተፈጸመ፤ በተወካዮች ምክር ቤት ለአጥር ግንባታ ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

መንግስት በዋጋ ውድድር ሊያገኝ የሚችለውን ቅናሽ እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

ግዥ አዋጅ መሰረት በውድድር መፈጸም እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የመንግሥት ግዥ አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 53/አንቀጽ 1 በጣም አስቸኳይ በመሆኑ ግዥው በቀጥታ ተገዝቶ ወደ ሥራ እንዲገባ በበላይ ኃላፊ በመወሰኑ የተፈጸመ እንደሆነ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት የስራ አመራ የተገለጸ ቢሆንም፣ ለወደፊቱ በአዋጁ መሰረት የግዥ ስርአቱን ተከትሎ ግዥ በእቅድ የሚከናወንበትን አሰራር መዘርጋት እንዳለበት፤ እንዲሁም በተወካዮች ምክር ቤት የአዲስ አበባ መንገዶች ባለስልጣን መንገድ ለማስፋት በፓርላማ ዋና በር በኩል ያለውን አጥር ሙሉ በሙሉ አፈርሶ እንደገና በራሱ ወጪ ከሰራ በኋላ ቀሪው አጥርም በማርጀቱ ምክንያት ለመፍረስ ተቃርቦ ስለነበርና ቀደም ብሎ የነበሩትን የአጥር ድንጋዮች በጥንቃቄ ፈልፍሎ በማውጣት አጥሩን ታሪካዊነቱን በጠበቀ መልኩ ወደነበረበት

ለመመለስ በመታሰቡ፣ ባለስልጣኑ አስቀድሞ ያፈረሰውን አጥር መልሶ በሰራበት ወቅት በሰራው ዲዛይን ወጥ ሆኖ ሌላውም አጥር መሰራት እንዳለበት በመወሰኑ፣ እንዲሁም ባለስልጣን መ/ቤቱ የመንግስት በመሆኑ በሀላፊነት መንፈስ በተሻለ ሁኔታ በአነስተኛ ዋጋ ሊሰራልን ይችላል በሚል አስተሳሰብ ባለስልጣኑ እንዲሰራው ተወሰኖ ግንባታው ያለጨረታ መሰጠቱ ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ ግንባታውን ለማከናወን የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች በማዘጋጀት ግንባታው በግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 መሰረት የጨረታ ውደድር በማድረግ ምክር ቤቱ በሚፈልገው መስፈርት መሰረት ውል በፈራረም ግንባታው መከናወን እንደነበረበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡የሌሎች ቀሪ መ/ቤቶች የስራአመራሮች የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብለውታል፡፡

## 3.9 የግዢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑ

የመንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ዓ.ም አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት ዓመታዊ የግዥ ዕቅድ ተዘጋጅቶ ግዥውም በዕቅዱ መሰረት የሚከናወን መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ፤ የድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ፤የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት፤የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ እና የቤተመንግስት አስተዳደር የግዢ እቅድ ያላዘጋጁ መሆኑ ታውቋል፡፡

ግዢ በዕቅድ መሠረት እንዲፈፀም ባለመደረጉ ግዥው ኢኮኖሚያዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዳይፈፀም ያደርጋል፡፡

መ/ቤቶቹ የግዥ ዕቅድ በአዋጁ መሰረት በማዘጋጀት በዚሁ መሰረት ግዥ መፈፀም እንዳለባቸውና ዓመታዊ የግዥ ዕቅዱም በአዋጁ ላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለግዥ ኤጀንሲ መላክ እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

የስራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብሎታል፡፡

## 3.10 በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከፍተኛ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ

በመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች የግዥ ግዥ በተቻለ መጠን እስከ ሚያዝያ 30/2002 ድረስ እንዲጠናቀቅ ይገልጻል፡፡ ሆኖም በኢትዮጵያ ካርታ ስራ ድርጅት በግንቦት እና በሰኔ 2002 ዓ.ም የብር 5,619,371.21 ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

በበጀት ዓመት መጨረሻ በጥድፊያ የሚፈፀም ግዥ ለመንግስት ገንዘብ መባከን መንስኤ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በእቅድ መሰረት አለመሰራቱ በጀቱ ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል ያደርጋል፡፡

መ/ቤቱ ማንኛውም ግዥዎች /አገልግሎቶች/ ባዘጋጀው እቅድ መሠረት ወቅቱን የጠበቀ ግዥ እንዲፈፀም ቁጥጥርና ክትትል ሊያደርግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብሎታል፡፡

# 4. የተሰብሳቢ ሂሳብ

## 4.1 ውዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳብ

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የሰነድ ሂሳብ በወቅቱ የሚወራረድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

| ተራ ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ | |
|---|---|---|---|
| | | ብር | ሣ |
| 1 | በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት | 2,597,111 | 00 |
| 2 | በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት | 7,090,342 | 53 |
| 3 | በአቅም ግንባታ ሚኒስቴር | 3,111,961 | 51 |
| 4 | በማዕከላዊ ስታስቲክስ | 12,165,505 | 97 |
| 5 | በተወካዮች ምክር ቤት | 293,863 | 81 |
| 6 | በኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ | 737,150 | 10 |
| 7 | በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር | 163,642 | 15 |
| 8 | በኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን | 88,203 | 92 |
| 9 | በደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ | 2,482,145 | 92 |
| | ድምር | 28,729,926 | 91 |

ውዝፍ የተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፣ የመንግስት ገንዘብም ያለአግባብ ለብክነትና ለሙስና ይጋለጣል፡፡

ያልተወራረደው ሂሳብ አስፈላጊው ክትትል ተደርጎ መወራረድ ያለበት ሲሆን፣ ሊወራረድ የማይችለው ደግሞ ተጣርቶ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ መሰረት ከመዝገብ ላይ የሚሰረዝበት ሁኔታ መመቻቸት እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የስራ አመራር የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የተቀበለው ሲሆን፣ ሊሰበሰብ የማይችሉ ተለይተው የሚሰረዝበት መንገድ እየተመቻቸ መሆኑን እንዲሁም ሊሰበሰብ የሚችሉትን ደግሞ ለመሰብሰብ ጥረት እየተደረገ መሆኑን እና ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆኑትን በሕግ ክትትል እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል፡፡

የማዕከላዊ ስታስቲክስ ሂሳቡ የሚወራረድበትን መፍትሄ ለመፈለግ ከኤጀንሲው እና ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተውጣጣ ኮሚቴ ተቋቁሞ ባደረገው ጥረት የብር 659,314.92 ሰነድ የሚወራረድበት መንገድ በመመቻቸት ላይ መሆኑ፣

በ1994 በጀት አመት መጨረሻ ከCash Basis ወደ Modified Cash basis ሽግግር ሲደረግ ወደ 1995 የበጀት ዓመት የዞረውን ትክክለኛ ያልሆነ ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ብር 6,506,109.38 በተመለተ በውስጥ ኦዲት በኩል ስለሂሳቡ ሁኔታ ያደረገውን ማጣራት መሰረት በማረግ ቀጣይ የማጣራት ስራዎች እንደሚሰሩና ከአቅም በላይ የሆነ አሳማኝ ምክንያት ካላገጠመ በስተቀር እጅግ ቢዘገይ የ2003 በጀት አመት ሲዘጋ የመጨረሻ እልባት የሚሰጥ መሆኑተገልጿል፡፡አሁንም ቢሆን ያተወራረደው ሰነድ የመጨረሻ እልባት እስከሚያገኝ ድረስ በመደረግ ላይ ያለው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል እና ችግሩ የመጨረሻ መፍትሄ ሊያገኝ ይገባል በማለት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡ሌሎች መስሪያ ቤቶች የተሰጠውን የስራ አመራር አስተያየት ተቀብለውታል፡፡

4.2 ማስረጃ ሌለው የተሰብሳቢ ሂሳብ

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የመ/ቤቱ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ብር 1,276,610.09 ማስረጃ ሌለው የተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት ማስረጃዎቹ ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የተመለከተው የተሰብሳቢ ሂሳብ በማስረጃ ያልተደገፈ እና ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡

በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከቱት የሂሳብ ሚዛኖች በማስረጃ የተደገፉ ሊሆን እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በሂሳብ መደብ 4209 እና 4211 ማስተካከያ መደረጉንና በቀጣይም በሁሉም የሂሳብ መደቦች ላይ የሰፈሩትን በማጣራት አፈጻጸሙ የሚቀጥል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

### 4.3 <u>ከደንበኞች የሚፈለገው ውዝፍ ሂሳብ የማይታወቅ ስለመሆኑ</u>

ከቴሌቪዥን ፈቃድ ከደንበኞች የሚፈለገውን ውዝፍ ሂሣብ በአግባቡ ተመዝግቦ የተያዘና ሂሳቡም በወቅቱ እንዲሰበሰብ ወቅታዊ ክትትል የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት የደንበኞችን ውዝፍ ሂሣብ ለማወቅ እንዲያስችል የአሰራር ሥርዓት የተዘረጋ ቢሆንም የደንበኞች ዝርዝር በተሟላ መልኩ ተመዝግበው ባለመገኘታቸው ያልተሰበሰበውን ውዝፍ ሂሣብ ለማወቅ አልተቻለም፡፡

በዚህ ምክንያት ሊሰበሰብ የሚገባው ሂሣብ አይታወቅም ፡፡ ይህም የመንግስት ገንዘብ ሳይሰበሰብ የሚቀርበትን አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡

ወቅታዊ ክትትል ለማድረግ እንዲያስችል የክትትል ሥርዓት በመዘርጋት መዝግቦ ከያዛቸው ደንቦች ያልተሰበሰበው ሂሣብ በሪፖርት እንዲቀርብ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በሰው ኃይል ችግር ምክንያት ስራው አለመሰራቱ የተገለጸ ቢሆንም ከችግሩ አሳሳቢነት አንጻር አፋጣኝ የመፍትሄ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

## 5. <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

### 5.1 <u>ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ</u>

የተሰበሰበው የመንግሥት ገቢ በገቢ ግብር አዋጅ መሠረት በወቅቱ ለሚመለከተው ግብር አስገቢ መ/ቤት መተላለፉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ  የደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት ፅ/ቤት የሰበሰበው ከቅድመ ታክስ ክፍያ /Withholding Tax/ ብር 1,135.03 ከተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ብር 8,207.40 በድምሩ ብር 9,342.43 በወቅቱ ለገቢዎችና ግምሩክ ባለሥልጣን ፈሰስ ያልተደረገ ሲሆን ብር 211.36 ደግሞ ከቋሚ

ሠራተኞች የተቀነሰ የጡረታ መዋጮ ለማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ ያለመከፈሉ እንዲሁም ለጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ /ማስያዣ/ ለብር 3000 ከባንክ የተጻፈ ደብዳቤ ጊዜው ያለፈበት በመሆኑ ለፕሮጀክቱ ጽ/ቤት ገቢ ያልተደረገ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

ተከፋይ ሂሣብ በወቅቱ ፈሰስ ካልተደረገ መንግሥት ልዩ ልዩ ወጪዎችን ለመሸፈን በልዩ ልዩ በተከፋይ ሂሣቦች የተያዙት በወቅቱ ካልተከፈሉ ጊዜ እየረዘመ በሄደ ቁጥር የዕዳ ክምችት ያስከትላሉ፡፡

በአዋጅ ቁጥር 286/94 መሠረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱ ለሚመለከተው መ/ቤት ገቢ የሚደረግበት ሁኔታ መመቻቸት ያለበት ሲሆን በተጨማሪም በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሣቦች የተያዙት ረጅም ጊዜ ሳይወስዱና ሳይከማቹ በወቅቱ በሚመለከተው ድርጅት ክፍያ መፈፀም እንዳለበት፣በሌላም በኩል በተከፋይ ሂሳብነት የተመለከተው ብር 3000 ሊሰበሰብ የሚገባው እንጂ የሚከፈል ባለመሆኑ ጉዳዩ መጣራት እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብሎታል፡፡ በዚህም መሠረት አስፈላጊው እርምጃ እንደሚወሰድ ተገልጿል፡፡

5.2 ማስረጃ የሌለው የተከፋይ ሂሳብ

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የመ/ቤቱ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተከፋይ ሂሳብ በድምሩ ብር 942,887.51 የተገኘ ሲሆን የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማጣራት ማስረጃዎቹ ለኦዲት እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ የተመለከተው የተከፋይ ሂሳብ በማስረጃ ያልተደገፈ እና ትክክል ላይሆን ይችላል፡

በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከቱት የሂሳብ ሚዛኖች በማስረጃ የተደገፉ ሊሆን እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

በሂሳብ መግለጫ ላይ በሂሳብ መደብ 5009፣ 5028 እና 5059 የሚታየው ሚዛን እንደተጣራ እና በሌሎች ሂሳብ መደብ የሚታየውን ግን በቀጣይ እንደሚጣሩ ገልጸዋል፡፡

## 6. የበጀት ሂሳብ

### 6.1 በስራ ላይ ላይ ያልዋለ በጀት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በአግባቡ የተጠቀሙበት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

| | | |
|---|---|---|
| የደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊ ፕሮጀክት ጽ/ቤት | ብር | 12,339,589.35 |
| የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር | ” | 15,836,018.88 |
| የብሔራዊ ቤተመፃህፍትና ቤተመዛግብት ኤጀንሲ | ” | 2,688,864.75 |
| የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን | ” | 4,706,015.00 |
| የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን | ” | 2,398,452.00 |
| የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር | ” | 462,182.00 |
| በድምሩ | ” | 38,431,122.00 |

ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡

መ/ቤቶች ጥቅም ላይ ከሚያውሉት በጀት በላይ በስማቸው የሚያዝ ከሆነ መንግሥት ለሌሎች ፕሮግራሞችና አስፈጻሚ መ/ቤቶች በሚይዘው በጀት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡

መ/ቤቶች መጠየቅ ያለባቸው ሥራ ላይ ሊያውሉት የሚችሉትን በጀት ብቻ መሆን እንዳለበት ለመ/ቤቶቹ በተላከው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጀክት የስራ አመራር በሰጡት ምላሽ ጽ/ቤቱ ባካሄደው አዲስ አደረጃጀት /BPR/ መሰረት የሠራተኛ ቅጥር ያከናወናል በሚል ሀሳብ በጀቱ የተፈቀደ ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት ቅጥሩ ባለመከናወኑ እና በቃሊቲ ኢንሴክተር ማዕከል የተለያዩ ግንባታዎች ይሠራሉ ተብሎ ሳይሠራ በመቅረቱ በጀቱ ሥራ ላይ ሳይውል መቅረቱ፣ እንዲሁም የአቅም ግንባታ ሚኒስቴር የስራ አመራር በ6100 አርዕስት ለተጠቀሰው ያልተሠራበት በጀት ከጀርመን አገር ባለሙያ ለመቅጠር ተመድቦ የነበረ ሲሆን ባለሙያዎችን ለማግኘትና ለመቅጠር ጊዜ በመውሰዱ መሆኑንና በ6200 አርዕስት የተመለከተውም ከላይ በተገለፀው ሁኔታ በተመሣሣይ የውጭ ባለሙያዎችን ለመቅጠር ተያያዥ ሥራዎችን ለመሥራት ጊዜ በመውሰዱና የተለያዩ የቢሮ መገልገያ መሣሪያዎችን ለመግዛት ጨረታ ከወጣ በኋላ

በምህንድስና አቅም ግንባታ ፕሮግራም የተዘጋጀ የእቃ ዝርዝር መግለጫ(Specification) ችግር ስለነበረበት ጨረታው በመሠረዙ ሥራ ላይ ሣይውል መገኘቱን፣የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን የስራ አመራር ለአዲሱ የቅርስ ኮንሰርቬሽን ላቦራቶሪ ህንፃ ስልክና ኢንተርኔት ኔትወርክ ዝርጋታ የተፈቀደ ሲሆን ዝርጋታውን ለማከናወን ሁለት ጊዜ ጨረታ ወጥቶ የጨረታው አሸናፊ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በመታወቁ ሌሎች ቅድመ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት ሲባል ክፍያው ሳይፈፀም ገንዘቡ ተመላሽ ተደርጎ በ2003 በጀት ዓመት መጀመሪያ ላይ ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር እንደገና በማምጣት የዝርጋታ ሥራውን ላሸነፈው ድርጅት የቅድሚያ ክፍያ መከፈሉን ተገልጿል፡፡ስለሆነም ለወደፊቱ የበጀት ጥያቄ ሲቀርብ ሊተገበር የሚችል መሆኑ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት እንደሚኖርበት በላክነው ስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡ የሌሎቹ መ/ቤቶች የስራ አመራሮች የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብለውታል፡

6.2 ከበጀት በላይ የወጣ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጀት ካላፀደቀ በስተቀር ከተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ክፍያ መፈጸም እንደማይቻል በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 ተደንግጓል፡፡

የወለጋ ዩኒቨርሲቲ የተመደበለትን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ እና በበጀት ድልድል መሰረት ሥራ ላይ ማዋሉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ስራ ላይ እንዲያውል ከተፈቀደለት በጀት በላይ ከዉስጥ ገቢ ብር 1,814,721.65 ተጠቅሞ ተገኝቷል፡፡

በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

ዩኒቨርስቲው ሀላፊነቱን ለመወጣት የሚያስፈልገውን የበጀት መጠን አስቀድሞ በማቀድ የሚያስፈልገውን በጀት ማስፈቀድ የሚችል ሲሆን፣ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ያልፀደቀ በጀት መጠቀም ፈጽሞ የማይፈቀድ በመሆኑ ዩኒቨርስቲው የፋይናንስ አዋጁን ተከትሎ በመስራት ረገድ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ከተመደበው በጀት በላይ ከውስጥ ገቢ የተጠቀምነው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ችግር እንዳይፈጠር በሚል በወቅቱ የተወሰደ እርምጃ መሆኑንና ተጨማሪ በጀት እንዲፈቀድልን ትምህርት ሚኒስቴርን በጠየቅነው መሰረት ተጨማሪ በጀት እንዲፈቀድልን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒቴር ደብዳቤ መጻፉንና ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴርም በተደጋጋሚ ቢጠየቅ ምላሽ ባለመስጠቱ የተከሰተ ችግር መሆኑ ተገልጿል፡፡ ይሁን እንጂ ለማመር ማስተማር ሂደቱ የሚያስፈልግ በጀት አስቀድሞ መታቀድ ያለበት በመሆኑ፣ በበጀት ዝግጅቱ ወቅት ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.3 <u>በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር</u>

<u>ሳይፈቀድ የተፈጸመ የበጀት ዝውውር</u>

የበጀት አያያዝ አጠቃቀምና አመዘጋገብ በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀፅ 17(2) የበጀት ዝውውር ጥያቄ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እያቀረበ ሲፈቀድለት ሥራ ላይ የሚያውል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቱር በፋይናንስ ደንቡ መሰረት የበጀት ዝውውር ሳይፈቀድለት ለሌሎች ድርጅቶች የሚደረግ ድጋፍ (6412) ከተደለደለው በጀት ላይ ብር 1,345,000.00 ሳይፈቀድ ለሌሎች አገልግሎቶች (6200) በማዛወር በጀቱ ሥራ ላይ ውሎ ተገኝቷል፡፡

አሠራሩ የፋይናንስ ደንብን ያልተከተለ ይሆናል፡፡

መ/ቤቱ በተደለደለለት በጀት መሠረት ክፍያ መፈፀም ያለበት ሲሆን፤ የተደለደለው በጀት በቂ በማይሆን ጊዜ በፋይናንስ አዋጅ መሠረት ዝውውር አስፈቅዶ ክፍያ መፈፀም እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሣቡን ተቀብሎታል፡፡

7. <u>ንብረት</u>

7.1 <u>የንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ</u>

የንብረት አጠባበቅና አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ፣ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር፤ በድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ የቋሚ ዕቃ ቆጠራ በበጀት በዓመቱ መጨረሻ አለመደረጉ

ታውቋል፡፡በተጨማሪም የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ የንብረት መዝገብ ያላቋቋመ መሆኑ ታውቋል፡፡

የንብረት ጉድለት ቢከሰት በወቅቱ አይታወቅም፡፡

በየአመቱ እየተቆጠረ ከንብረት መዝገብ ጋር መገናዘብ እንደሚኖርበት እና የድሬድዋ ዮኒቨርሲቲም የንብረት መዝገብ ማቋቋም እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ አስተያየት የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብሎታል፡፡

7.2 <u>ለቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ</u>

የመ/ቤቱ ቋሚ ዕቃዎች የመለያ ቁጥር የተሰጣቸው መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፤በደቡብ ስምጥ ሸለቆ የቆላ ዝንብ ማጥፊያ ፕሮጄክት ጽ/ቤት፤ ለቋሚ ዕቃዎች ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለቁጥጥርና ክትትል አመቺ ካለመሆኑም በላይ ንብረቶቹ ለብክነት ሊዳረጉ ይችላሉ፡፡ መ/ቤቱ በንብረት አያያዝ መመሪያ መሠረት የመለያ ቁጥር መሰጠት እንደሚኖርበት በተላከው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብሎታል፡፡

7.3 <u>በንብረት መዝገብ ያልተመዘገበ ንብረት መገኘቱ</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዙት ዕቃዎች በሙሉ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጋቸውንና በንብረት መዝገብም ላይ በትክክል መመዝገባቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በፌደሬሽን ምክር ቤት ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረጉ 445 CDዎች ሆነው በንብረት መዝገብ ላይ የተመዘገቡት ግን 328 CDዎች ብቻ በመሆናቸው 117 CDዎች በመዝገብ ሳይመዘገቡ ተገኝቷል፡፡

በመንግሥት ንብረት መመሪያ መሠረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለትን ዕቃ በመዝገብ ላይ አለመመዝገብ ንብረትን ለብክነትና ለጥፋት ሊዳርግ ይችላል፡፡

ያልተመዘገቡ CDዎች በንብረት መዝገብ ላይ እንዲመዘገቡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ ለወደፊቱም ም/ቤቱ ማንኛውም የንብረት ደረሰኝ የተቆረጠለት ዕቃ ሁሉ በአግባቡ

መመዝገቡን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት መዘርጋት እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብሎታል፡፡

7.4 <u>በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቀድ</u>

<u>ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረገ ዕቃ መገኘቱ</u>

ዕቃ ከንብረት ክፍል ወጪ ሲደረግ በሚመለከተው ኃላፊ እየተፈፈቀደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ቶነር 49-A የተባለ ዕቃ የዕቃ ወጪ መጠየቂያ (ሞ/20) እንዲሁም የዕቃ ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) ሣይዘጋጅለትና በኃላፊ ሳይፈቀድ በመዝገብ ላይ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ያልተፈቀደ እቃ ከንብረት ክፍል ሊወጣ ይችላል ይህም የመንግስት ንብረት ለብክነት እንዲጋለጥ መንሰኤ ሊሆን ይችላል፡፡

የመንግስትን ንብረት በአግባቡ ለመጠቀምና ከብክነት ለማዳን ይቻል ዘንድ ንብረት ሳይፈቀድ ወጪ መደረግ የለበትም፡፡ ሳይፈቀድ የወጣውም ቶነር ጉዳይ ሆኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የሥራ አመራሩ የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብሎታል፡፡

7.5 <u>ለበርካታ አመታት ተከማችተው የተገኙ ንብረቶች</u>

በመንግሥት ንብረት መመሪያ ቁጥር 6/91 መሰረት አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች እንዲወገዱ መደረጉን እንዲሁም ሊያገለግሉ የሚችሉት ደግሞ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በድሬድዋ ዩኒቨርሲቲ በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ እና በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ንብረቶች የሚገኙ ሲሆኑ የሚሸጡ፣ የሚተላለፉ ወይም ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ተለይተው እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣ የተለያዩ ከትምህረት ሚኒስቴር የመጡ አዳዲስ ጠረጴዛዎች እና ወንበሮች ያለምንም አገልግሎት ጥበቃው አስተማማኝ ባልሆነ ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤በተወካዮች ምክር ቤት ከ1995 በጀት ዓመት ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጠ የጥርስ ህክምና መሣሪያ እና ሌሎች ለዚሁ የሚያገለግሉ ዕቃዎች እንዲሁም ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ ኮምፒዩተሮች ፤ በገንዘብና ኢኮኖሚ

ልማት ሚኒስቴር በርካታ ኮምፒውተሮች፣ ፕሪንተሮች፣ ወንበሮች፣ የመኪና መለዋወጫዎች እንዲሁም የተለያዩ ዕቃዎች ፤ በኢትዮጵያ ስብሰባ ማዕከል፤ አገልግሎት የማይሰጡና ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የተለያ ንብረቶች ለረዥም ዓመታት ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑን፤ እንዲሁም ለረዥም ዓመታት የቆዩ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ሶስት መኪናዎች መገኘታቸውና አንዱ ተሽከርካሪ ሊብሬ የሌለው መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ሊወገዱ የሚገባቸው እቃዎች በወቅቱ ካልተወገዱ እንዲሁም ተጠግነው ሊያገለግሉ የሚችሉ ንብረቶች ተለይተው ወቅታዊ አርምጃ ካልተወሰደ ንብረቶች ለብልሽት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡

ሊወገዱ የሚገባቸው እንዲወገዱ፤ተጠግነው አገልግሎት የሚሰጡት ደግሞ እንዲጠገኑ በወቅቱ እርምጃ ሊወስድባቸው የሚገባ መሆኑን በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳቡን ተቀብሎታል፡፡

7.6 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች</u>

በመ/ቤቶች የሚገኙ ተሽከር ካሪዎች አያያዝ ሁኔታ ኦዲት ሲደረግ፤ በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ያለአገልግሎት የቆሙና የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች፣ እንዲሁም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እና የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው ሞተር ሣይክሎች መኖራቸው፤ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት፤ሁለት ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት መታወቂያ የሌላቸው እና መኪናዎቹ በአካል ቀርበው ሲታዩ የሞተር ቁጥር የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡

ተሽከርካሪዎች በአግባቡ እንዲጠበቁ ካልተደረገ መስጠት የሚገባቸውን አገልግሎት ላይሰጡና ለስርቆት ሊዳረጉ በተጨማሪም መ/ቤቱን ላላስፈላጊ ወጪ ሊዳርጉት ይችላል፡፡

የመንግስት ንብረት ውጤታማ ሳይሆን ሲቀር በመመሪያው መሰረት ማስወገድ ተገቢ ነው፡፡ በተጨማሪም ሊብሬና የሞተር ቁጥር የሌላቸው ተሽከርካሪዋች በትክክል የመ/ቤቱ ለመሆናቸው ማረጋገጫ የሌላቸውና በጉዞው ላይ እያሉ አደጋ ቢደርስባቸውና በህግ ለመጠየቅ ጉዳዩን አስቸጋሪ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም የሚወገዱትን ተሽከርካሪዎች

ማስወገድ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸውን ደግሞ የባለቤትነት መታወቂያ ማውጣት እንደሚያስፈልግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>ልዩ ልዩ</u>

- በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት በ2000 በጀት አመት የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ውጤት እና የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት እንዲስተካከል አስተያየት የሰጠበት የሳጥን ሂሳብ ብር 216,256.11 ሳይስተካከል የተገኘ በመሆኑ እንዲስተካከል ለድርጅቱ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት በድጋሚ አሳስበናል፡፡
- በኢትዮጵያ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት፤ በታላቁ ቤተ መንግስት፤ የውስጥ ኦዲት ስራ ያልተከናወነ መሆኑ ታውቋል፡፡ የውስጥ ኦዲቱ በዓመቱ ሊሠራ ያቀደውን ኦዲት በመከፋፈል ኦዲት አድርጎ ውጤቱን ለበላይ አካል ሪፖርት ማቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች

የ2002 በጀት ዓመት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሀሳብ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

1. <u>የ2002 በጀት ዓመት የባለስልጣን መቤቱ የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ለኦዲት ያልቀረበ ስለመሆኑ</u>

   የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደርን ለመደንገግ የወጣ አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ 62 (2) እና (3) የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኃላ ባለው የሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ሂሣቡን ዘግቶ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም ለኦዲት ማቅረብ እንደሚገባ ይገልፃል፡፡ ይሁን እንጂ የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ በፋይናንስ አዋጁ መሰረት እስከ መስከረም 30/2003 ተዘግቶ መቅረብ ሲገባው ዘግይቶ ታህሣስ 14/2003 ዓ.ም በመቅረቡ ምክንያት የባለስልጣን መ/ቤቱን የተጠቃለለ የሂሳብ መግለጫ ኦዲት አድርጎ አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

   የባለሥልጣኑ ሂሳብ በየወሩ ባለመጠቃለሉ ሂሣቡ በወቅቱ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል እንዳይቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

   የባለሥልጣን የመ/ቤቱን የፋይናንስ እንቅሥቃሴ ሪፖርት በወቅቱ አዘጋጅቶ ለማቅረብ ያስችለው ዘንድ ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የሂሣብ ሪፖርት በወቅቱ እንዲመጣ በማድረግ የተጠቃለለ ሪፖርት በየወሩ ቢዘጋጅ የዓመቱ ሂሣብ በወቅቱ ሊዘጋ የሚችልበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ ለወደፊቱ የተጠቃለለ ሪፖርት በየወሩ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም የተጠቃለለው የመ/ቤቱ የሂሣብ ሪፖርት በአዋጁ መሠረት ወቅቱን ጠብቆ ሊዘጋጅ እና ለኦዲት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

   የሥራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የተቀበለው ሲሆን ባለስልጣን መ/ቤቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በኮርፖሬት ደረጃ የሂሣብ ሪፖርት ለማዘጋጀት በሂደት ላይ በመሆኑና የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን እና የጉምሩክ ባለስልጣል በአንድ በመዋሃዳቸው ምክንያት የሂሳቡን ከወጪ ቀሪ አጣጥሞ ለመዝጋት ያልተቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

## 2. የገቢና የወጪ ንግድ (Import and Export) ቀረጥና ታክስን በተመለከተ

### 2.1 በዕለቱ ወደ ባንክ ገቢ ያልተደረገ ሂሣብ

እያንዳንዱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በየእለቱ የሚሰበስበውን ገንዘብ በሙሉ በእለቱ ወደ ባንክ ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን እንዲሁም ሂሣቡ በትክክል ወደ ባንክ ገቢ ስለመደረጉ የሚጣራበት የቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በድምሩ ብር 5,094,327.00 በወቅቱ ባንክ ገቢ ሳይሆን ከ 1-11 ቀን በገንዘብ ያጅ እጂ የቆየ መሆኑ፤
- በሞጆ መቅረጫ ጣቢያ ከግል ባንኮች በቼክ በየእለቱ የሚሰበሰበዉ ገቢ ሳይመነዘር እስከ 15 ቀን የሚቆይ መሆኑ፤
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በተለያዩ ደረሰኞች የተሰበሰበ ቀረጥ ሳይመዘገብ ማስረጃው በገንዘብ ያጂ እጅ እስከ 15 ቀን የሚዘገይ መሆኑ፤

ለመንግስት ገንዘብ ብክነት መንስኤ ሊሆን ይችላል፡፡

የተሰበሰበ ገቢ በእለቱ ወደ ባንክ እንዲገባና ሂሳቡም በትክክል የገባ መሆኑ እየተረጋገጠ በእለቱ መመዝገብ እንዳለበት ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የስራ አመራር አስተያየታችንን የሰጠን ሲሆን ባለስልጣን መ/ቤቱም ይህን ሊያረጋግጥ የሚችልበትን የቁጥጥር ስርአት ሊዘረጋ እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የቅ/ጽ/ቤቶቹ የስራ አመራር ተቀብለውታል፡፡

የሞጆ መቅረጫ ጣቢያን በተመለከተ በአካባቢው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ስላልተከፈተ፣ ለጊዜው አስመጪዎች ራሳቸው ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ገንዘቡን ገቢ እያደረጉ የባንክ እስሊፕ እንዲያቀርቡ በማድረግ ችግሩን ለማቃለል ጥረት እየተደረገ መሆኑና፣ ችግሩን ለዘለቄታው ለመፍታት ከዋና መ/ቤት ጋር በጋራ በመሆን መፍትሄ እያፈላለጉ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 2.2 ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.Code) እና CPC Code ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2009 አንቀጽ 45(1) መሰረት ዕቃዎች፡-

ሀ) በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.Code) ባለመመደባቸው ምክንያት

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብር 342,777.13፣
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 9,993.58፣
- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በEL-Sewedy Cables በተባለ ድርጅት በሁለት ዲክላራሲዮን ከገባው ዕቃ ብር 1,349,389.66፣

ለ) በትክክለኛው CPC Code ባለመመደባቸው ምክንያት እቃዎች ያለአግባብ በሁለተኛ መደብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በመደረጉ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ከመኪና መለዋወጫ በድምሩ ብር 28,195.52 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

በድምሩ ከሶስቱም ቅ/ቤ/ቶች ብር 1,730,356.29 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር ካልተመደቡ እንዲሁም የሁለተኛ መደብ ተጠቃሚ ባልሆኑ ዕቃዎች ላይ ድርጅቶች ማግኘት የማይገባቸውን ጥቅም እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡ በዚህም ምክንያት መንግሥት ሊሰበስብ የሚገባውን ገቢ እንዲያጣ ያደርጋል፡፡

ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር ባለመመደባቸው ምክንያት ያልተሰበሰበ ሒሳብ ብር 1,730,356.29 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲሰበሰብ እንዲሁም እያንዳንዱ እቃ በየትኛው ታሪፍ ቁጥር ላይ እንደተመደበ የሚገልጽ የተሟላ መረጃ መስጫ ዲክላራሲዮን መሞላት እንዳለበት እና የሚመለከታቸው ሠራተኞችም በተለይ እያንዳንዱ ዕቃ የተመደበበት ታሪፍ ቁጥር ባልታወቀበት ሁኔታ ዲክላራሲዮን ተቀብለው እንዳያስተናግዱ አስፈላጊው የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ መሰራት እንዳለበት  ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የስራ አመራር አስተያየታችንን

ሰጥተናል፡፡ የባለስልጣን መ/ቤቱም ይህን ሊያረጋግጥ የሚችልበትን የቁጥጥር ስርአት መዘርጋቱን ማረጋገጥ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ያልተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር 38,189.10 ከሚመለከታቸው
- ግብር ከፋዮች ገንዘቡ የተሰበሰበ ለመሆኑ ከተሰጠዉ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡ በዚሁ መሰረት ብር 315,991.45 ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ገንዘቡ የተሰበሰበ ሲሆን፣ ለቀሪው ብር 26,785.68 የክፍያ መጠየቂያ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች የተላከ መሆኑን በላከው ምላሽ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም ችግሩን ለማስወገድ በታሪፍ አመዳደብ ላይ ለሰራተኞች ስልጠና እንደሚሰጥ ገልፀዋል፡፡
- የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራርም ያልተሰበሰበው ገቢ እንደሚሰበስቡ ገልጸዋል፡፡

## 2.3 የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው

በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣ አዘገጃጀት፣ ስርጭት አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 10/1996 መሰረት የጨርቃ ጨርቅ ውጤቶች፣ ጫማዎች፣ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች እና የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች በመነሻ ዋጋ መሰረት መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በድምሩ ብር 410,661.06 ፣
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,239.42

በአጠቃላይ ከሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች በመነሻ ዋጋ መሰረት ባለመሰራቱ ምክንያት ብር 412,900.48 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

በመመሪያው መሰረት ካልተሰራ ወደ ሀገር ውሰጥ ከሚገቡ ዕቃዎች ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው እቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ባለመስተናገዳቸው ምክንያት ያልተሰበሰበ የቀረጥ ብር 412,900.48 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲሰበሰብ ለወደፊቱም በመመሪያው መሰረት እንዲሰራ አሳስበናል፡፡ የባለስልጣን መ/ቤቱም መመሪያው ተግባራዊ መደረጉን የሚከታተልበት የቁጥጥር ስርአት ሊዘረጋ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ያልተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር 2,239.42 ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ገንዘቡ የተሰበሰበ ለመሆኑ ከተሰጠዉ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት ብር 275,341.94 ለመሰብሰብ የክፍያ መጠየቂያ ለሚመለከታቸው ድርጅቶች የተላከ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፣ በአምቼ ስም በዲ/ዮን ቁጥር C-24824/09 ለተጠየቀዉ አስመጪው የ"IVECO" ብቸኛ ወኪል በመሆኑና መመሪያውም ሲታይ ብቸኛ ወኪሎች በሚያስመጧቸው እና በጉምሩክ የቀረበው የኤሌክትሮኒክስ እና የተሸከርካሪ መለዋወጫ እቃዎች ዋጋ ከአለም አቀፍ ዋጋ አንጻር ሲታይ ከፍተኛ ልዩነት የሚታይበት ሆኖ ሲገኝ ከአለም አቀፍ የመረጃ ምንጭ በሚገኝ ዋጋ መሰረት ጣቢያው ለመወሰን እንደሚችል በመግለጽ በዚሁ መሰረት ለብቸኛ ወኪሎች አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ይሁን እንጂ የመኪና መለዋወጫውን በተመለከተ በዲክላራሲዮን ቁጥር C-26515/09 ተመሳሳይ እቃ ከተመሳሳይ አገር (ጣሊያን) ወደ ሀገር ውስጥ በሌላ ድርጅት (በDouble M Trading PLC) የሚገባ መሆኑ ታውቋል፡፡ ከዚህ በመነሳት አስመጪው ብቸኛ ወኪል ናቸው ለማለት ያስቸግራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከላይ ለተጠቀሱት እቃዎችም ሆነ ለሌሎች ዕቃዎች ብቸኛ አስመጪዎች የትኞቹ ድርጅቶች እንደሆኑ ከሚመለከተው አካል በግልጽ ተለይተው የተገለጹበት ሁኔታ ለመኖሩ መረጃ ሊቀርብ አልቻለም፡፡

የሚመለከታቸውም ሰራተኞች ተጠይቀው በተለምዶ እየሰሩበት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡

በዚህም ምክንያት የተሰጠው ምላሽ አሳማኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመሆኑም ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ከሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲሰበሰብ አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

በተጨማሪ ዋናው መ/ቤት በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ ተደጋጋሚ ችግር ለሚታይባቸዉ የተወሰኑ እቃዎች የመነሻ ዋጋ እየወሰነ በዋጋ CD አማካይነት ስራ ላይ እንዲውል የሚያደርግ መሆኑ ይታወቃል፤፤ከዚህ በተቃራኒው ግን ብቸኛ አስመጪዎች ናቸው በሚል ከመነሻ ዋጋ (CD-Price) በታች የቀረቡ የዋጋ ሰነዶች ተቀባይነት የሚያገኙበት ሁኔታ ስላለና በቀረጥና ታክስ አሰባሰቡ ላይ ከፍተኛ ክፍተት እየተፈጠረ ስለሆነ ዋናው መ/ቤት ይህን አስመልክቶ ግልጽ የሆነ መመሪያ ለጣቢያዎች ሊያስተላልፍ ይገባል፡፡

## 2.4 <u>በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ ያልተሰበሰበ ብር 2,882,006.68</u>

በጉምሩክ ዋጋ መረጃ ክምችት፣አዘገጃጀት፣ ስርጭትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 10/1996 አንቀጽ 17 (ለ) መሰረት በአስመጪው የቀረበው በዋጋ መረጃ ክምችቱ ውስጥ ተመዝግቦ ከሚገኘው አንድ አይነት ዕቃ ዋጋ ጋር ሲነፃፀር ከ5 በመቶ ወይም 10% (አነስተኛ የስጋት ደረጃ ላለው አስመጪ) የበለጠ ሲያንስ ቀረጥና ታክስ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በማነጻጸሪያ ዋጋ መሰረት ባለመሰራቱ ምክንያት:-

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብር 454,663.25
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 160,733.43
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,266,610.00

በአጠቃላይ ከሦስቱም ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 2,882,006.68 ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ተገኝቷል፡፡

ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

ትክክለኛው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ባለመወሰዱ ምክንያት ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ብር 2,882,006.68 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች እንዲሰበሰብ እንዲሁም አሰራሩ በመመሪያው መሰረት እንዲስተካከል ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የስራ አመራር አሳስበናል፡፡

- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ያልተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር 160,733.43 ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ገንዘቡ የተሰበሰበ ለመሆኑ ከተሰጠዉ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት አስመጪው ድርጅት ከአምራች ኩባንያ በቀጥታ የሚያመጣ በመሆኑና ዋጋው በከፍተኛ ደረጃ ልዩነት ሊያሳይ የቻለው የዋጋ CDው ስህተት ያለበት በመሆኑ ሊሆን ይችላል በማለት በተደጋጋሚ አስመጪው ያቀረበውን ኢንቮይስ በማያያዝ ለዋናው መ/ቤት እያሳወቁ ሲስተናግዱ የቆዩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጣቢያው በዋጋ መረጃው ላይ ልዩነት ቢኖረውም እንኳን በዋጋ መረጃው መሰረት አስተናግዶ ልዩነቱን ለዋናው መ/ቤት ማቅረብ ሲገባው ከዋጋ CD በላይ አስመጪው ያቀረበውን ኢንቮይስ ተአማኒ አድርጎ ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ መደረጉ መመሪያውን ያልተከተለ አሰራር ነው፡፡

  በመሆኑም የተሰጠውን ምላሽ አሳማን ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ያልተሰበሰበው የመንግስት ገንዘብ ከሚመለከተዉ ድርጅት ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ ዋናው መ/ቤትም ጉዳዩን ሊከታተለው ይገባል፡፡
- የድሬ ዳዋ ቅ/ጽ/ቤት ከሦስቱ ዲክላራሲዮኖች ያልተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ብር 2,164,198.00 ከሚመለከታቸው ድርጅቶች ለመሰብሰብ ጥረት የሚያደርጉ መሆኑን ገልፀው በዲክላራሲዮን ቁጥር C-744/09 የሚፈለገው ቀሪ ሂሳብ (ብር 102,412.00) ግን የፍተሻ ውጤቱ ከአዳማ ቅ/ጽ/ቤት እንዲመጣ ደብዳቤ ጽፈው በመጠየቅ ላይ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

## 2.5 <u>ቀረጥና ታክስ በትክክል የተሰላና ሊሰበሰብ የሚገባውም ገቢ መሰብሰቡን ለማጣራት ያልተቻለ</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2009 አንቀጽ 18(1) መሰረት የዋጋ ሰነድ አስፈላጊ ዝርዝሮችን የያዘ መሆኑን እና ቀረጥና ታክስም በዚሁ መሰረት መሰላቱንና መሰብሰቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በዲክራሲዮን ቁጥር C-26028/2009 ለገባው እቃ የእያንዳንዱ ዕቃ ዋጋ ሳይታወቅ ጥቅል ዋጋውን (CIF Value) በመውሰድ በአንድ የታሪፍ ቁጥር ላይ በመመደብ በ20% የጉምሩክ ቀረጥ ምጣኔ ገቢ የተሰበሰበ ሲሆን ከነዚህ ዕቃዎች ውስጥ በ30% እና በ35% የቀረጥ ምጣኔ መሰረት ሊስተናገዱ የሚገባቸው እቃዎችም እንዳሉ ታውቋል፡፡
- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በዲክራሲዮን ቁጥር C-37581,29/10/2009 እና C-24159,15/07/2009 በዋጋ ሠነድ ላይ የእያንዳንዱ ዕቃ ዝርዝር እና የእያንዳንዱም ዕቃ ዋጋ ሳይገለጽ በዝርዝር የዕቃውን ዋጋ የሚያሳይ የዋጋ ሰነድ እንደቀረበ ተደርጎ ቀረጥና ታክስ ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡
- በአዲስ አበባ ኤርፖርትና በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት ብዙ ዕቃዎችን የያዙ የዋጋ ሰነዶች ላይ እያንዳንዱ ዕቃ የተመደበበት ታሪፍ ቁጥር በተሟላ ሁኔታ በዕቃዎች መረጃ መስጫ ዲክላራሲዮን ላይ ሳይሞላ ቀረጥና ታክስ ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት እያንዳንዱ እቃ የተመደበበት የታሪፍ ቁጥር ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በአዲስ አበባ ኤርፖርትና በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የእቃውን ዋጋና ታሪፍ ቁጥር ለመወሰን አሻሚ የሆኑ አንዳንድ የዋጋ ሰነዶች በፍተሻም ይሁን በመረጃ መስጫ ዲክላራሲዮን ላይ ስለእቃው ሁኔታ ተጨማሪ መረጃ ሳይቀርብ ዲክላራሲዮኑ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

ከፍተኛ የታሪፍ ምጣኔ ያላቸው ዕቃዎች አነስተኛ የታሪፍ ምጣኔ ካላቸው ዕቃዎች ጋር አንድ ላይ እየተመደቡ በአነስተኛ የታሪፍ ምጣኔ መሰረት ቀረጥና

ታክሱ የሚሰበሰብበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህም ለብልሹ አሰራር በር ከፋች ነው፡፡

የዋጋ ሰነዱ ብዙ እቃዎች ሲይዝና የተገለፁት እቃዎች ለታሪፍ አመዳደብና ዋጋውን ለመተመን አሻሚ በሚሆኑበት ወቅት እያንዳንዱ ዕቃ በየትኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S-code) ላይ እንደተመደበ በዕቃዎቹ ፍሬ ነገር መግለጫ ላይ ትራንዚተሩ መረጃ እንዲሰጥ በማድረግና በዚያው መሰረት ትክክለኛነቱ እየተረጋገጠ በትክክለኛው የታሪፍ ምጣኔ መሠረት ቀረጥና ታክሱ መሰብሰቡ መረጋገጥ አለበት፡፡

በሌላም በኩል አሻሚ በመሆናቸው ምክንያት ለታሪፍ አመዳደብ ግልጽ ያልሆኑ እቃዎች ደግሞ በፍተሻ በማረጋገጥ የእቃው አይነት የሚገለጽበትና ቀረጥና ታክሱም ይህንኑ መሰረት አድርጎ እንዲሰራ የሚደረግበት አሰራር በአግባቡ ተግባራዊ መደረግ እንዳለበትና እንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ የገባው ዝርዝር ዕቃ ዋጋ የሚያሳይ የዋጋ ሰነድ ባልቀረበበት ሁኔታ መስተንግዶ መስጠቱ አግባብ እንዳልሆነ በመግለጽ አሰራሩ ሊስተካከል እንደሚገባዉ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የስራ አመራር አስተያየታችንን ሰጥተናል፡፡

- ቅ/ጽ/ቤቶቹ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የተቀበሉት ሲሆን፣ በዚሁ መሰረት የአዲስ አበባ የንግድ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በዲክራሲዮን ቁጥር C-26028/2009 የገባውን እቃ በተመለከተ ድርጅቱ ያለበትን ቀሪ እዳ እንዲከፍል የክፍያ መጠየቂያ መላኩን በሰጠው ምላሽ ገልጿል፡፡ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር ለሰራተኞች የተለያየ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የሚሰጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡
- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤትም ከላይ ለተገለጹት የአሰራር ክፍተቶችን ለማስተካከል በአግባቡ Decelaration of fact እንዲሞላ እየተደረገ መሆኑንና በፍተሻምና በአሰስመንት ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና የተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 2.6 የማስጫኛ እና የኢንሹራንስ ክፍያ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 39 መሰረት በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ እንዲካተት የማይደረግ መሆኑ

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 1 ሀ መሰረት ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ እቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን ለእቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈል ዋጋ ላይ እቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ ትራንስፖርት፣ የመጫኛ፣ የማራገፊያና፣ የኢንሹራንስ ወጪ በመደመር ቀረጥና ታክስ የሚሰላ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፡-

- ለማስጫኛ ከተከፈለዉ ወጪ ውስጥ 1/3ኛውን ብቻ በመውሰድ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ (CIF Value) ውስጥ የሚካተት መሆኑ፣
- የማስጫኛ እና ኢንሹራንስ ደረሰኝ በአስመጪዎች በማይቀርብበት ጊዜ ለማስጫኛ ዋጋ የFOB ዋጋውን 10%፣ ለኢንሹራንስ ደግሞ የFOB ዋጋና የማስጫኛውን ድምር 5% በመውሰድ ቀረጥና ታክሱ የሚሰላ መሆኑ

ታውቋል፡፡

አሰራሩም ለረዥም ጊዜ የቆየ ሲሆን በመመሪያ ያልተደገፈ እና በልምድ ሲሰራበት የቆየ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በአዋጁ መሰረት ለማስጫኛ የተከፈለዉ ጠቅላላ ወጪ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ (CIF value) ውስጥ ካልተካተተ መንግስት ከገቢ እቃዎች ማግኘት ያለበትን ገቢ ላያገኝ ይችላል፡፡

የማስጫኛና ኢንሹራንሰ ደረሰኝ በአስመጪዎች በማይቀርብበት ጊዜ የማስጫኛና ኢንሹራንስ ዋጋውን ለመወሰን እንዲቻል በቂ ጥናት ተደርጎ ይህ ሁኔታ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር የሚወሰንበት ግልጽ የሆነ መመሪያ መዘጋጀት እንዳለበት ለስራ አመራሩ አስተያየታችንን የሰጠን ሲሆን፣ በተጨማሪም ለማስጫኛ የተከፈለው ጠቅላላ ዋጋ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ውስጥ 1/3ኛው ብቻ ስለሚካተት ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ጉዳዩን በማጥናት አሰራሩ ህጋዊ መሰረት እንዲኖረው ማድረግ ይገባል፡፡

በመሆኑም በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 39 ንኡስ አንቀጽ 1 (ሀ) ወደሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎች የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ሲወሰን ለእቃዎቹ በተከፈለው ወይም በሚከፈል ዋጋ ላይ እቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል መጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ ትራስፖርት፣ የማስጫኛ፣ የማራገፊ፣ የመንከባከቢያ እና የኢንሰሹራንስ ክፍያን ያካተተ መሆን ስላለበት አሰራሩ በዚሁ መሰረት መስተካከል እንዳለበት አሳስበናል፡፡

አሰራሩ ረዘም ላለ ዓመት ሲሰራበት የቆየ መሆኑና በመመሪያ ሊደገፍ እንደሚገባው በማመን ጉዳዩን ዋናው መ/ቤት በደብዳቤ እንዲያውቀው የተደረገ ሲሆን፣ በዚህም መሰረት በዋናው መ/ቤት አዲስ መመሪያ ለማውጣት በዝግጅት ላይ መሆኑ ተገልጿል፡፡

## 2.7 <u>በተመሳሳይ የወጪ ባንክ ፈቃድ ቁጥር ሁለት ጊዜ ወደ ውጭ የተላከ እቃ</u>

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል ድሬ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/ የግል ድርጅት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አዲስ ከተማ ቅርንጫፍ በተሰጠ ተመሳሳይ የባንክ ፈቃድ ቁጥር ሁለት ጊዜ እቃ ወደ ውጭ አገር ልኮ ተገኝቷል፡፡

መንግሥት ማግኘት ያለበትን የውጪ ምንዛሪ እንዲያጣና የወጪ ንግድን ለማበረታታት በተሰጠው መብት ግለሰቦች ያለአግባብ እንዲጠቀሙ ያደርጋል፡፡ አንድ አስመጪ በተመሳሳይ ባንክ ፍቃድ ቁጥር ከአንድ ጊዜ በላይ መስተንግዶ እንዲያገኝ የሚደረግ ከሆነ አገራችን ልታገኝ የሚገባትን የውጪ ምንዛሪ እንድታጣ የሚያደርግ አሰራር ከመሆኑም በላይ ህገወጥ ስራ እንዲስፋፉ ከፍተኛ እድል የሚፈጥር በመሆኑ የASYCUDA የመረጃ መቀበያ የቁጥጥር ስርአት ይህን መሰል ህገወጥ አሰራሮች እንዳይከሰቱ ሊከላከል በሚችል መልኩ የሚስተካከልበት ሁኔታ መመቻቸት እንዳለበት እና በአንድ ፈቃድ ሁለት ጊዜ የላከውም ድርጅት የውጭ ምንዛሪውን ተመላሽ እንዲያደርግ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

በተጨማሪም የተሳሳተ የባንክ ፈቃድ በሚሰጡ ባንኮች ላይ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር ሊዘረጋ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ተቀብሎታል፡፡ ASYCUDA አንድ ላኪ በተመሳሳይ የባንክ ፈቃድ ቁጥር ደጋግሞ ቢልክ የሚቆጣጠርበት ስርአት የሌለው በመሆኑ ችግሩ መፈጠሩን ፣ የችግሩ መንስኤዎች ደግሞ ባንኮች በመሆናቸው ጉዳዩንም ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያሳወቁ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተሰጠውም የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ASYCUDA የዚህ አይነቱን ችግር መቆጣጠር እንዲችል የማሻሻያ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

## 2.8 <u>በባንክ በተፈቀደው የውጪ ምንዛሪ እና ተገዝቶ ወደ አገር ውስጥ በገባው የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ (FOB) መካከል ስለታየው የውጭ ምንዛሪ ልዩነት</u>

ለኦዲት ከተመረጡ ዲክላራስዮኖች ውስጥ ከባንክ የተፈቀደላቸው የውጪ ምንዛሪ ቀረጥና ታክስ ከተከፈለበት የእቃ የዋጋ ጋር ሲነጻጸር

- በድሬደዋ ቅ/ጽ/ቤት ወደአገር ውስጥ ከገቡት እቃዎች፣ የእቃው ዋጋ በባንክ ከተፈቀደው የውጭ ምንዘሪ በ USD 3,723,716.75 ብልጫ የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል፡፡

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በ18 ዲክላራሲዮኖች ወደ አገር ውስጥ ከገቡ እቃዎች፣ የእቃው ዋጋ በባንክ ከተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ በ USD 610,907.27 ብልጫ ሚያሳይ መሆኑ፣

<u>ከነዚህ ውስጥ ለምሳሌ</u>

1. በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት በዲክላራሲዮን ቁጥር c-2000/10 ወደ አገር ውስጥ ለገባው 5250 ኩንታል ስኳር የተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ ደግሞ $ 5,250.00 ነው፡፡ ይህም ማለት አንድ ኩንታል ስኳር በ USD 1 እንደተገዛ ያመለክታል፡፡
2. በድሬደዋ ቅ/ጽቤት ከብራዚል ተገዛ ተብሎ ወደ አገር ውስጥ የገባ የአንድ ኩንታል ስኳር USD 0.31 እንደተገዛ ያመለክል፡፡

እነዚህ ማስረጃዎች አጠራጣሪና ሊታመኑ የማይችሉ እንደሆነ መገመት የማያዳግት በመሆኑ አሰራሩ ህጋዊ ያልሆነ የውጭ ምንዛሪ ግብይትን እና በአገራችን የፋይናንስ ተቋማት በኩል የማይታወቅ የገንዘብ ዝውውር እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑ ተገቢው ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

ከባንክ ባልተገኘና በህገወጥ መንገድ በተገኘ የውጭ ምንዛሬ እቃ ወደ አገር ውስጥ ሊገባ ይችላል፡፡

ምንም እንኳ ቅ/ጽ/ቤቶች በዋጋ CD መሰረት ሊሰበሰብ የሚገባውን ቀረጥና ታክስ የሰበሰቡ ቢሆንም፣ በቀረጥ ማስከፈያ ዋጋና (FOB) በተፈቀደው የውጭ ምንዛሪ መካከል ከፍተኛ ልዩነት በሚታይበት ጊዜ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፋይናንስ ተቋማት ጋር ግንኙነት በመፍጠር የልዩነቱ መንስኤ የሚጣራበት አሰራር ቢዘረጋ ህጋዊ ባልሆነ የውጭ ምንዛሪ ወደ አገር ውስጥ ሊገባ የሚችለውን እቃ መቆጣጠር ይቻላል፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ ተመሳሳይ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙት ተገቢውን የማጣራት ስራ መከናዎን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

- የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የስራ አመራሩ ተቀብሎታል፡፡
- የድሬ ደዋ ቅ/ጽ/ቤት አስመጭዎች አነስተኛ የውጭ ምንዛሪ ከፋይናንስ ተቋማት አስፈቅደው በርከት ያለ እቃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ካደረጉ የውጭ ምንዛሬን በቁጠባ ከመጠቀም አንጻር ለአገራችን ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም በማለት ተገልጿል፡፡

## 2.9 <u>ቀጣዩ የጉምሩክ ስነስርአት በወቅቱ ያልተፈጸመባቸው ዲክላራሲዮኖች ሳይሰረዙ እና አሴስ ሳይደረጉ መገኘታቸው</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/01 አንቀጽ 17 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የጉምሩክ ዲክራሲዮን ከቀረበበት ወይም የክፍያ ማስተወቂያ ከተዘጋጀበት ቀን አንስቶ እስከ 5 ቀናት ድረስ ቀጣዩን የጉምሩክ ስነሥርዓት ካልፈፀመ ዲክላራሲዮኑ እንዲሠረዝ የተደረገ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል በE-2912, 30/01/2010 እና በ E-3475 , 02/04/2010 የተመዘገቡት ዕቃዎች አሴስ ሳይደረጉ ወደ ውጭ የተላኩ መሆኑ፣ እንዲሁም ተመዝግበው ቀጣዩን የጉምሩክ ስነስርአት ሳይፈጽሙ ለረገጅም ጊዜ ሳይሰረዙ የቆዩ 4 የወጪ ዲክላራሲዮኖች መገታቸው፣

- በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት 40 ዲክላራሲዮኖች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሳይፈጸምባቸው ከተከፈቱ ከአመት በላይ የሆናቸው ዲክላራሲዮኖች በትራንዚት ቡድን ክፍል ተከማችተው ተገኝተዋል፡፡

ከአገር ውስጥ የሚላከው እቃም በተሰጠው የባንክ ፈቃድ ልክ መሆኑን ለማረጋገጥ ያዳግታል፡፡ ይህም መንግሥት ሊያገኝ የሚገባውን የውጭ ምንዛሪ እንዲያጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በተጨማሪ እቃዎች የጉምሩክ ስነስርአት ሳይፈፀምባቸው ወደ አገር ውስጥ ሊገቡ የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡

በአዋጅ ቁጥር 622/01 በአንቀጽ 17 መሰረት ጊዜ ያለፈባቸውና በወቅቱ የጉምሩክ ስነ-ሥርዓት ያልተፈፀመባቸው ዲክላራሲዮኖች ላይ አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ሊሰረዙ እንደሚገባ ለየቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ስራ አመራር በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱም ጉዳዩን የሚከታተልበት ስርአት እንዲዘረጋ አሳስበናል፡፡

- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት አሴስ ሳይደረጉ ወደ ውጭ እንዲላክ በተደረገው እቃ ላይ ተሳታፊ በሆኑ በአጥፊዎች ላይ እርምጃ እንዲወሰድ ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት በ3/12/02 ደብዳቤ መጻፉ ታውቋል፡፡
- የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

## 2.10 ጥፋት በፈፀሙ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ

የጉምሩክ አስተላላፊዎች የሚያስፈሚቸውን ህጎችና መመሪያዎች በመተላለፍ በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ጥፋት ከፈጸሙ በአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 34/1998 እንዲሁም በተላላፊ ዕቃዎች ስነስርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 39/2002 አንቀጽ16 መሰረት የእቃ አጓጓዥ ከተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ዘግይቶ ከደረሰ ወይም ማጓጓዣው እንዲንቀሳቀስ በጉምሩክ ከተፈቀደ በኋላ ምክንያቱን ለጉምሩክ ሳያሳውቅና ፈቃድ ሳያገኝ እንዲቆይ ካደረገ በመመሪያዎቹ መሰረት አስፈላጊው አስተዳደራዊ እርምጃ የሚወሰድ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡

- በአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ ግልጽ የሆነ ጥፋት በፈጸሙ አንዳንድ የጉምሩክ አስተላላፊዎች ላይ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ የወጪ እቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የተወሰነላቸውን የጊዜ ገደብ ጠብቀው ባለማጓጓዛቸው ቅጣት ከተወሰነባቸው ሾፌሮች እና ወኪሎች ያልተሰበሰበ ብር 15,000.00 መኖሩ

ታውቋል፡፡

ህገወጥነት እንዲበረታታና ተደጋጋሚ ጥፋቶች እንዲፈጽሙ ይገፋፋል፡፡ በዚህ ምክንያት በገቢ አሰባሰብ ላይ የማጣራት የስራ ጫናን ሊያስከትል ይችላል፡፡ በተጨማሪም መንግስት ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዲያጣ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በቀረጥና ታክስ አሰባሰብ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ጥፋት በሚፈጽሙ አስተላላፊዎች፣ ሾፌሮችና የአስመጪ ወኪል ላይ በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ መወሰድ እንዳለበትና ይህንንም ለማድረግ በደንበኞች አገልግሎት እና በሌሎች የስራ ሂደቶች መካከል ተገቢው የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር መደረግ እንዳለበት እና ግዴታቸውን ያልተወጡ አጓጓዦችም ድጋሜ መስተንግዶ እንዳይሰጣቸው ቢደረግ ለመመሪያው አፈጻጸም ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑን እንዲሁም ሾፌሮችና የአስመጪ ወኪሎች ላይ የተጣለው ቅጣት መሰብሰብ እንዳለበት ለቅ/ጽ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የቅ/ጽ/ቤቶቹ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብለውታል፡፡

## 2.11 <u>የዋስትና የጊዜ ገደቡ ሲያልፍ ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተላለፈ ሂሣብ</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 3-4 እንደተመለከተው በጊዜያዊነት ወደ አገር ውስጥ የገባ እቃ በጊዜ ገደቡ ውስጥ ተመልሶ ከአገር መውጣት እንዳለበት ፣ የእቃው ቆይታ ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር የመቆያ ጊዜው እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ እቃው ተመልሶ ካልወጣ በዋስትና የተያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ መደረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ እንዲሁም ዕቃ በዋስትና ስለሚለቀቅበት ሁኔታ

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በወጣው የአፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 37/2002 ክፍል ሶስት 9 እና 10 መሠረት በሠነድ አለመሟላት ምክንያት በዋስትና የተያዘው ሂሣብ ሠነድ በ30 ቀናት ውስጥ ተሟልቶ ካልቀረበ ዋስትናውን የፈቀደው የሥራ ሂደት ለባለሥልጣኑ ገቢ እንዲደረግ ማዘዝ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡ በዚህ መሠረት

- በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በኩል በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ ለገባ ዕቃ በዋስትና የተያዘ ሂሳብ ብር 25,539.89፣ እንዲሁም በሰነድ አለመሟላት ምክንያት በዋስትና የተያዘ ሂሳብ ብር 127,538.37፣
- በድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት በኩል በሰነድ አለመሟላት ምክንያት በዋስትና የተያዘ ሂሳብ ብር 269,690.93፣
- በአዳማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በኩል በጊዜያዊነት ለገባ እቃ በዋስትና የተያዘ ሂሳብ ብር 247,160,667.72 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 197,000,000.00 ወደ ቀጥታ ገቢ መዞሩ ታውቋል፣
- በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዋስትና የተያዘ ሂሳብ ብር 55,389,492.76 ቦንድ ጊዜ ያለፈበትና በባለስልጣኑ ፈቃድ ጊዜያቸው ያልተራዘመላቸው፣

በድምሩ ብር 302,972,929.66 በመመሪያው መሰረት የዋስትና ጊዜ ገደቡ ቢያልፍም ወደ ቀጥታ ገቢ ያልተላለፈ መሆኑ ታውቋል፡፡

የዋስትና ጊዜው ያለፈባቸውን በአዋጁና በመመሪያው መሰረት ተፈፃሚ ካልሆነ መንግሥት ማግኘት ያለበትን ገቢ እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በጉምሩክ አዋጅ እና መመሪያ መሠረት በዋስትና የተያዘ ሂሣብ የጊዜ ገደቡ ሲያልፍ ወደ ቀጥታ ገቢ እንዲተላለፍ መደረግ ያለበት ሲሆን፣ ለወደፊቱም በዚህ ረገድ ክትትል እየተደረገ በአዋጁ መሠረት ወቅታዊ እርምጃ የሚወሰድበት አሰራር እንዲዘረጋ እናሳስበናል፡፡

- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠዉ የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ብር 127,768.55 ወደ ቀጥታ ገቢ የተላለፈ መሆኑን ከተሰጠዉ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

- የአዲስ አበባ የወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ጽ/ቤት የዋስትና ጊዜ ያለፈባቸው ድርጅቶች ሂሳብ ተጣርቶ ለጽ/ቤቱ የህግ ማስከበር ቡድን መተላለፉንና የህግ ማስከበር ቡድን ደግሞ የወንጀልን ጉዳይ እንጂ የፍታብሄርን ጉዳይ የማያይ በመሆኑ ለጉዳዩ እልባት መስጠት መቸጋራቸውን ገልጸዋል፡፡

## 2.12 የቫውቸር ስርአት ተጠቃሚዎች ወደ አገር ውስጥ ባስገቡት ጥሬ እቃ የተመረተው ምርት ወደውጭ ስለመላኩ ማረጋገጥ ያልተቻለ

በወጪ ንግድ የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ስርዓት አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 22/2000 አንቀጽ መ/4 መሰረት የቫውቸር ዋስትና ተሰጥቶበት ወደ አገር ውስጥ በገባ ጥሬ ዕቃ የተመረተው ምርት ወደ አገር በገባ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ወደ ውጪ መላኩንና ምርቱ ወደ ውጪ ለመላኩ ማስረጃዎች ለጉምሩክ ባለስልጣን ቀርበው ቫውቸሩ እንዲወራረድ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በወጪ ንግድ ላይ ለተሰማሩ ነጋዴዎች ጥሬ እቃ ወደ አገር ውስጥ እንዲያስገቡ በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የብር 68,769,394.97 ቀረጥና ታክስ ማበረታቻ ፈቃድ የተሰጣቸው ሲሆን፣ የቫውቸር ተጠቃሚዎች ወደ አገር ውስጥ ያስገቡት የጥሬ እቃም ሆነ ወደ ውጭ የተላከውን ምርት መከታተያ ስርአት ቢሆንም ያልተተገበረ በመሆኑ በመመሪያው መሰረት ስለመፈጸሙ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

በዚህም ምክንያት በቫውቸር ስርዓት ወደ አገር ውስጥ የገባ ጥሬ እቃ ለማምረት ስራ ሳይውል በቀጥታ ለሺያጭ ቢውል በቀላሉ አይታወቅም፡፡ ይህም ከውጭ ንግድ ለማግኘት የሚታሰበው የውጭ ምንዛሪ እንዳይገኝ እና ሊከፈል የሚገባውም ቀረጥና ታክስም ሳይሰበሰብ እንዲቀር ያደርጋል፡፡

ከጠቅላላው የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚዎች ውስጥ 27 ድርጅቶች የተፈቀደላቸው የቫውቸር መጠን በድምሩ ብር 68,769,394.97 ቀረጥና ታክስ አለማወራረዳቸውና ቫውቸራቸውንም ያላሳደሱ መሆኑ ታውቋል፡፡

ምርቱ ወደ ውጭ መላኩንና የውጭ ምንዛሬ ማስገኘቱን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ምርቱም ወደ ውጭ ካልተላከ ሊሰበሰብ የሚገባው ቀረጥና ታክስም ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

እያንዳንዱ የቫውቸር ስርዓት ተጠቃሚ ድርጅት በተፈቀደለት የቀረጥና ታክስ ማበረታቻ መሰረት ወደ አገር ውስጥ ባስገባው ጥሬ እቃ ያመረተው ምርት በአንድ አመት ውስጥ ወደ ውጭ አገር የተላከ መሆኑን ለመከታተል የሚያስችል የአመዘጋገብ ስርዓት በቅ/ጽ/ቤቱ ውስጥ ሊዘረጋ ይገባል፡፡ ያላወራረዱና ጊዜው ያልተራዘመላቸው ድርጅቶች እየተጣራ በመመሪያው መሰረት ተገቢ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

27ቱ የቫውቸር ደብተራቸውን ያላሳደሱ በመሆኑ ጉዳዩ ወደ ዋናው መ/ቤት የህግ ማስከበር ዘርፍ የተላለፈ መሆኑን፣ የቫውቸር ተጠቃሚ ላኪዎች በመመሪያው መሰረት ለመከታተል የሚያስችል ስርአት ለመዘርጋት በውጭ ባለሙያዎች ስራው መጀመሩን እና የቫወቸር ተጠቃሚዎች ሂሳብ በሰነድ አጣሪ ቡድን (PCA) እንዲጣራ በማድረግ እርምጃ መውሰድ መጀመሩን እና ድርጅቶቹም በ10 ቀናት ውስጥ ቀርበው ሂሳባቸውን እንዲያወራርዱ ማስታወቂያ የወጣ መሆኑ ተገልጿል፡፡

## 2.13 ለአንድ አይነት ዕቃ ሁለት የውጪ ምንዛሪ ዋጋ የተሰጠው ስለመሆኑ

በአዲስ አበባ ወጪና ሌሎች እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት በኩል በዲክላራሲዮን ቁጥር E-4051/2010 አባሪ ሰነዶች ውስጥ በኖቫ ስታር ጋርመንት ፋብሪካ ሀላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ወደውጭ የተላኩ ተመሳሳይ ዕቃዎች በአንድ ኮሜርሺያል ኢንቮይስ ላይ ሁለት አይነት ዋጋ ተጠቅሶ ተገኝቷል፡፡ ከተላኩት 1988 ኪሎ ግራም ተመሳሳይ እቃዎች ውስጥ፡-

- ክብደቱ 1896 ኪሎ ግራም ለሆነ እቃ የአንዱ ዋጋ በዶላር 0.85 ፣
- ቀሪው 92 ኪሎ ግራም ደግሞ የአንዱ ዋጋ በዶላር 4.285፣

በመሰላቱ በአነስተኛ የነጠላ ዋጋ የተስተናገዱት እቃዎች አገራችን ልታገኝ የምትችለውን የውጭ ምንዛሪ ያሳንሳል፡፡

ለአገራችን የሚያስገኘውን የውጭ ምንዛሪ ገቢ መጠን የሚቀንሰው ከመሆኑም በላይ ትክክለኛው የነጠላ ዋጋ የትኛው እንደሆነ ለመለየት አስቸጋሪ ይሆናል ፡፡ ከአገር ውስጥ የተላከውን እቃ የሚረከበው ድርጅት ከላኪው ጋር በሚኖረው

የጥቅም ትስስር የእቃ ዋጋ ኢንቮይስ ዝቅ እንዲል በማድረግ ከውጭ ንግድ የሚገኘው ምንዛሬ እንዲያንስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ከዲክሌራሲዮን ቁጥር E-4051/2010 አባሪ ሰነዶች ውስጥ በአንድ ኮሜርሽያል ኢንቮይስ ላይ አንድ አይነት ዕቃ የተለያየ የነጠላ ዋጋ መጠቀሱ ከውጭ ንግድ ላይ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ የሚያደርገው ከመሆኑም በላይ በተለይም በዝቅተኛ የነጠላ ዋጋ የተሰላው እቃ አገራችን ልታገኝ የሚገባትን የውጭ ምንዘሬ የሚያሳጣ በመሆኑ ተመሳሳይ ሁኔታ ሲያጋጥም ጉዳዩን ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመነጋገር ችግሩ የሚስተካከልበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት፡፡ የእቃው ዋጋም በጥሬ እቃነት ወደ አገር ውስጥ ከገባው አንድን እቃ ለማምረት ያስፈልጋል ተብሎ ከተገመተውና ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ ከተደረገው ጥሬ እቃ ጋር በማገናዘብ ልዩነቱ ሲኖረው ተገቢው የእርምት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ወጪ እቃን ዋጋ የመቆጣጠር ስልጣን የተሰጠው ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ሰለሆነ ከባንኩ በተላከ መረጃ መሰረት መስተንግዶ የሚሰጥ መሆኑንና የጎላ የዋጋ ልዩነት ሲኖር ጉዳዩ ሪፖርት እንደሚደረግ እና ለወደፊቱም ሀኔታውን ዋናው መ/ቤት እንዲያውቀው በማድረግ ከብሄራዊ ባንክ ጋር የጋራ መፍትሄ እንዲፈለግ ጥረት የሚደረግ መሆኑ እና በዲክላራሲዮን ቁጥር E-4051/10 የተስተናገዱት ላኪ ብሄራዊ ባንክ ባረጋገጠው ዋጋ መሰረት ሲሆን በወቅቱ ጉዳዩ ተደርሶበት እንዲታረም ጥያቄ አቅርበን ባንኩ በድጋሜ ማህተም በማድረግ ዋጋው ትክክል ስለመሆኑ በማረጋገጡ መስተንግዶ መሰጠቱ ተገልጿል፡፡

ይሁን እንጂ ድርጊቱ በአገር ላይ ሊያስከትል ከሚችለው ጉዳት አንጻር አፋጠኝ መፍትሄ የሚፈልግ በመሆኑም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

### 2.14 በኮንትሮባንድ የሚያዙ ንብረቶች አጠባበቅ በተመለከተ

ውርስ የተደረጉትም ሆነ ጊዜያዊ ርክክብ የተደረገባቸው ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች የኮንትሮባንድ እቃዎች በአግባቡ የሚጠበቁ መሆኑንና የተሽከርካሪዎቹም አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ተመዝግበው የተያዙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለፁት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

## I. የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

- ተሽከርካሪዎቹ የሚገኙበት ቦታ አጥር የሌለው በመሆኑ የተሽከርካሪዎቹ የተለያዩ አካሎች ለስርቆት የተጋለጡ መሆናቸው፣
- የአንድ ተሽከርካሪ ሞተር ከሻንሲው (ቦዲው) ተለያይቶ ለብቻው የሚገኝ መሆኑ፣
- ከ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ውርስ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ቢኖሩም እስከአሁን ግን ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑና አብዛኞቹ ተሽከርካሪዎች እየተበላሹ ያሉበት ሁኔታ መኖሩ፣
- ብዙ ተሽከርካሪዎች በሞ/265 ውርስ በሚደረጉበት ጊዜ የተሽከርካሪዎቹ ዋና አካል የሆኑ የሞተር እና ሻንሲ ቁጥራቸው ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

## II. አዳማ ቅ/ጽ/ቤት

- በኬላ ላይ  ከግለሰቦች የተወረሰው ንብረት (በሞዴል 270) ሙሉ በሙሉ ወደ መጋዘን (የእቃ መረከቢያ ሞዴል 265) ገቢ መደረጉ ሲጣራ በሞዴል 270  ቁጥር 887555 ኬላ ላይ የተወረሰ ንብረት በሞዴል 265 ቁጥር 317716 ወደ መጋዘን ገቢ ሲደረግ ከፊሉ ገቢ ሳይደረግ የቀረ መሆኑ፣
- በሽያጭ የተወገደና ወደመጋዘን የገባ እቃ የተለያየ ሆኖ መገኘቱ፣
- ንብረቱ ገቢ የተደረገበት፣እና በሽያጭ ሲወገድ ከንብረት ክፍል ወጪ የተደረገበት ደረሰኝ ቁጥር የማይጠቃቀስ መሆኑ፣
- እቃዎች ተይዘው ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ መሆኑ፣
- የእቃ መመዝገቢያ ቢን ካርድ ስርዝ ድልዝ የበዛበት መሆኑ፣
- የእቃዎች አቀማመጥ የተዘበራረቀ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## III. <u>ድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት</u>

በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ያልተወረሱ ወይም በፍርድ ሂደት ላይ ያሉ ዕቃዎች ወይም ንብረቶች ለመንገደኞች በሚሰጥ ደረሰኝ (ሞዴል 270) የሚያዙ ሲሆን፣ ጉዳዩ ተጣርቶ እቃው እንዲወረስ ሲደረግ በውርስ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 265) አማካኝነት እቃው ገቢ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በውርስ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 265) በቅድሚያ ከተያዘበት የመንገደኛ ደረሰኝ እና እንዲወረስ ከታዘዘበት ደብዳቤ ጋር የማይጠቃቀስ በመሆኑ ከመንገደኞች የተወረሱት በሙሉ በውርስ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ገቢ ደረሰኝ (በሞዴል 265) ገቢ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አልተቻለም ፡፡

- የተሽከርካሪዎቹ የተለያዩ ክፍሎች ተመዝግበው ባለመያዛቸውና ሊጠበቅ በሚችል ቦታ ባለመቀመጣቸው ለስርቆት ይጋለጣሉ፡፡ አሰራሩም ጥፋት ቢፈጸም የሚመለከተውን ሰራተኛ ወይም ግለሰብ ተጠያቂ ለማድረግ አያስችልም፡፡ እንዲሁም በወቅቱ ካልተወገዱ በቆይታ ብዛት ለብልሽት ተጋልጠው ጥቅም የማይሰጡ ይሆናሉ፡፡
- በመንገደኛ ደረሰኝ ገቢ የሆኑ እቃዎች ወደ ውርስ እንዲተላለፉ ውሳኔ ሲሰጥባቸው እቃዎቹ በውርስ ወይም በኮንትሮባንድ እቃ ደረሰኝ ገቢ ላይደረጉ ይችላሉ፡፡
- ተሽከርካሪዎቹ የሚገኙበት ቦታ ለስርቆት በማያጋልጥና ለጥበቃ በሚያመች ሁኔታ የተከለለ/የታጠረ መሆን እንዳለበት፤
- የተወረሱ ተሽከርካሪዎችም በወቅቱ ሊወገዱ እንደሚገባ፤
- የተሽከርካሪዎቹ ዋና ዋና አካላት የሆኑት ሞተርና ሻንሲ ቁጥሮች ተመዝግበው መያዝ እንዳለባቸው፤
- የንብረት አያያዙና አጠባበቁ ሊስተካከል እንደሚገባ፤
- በመንገደኛ ደረሰኝ ገቢ የተደረጉ እቃዎች እንዲወረሱ ሲደረግ የውርስ ወይም የኮንትሮባንድ እቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 265) ላይ በቅድሚያ ገቢ

የተደረገበት የመንገደኛ ደረሰኝ (ሞዴል 270) ቁጥር እና እቃዎች እንዲወረሱ የተጻፈ ደብዳቤ መጠቃቀስ እንዳለበት፤

ለየቅርንጫፍ መ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡ ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብለውታል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት ተሽከርካሪዎቹን ለማስወገድ የጨረታ ሰነድና ማስታዎቂያ ለመላክ በዝግጅት ላይ መሆኑን፣ እንዲሁም የተሽከርካሪዎች ሞተር ቁጥር እና ሻንሲ ቁጥር መመዝገቡን በተሰጠው ምላሽ ተገልጿል፡፡

የዋናው መ/ቤትም በዚሁ መሰረት የማሻሻያ እርምጃዎች የተወሰዱ መሆኑን መከታተል ይኖርበታል፡፡

## 2.15 በውርስ መጋዘን ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆዩ የተለያዩ እቃዎች እና ኬሚካሎች መገኘታቸው

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ዓ.ም አንቀጽ 62 እና በጉምሩክ አዋጅ መሰረት የመንግስት ንብረት በአግባቡ የመያዝ እና የመጠቀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የማስወገድ ተግባር መከናወን እንዳለበት ይገልፃል፡፡ በዚም መሰረት መፈጸሙን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ

1. የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት

   በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በውርስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ እቃዎች አያያዝ በናሙና ሲታይ የተለያዩ ንብረቶችና እና ኬሚካሎች ሳይወገዱ ከ1997 ዓ.ም ጀምሮ በውርስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ ታዉቋል፡፡ ቅ/ጽ//ቤቱ ለሚመለከተው መ/ቤት (ጨረር መከላከል) ጉዳዩን ያሳወቀ ሲሆን ኬሚካሉ ሊወገድ የሚችለው በውጭ አገር ነው በመባሉ እስከአሁን ያልተወገዱ መሆኑን ተገልጿል፡፡

2. <u>የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት</u>

የምግብ ውጤቶች እና መድሐኒቶች ለረጅም ጊዜ በመጋዘን ውስጥ የቆዩና በአዋጁ መሰረት ተገቢው እርምጃ ሳይወሰድ ከስድስት ወር እስከ አራት አመት የቆዩ መሆኑ፣

3. <u>የድሬዳዋ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- በቅ/ጽ/ቤቱ በመጋዘን ውስጥ ሳይወገዱ ብዙ ጊዜ የሆናቸውና ጊዜው ያለፈባቸው ምግብ ነክ የሆኑ እቃዎች ተገኝተዋል፡፡
- ብዙ ዓመት የሆናቸው መኪናዎች ባለመሸጣቸው ለብልሽት ተዳርገዋል፡፡
- CARBARYL የተባለ የነፍሣት ማጥፊያ መርዛማ መድሃኒት በአንድ መጋዘን ውስጥ ከምግብ ነክ እና ሌሎች ዕቃዎች ጋር ተቀምጠው ተገኝተዋል፡፡

እቃዎች በውርስ መጋዘን ለረጅም ጊዜ ሲቆዩ ለብልሽት ስለሚዳረጉ መንግሥት ከሽያጭ ማግኘት ያለበትን ገቢ ያሳጣል፡፡ እንዲሁም ቅ/ጽ/ቤቱ ከሚመለከታቸው መ/ቤቶች ጋር ኬሚካሎቹ ስለሚወገዱበት ሁኔታ የተፃፃፈ ቢሆንም ለረጅም ጊዜ በቆዩ ቁጥር በመጋዘን ሠራተኞች እና በአካባቢው ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡

እቃዎች ለብልሽት ከመዳረጋቸው በፊት ተሸጠው ለመንግሥት ገቢ የሚያስገኙበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ ኬሚካሎች፣ መድሀኒቶች እና የምግብ ውጤቶች በሰራተኞችና በአካባቢው ላይ ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ሊወገዱ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ያልተሸጡ እቃዎች ቀደም ካለ ጊዜ ጀምሮ በሐራጅ ሽያጭ ሳይሸጡ ሲንከባለሉ የመጡ እንደሆኑና ጽ/ቤቱ ከጅንአድ ጋር ባለው ውል መሠረት ዕቃዎችን የሚያስረክብ ቢሆንም፣ ጅንአድ እየመረጠ የሚረከብ በመሆኑ ክምችቱ እየበዛ መምጣቱን፤
- የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት የምግብ ውጤቶቹንና መድሐኒቶቹን በተመለከተ የመድሐኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን

ባለሙያ በቅድሚያ መድሐኒቶቹን በመመልከት ስላወጋገዱ ፍቃድ እንዲሰጥበት በደብዳቤ በተደጋጋሚ ጥያቄ ቢያቀርቡም ምላሽ ሊሰጥ ባለማግኘቱ ማስወገድ አለመቻሉን፣

- የድሬዋ ቅ/ጽ/ቤት ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በመነጋገር መኪናዎችን በጨረታ ለመሸጥ ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

ይሁን እንጂ ጅንአድ ሊረከባቸው ያልቻሉት ዕቃዎች አስቀድሞ ከታወቀ እቃዎች በመጋዘን ውስጥ ሳይቆዩ በጨረታ ማስወገድ ይቻል የነበረ ቢሆንም ይህ ሳይደረግ መቆየቱ ለጉዳዩ ትኩረት ያለመሰጠቱን የሚያመላክት በመሆኑ ሊታረም ይገባል፡፡ መድሀኒቶቹንም በተመለከተ የመድሐኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሀላፊዎችን በግንባር በማነጋገር ችግሩ መፍትሄ እንዲያገኝ ጥረቱ ሊቀጥል ይገባል፡፡

## 2.16 የተሰብሣቢ ሂሣብን በተመለከተ

በቁጥር H-42-1/650/691 በቀን 04/02/01 በተላለፈ የውስጥ መመሪያ መሰረት በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢው የቁጥጥር ሥርዓት የተዘረጋና ከድርጅቶች የሚፈለገውም ሂሳብ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ክትትል የሚደረግበት ሥርዓት መዘርጋቱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከዚህ በታች የተገለፁት ሁኔታዎች ታይተዋል፡፡

### 2.16.1 የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት

- ሊሰበሰብ የሚገባው ብር 4,823,683.36 ውዝፍ ሂሣብ የተገኘ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ ብር 1,064,639.40 ሳይሰበሰብ ከአንድ ዓመት በላይ የቆየ መሆኑ፣ ብር 2,703,984.86 ደግሞ ከ6 ወር እስከ አንድ ዓመት ሳይሰበሰብ የቆየ መሆኑ በኦዲቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሣቦች አያያዝ ቡድን ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ ለክትትል እንዲያመች በየ15 ቀኑ ለደንበኞች አገልግሎት

የሥራ ሂደት ሪፖርት ማድረግ የሚጠበቅበት ቢሆንም የደንበኞች አገልግሎት ሪፖርት የማይደርሰው መሆኑ፣

- የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሣቦች አያያዝ ቡድን ተሰብሳቢ (ቀሪ) ሂሣብን አስመልክቶ የተሟላ እና ወቅታዊ መረጃ የማይዝ በመሆኑ፣

በዚህም ምክንያት የውዝፍ አሰባሰብ የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት እና የተዘረጋው የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት አስተማማኝ መረጃን ሊሰጥ የማይችል መሆኑ ታውቋል፡፡

### 2.16.2 የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማስተናገጃ ቅ/ጽ/ቤት

ተሰብሳቢ ሂሳብ በሂሳብ ክፍሉ ተቀጽላ መዝገብ ተከፍቶ በየድርጅቶቹ ስም ተመዝግቦ ያልተያዘ በመሆኑ የቅ/ጽ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሒሳብ ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅ መሆኑ እና ለመክፈል ፈቃደኛ ያልሆኑ ድርጅቶች ተለይተው ህጋዊ እርምጃ ለሚወስደው የስራ ክፍል ያልተላለፈ መሆኑ ታውቋል፡፡

### 2.16.3 የአዳማ ቅ/ጽ/ቤት

የአጣሪ እና ውሣኔ ሰጪ ቡድን በኩል በተሰብባቢነት የተያዘው ሂሳብ ብር 9,052,520.40 እንዲሁም በድህረ ዕቃ አወጣጥ ምርመራ /PCA/ ቡድን በኩል የተገኘ ከአስመጭዎች ሊሰበሰብ የሚገባው ሂሳብ ብር 58,809,685.43 በድምሩ ብር 67,862,205.83 ያልተሰበሰበ ገቢ የተገኘ ሲሆን፣ ሂሳቡንም በገቢ ሒሳብ ክፍል በኩል ተመዝግቦ ያልተያዘና በደንበኞች አገልግሎት የስራ ሂደትም በኩል ክትትል የማይደረግበት መሆኑ ታውቋል፡፡

በገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሣቦች ቡድን በኩል የተጣራ መረጃ አለመያዙ ጽ/ቤቱ በተሰብሳቢነት የሚፈልገውን የሂሣብ መጠን በትክክል ለማወቅና ክትትል አድርጎም ሂሣቡን ለመሰብሰብ አዳጋች ይሆንበታል፡፡

ቀሪ ሂሣብ ወቅቱን ጠብቀው በማይከፍሉት ላይ መስተንግዶ እንዳያገኙ ከሲስተም የሚያግድበት አሠራር በቅ/ጽ/ቤቱ ያለ በመሆኑ ይህንኑ አሰራር አጠናክሮ እንዲታገዱ

የተወሰነባቸው ድርጅቶች በተግባር መታገዳቸውን ማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋትና አፈፃፀሙን መከታተል ያስፈልጋል፡፡

የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሣቦች ቡድን ከገንዘብ ሰብሳቢዎች እና ከደንበኞች አገልግሎት ጋር ቅንጅት በመፍጠር የሚፈለግባቸውን ቀሪ ሂሣብ ባልከፈሉት ድርጅቶች ላይ ወቅታዊ እርምጃ መውሰድ እንዲቻል፣ በማኔጅመንቱ በተወሰነው መሠረት በየ15 ቀኑ የተጣራ መረጃ ለደንበኞች አገልግሎት ማስተላለፍ ቀሪ ሂሣቡ በወቅቱ እንዲሰበሰብ ማድረግ ተገቢ እንደሆነ አሳስበናል፡

- የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ብር 1,353,229.47 የተሰበሰበ መሆኑንና ባልከፈሉት ላይ መስተንግዶ እንዳያገኙ ከሲስተም የታገዱ መሆኑንና ዝርዝራቸዉም በቅ/ጽ/ቤቱ ለሚገኘዉ የህግ ማስከበር የስራ ሂደት የተላለፈ መሆኑን በተሰጠው ምላሽ ተገልጿል፡፡
- የአዲስ አበባ ንግድ እቃዎች ማ/ጽ/ቤት ከጣቢያው ስፋትና ከተገልጋዩ ብዛት አኳያ በማንዋል መስራት ከቡድኑ አቅም በላይ በመሆኑ የገቢ አሰባሰብና የዋስትና ሂሳቦች ቡድን ከአሲኩዳ ሲስተም ባለመገናኘቱ ምክንያት መስራት አለመቻሉን ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ በቀሪ ሂሳብ ላይ አስፈላጊውን ክትትል አለማድረግ መንግስት በወቅቱ ማግኘት ያለበትን ገቢ የሚያሳጣው በመሆኑ ቅ/ጽ/ቤቱ ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ አሰራሩን ማስተካከልና ተሰብሳቢውም ሂሳብ እንዲሰበሰብ መደረግ አለበት፡፡

## 2.17 ልዩ ልዩ

የቅ/ጽ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ፣ የማስረጃዎች አጠባበቅ እና አያያዝ ሲጣራ ቀጥሎ የተመለከቱት ችግሮች ተገኝተዋል፡

### የአገር ውስጥ ገቢን በተመለከተ

### 2.17.1 የገንዘብ ትልልፍ ሂደትን በተመለከተ

በግንቦት 25 2000 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር አመ3/17/28/5 ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በተፃፈ ደብዳቤ መሰረት፤ ለቼክ መመንዘሪያ የሚከፈተው የባንክ ሂሣብ ወዲያውኑ ቼኩን መንዝሮ የክልልን ወደ አደራ የባንክ ሂሣብ፤ የፌዴራሉን ደግሞ ወደ መደበኛው የፌዴራል ገቢ የባንክ

ሂሣብ በማስተላለፍ የየዕለቱ የመመንዘሪያ ባንክ ሂሳብ ሚዛን ዜሮ መሆን እንዳለበት እና ምንም ዓይነት ገንዘብ ሊቀመጥበት እንደማይገባ ይገልፃል፡፡

ከዚህ አንጻር የቅርንጫፍ ጽ/ቤት አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ

- የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት በየሣምቱ የሚተላለፍ በመሆኑ ብር 676,020.70፣
- የምሥራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በየወሩ የሚተላለፍ በመሆኑ ብር 807,384.99
- የባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት በየወሩ የሚተላለፍ በመሆኑ ብር 109,560.75

በድምሩ ብር 1,592,966.44 የተሰበሰበው ገቢ በወቅቱ ለትሬዠሪ ዝውውር ባለመደረጉ መንግስትን ለተጨማሪ የወለድ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

መንግስት ወጪውን ለመሸፈን፣ የተሰበሰበ ገቢ እያለ ብድር ሊበደር ይችላል ይህም ለተጨማሪ የወለድ ክፍያ ይዳርጋል፡፡

መንግስት ወጪን ለመሸፈን በዋናነት የሚጠቀመው ከአገር ውስጥ በሚሰበስበው ገቢ በመሆኑ፣ የተሰበሰበው ገቢ በወቅቱ ፈሰስ ካልተደረገ መንግስት ወጪውን ለመሸፈን የአጭር ጊዜ ብድሮችን ለመበደር ይገደዳል፡፡ ይህም ለተጨማሪ የወለድ ክፍያ የሚዳርግ በመሆኑ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሰበሰበውን ገቢ በወቅቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲተላለፍ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ሶስቱም ቅ/ጽ/ቤቶች የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብለውታል፡፡ በዚሁ መሰረት የከፍተኛ ግብር ከፋዮች እና የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት የየ3 ቀኑን ገቢ በ4ኛው ቀን ወደ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ መጀመራቸውን በተሰጠው ምላሽ ገልጸል፡፡

2.17.2 <u>ግብርና ታክስ ገቢ ለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበለት</u>

የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ ቅፅ ገቢ ከተሰበሰበ በኃላ ወደ ግብር ከፋይ ፋይል በሚተላለፍበት ወይም ርክክብ በሚደረግበት ወቅት በተከሰተ ችግር ምክንያት የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፤

- በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 52,077,955.42፣
- በምሥራቅ አዲስ አባበ ቅ/ጽ/ቤት ብር 2,790,840.15፣
- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,499,623.52፣
- በምእራብ አዲስ አበባ የ9 /ዘጠኝ/ ግብር ከፋዮች ሂሳብ ግብር ከፋዮች ያቀረቡት ማስረጃ በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ፣

የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የተሰበሰበው ገቢ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ እንዲሁም በዶክመንቴሽ የቁጥጥር ሥርዓት ደካማ መሆኑን ያሣያል፡፡

የገቢ ደረሰኝ እና የግብር ማሣወቂያ ቅፅ አስፈላጊው ሥራ ከተጠናቀቀ በኃላ የግብር ከፋዩ ማህደር ወደ ሚገኝበት ክፍል ሲተላለፍ የርክክብ ሂደቱን በማስረጃ በማስደገፍ መተላለፍ እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

ቅ/ጽ/ቤቱ በኦዲቱ ግኝት ወቅት የተጠቀሱት ሰነዶች ጠፍተው ሣይሆን በአሰራር ቅብብሎሽ ወቅት የሥራ ኡደታቸው ባለማጠናቀቃቸውና መዝገብ ቤት ባለመድረሳቸው፣ የቅ/ጽ/ቤቱ ግብር ከፋዮች በአዲስ መልክ መደልደላቸውና የሰነዶቹ ከአንድ ፋይል ወደ ሌላ ፋይል በመቀየራቸው ምክንያት የመጣ መሆኑ ገልፀዋል፡፡

ለወደፊቱም በተሰጠው ገንቢ አስተያየት መሰረትም ቅ/ጽ/ቤቱ አሰራሩን ይበልጥ ፈትሾና መርምሮ በተጠያቂነት ላይ የተመሰረተ የተጠናከረ የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት ለመዘርጋት ጥረት በማድረግ ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም ችግሩን ለመፍታት እየተደረገ ያለውን ጥረትን አጠናክሮ በመቀጠል ማስረጃዎች በአግባቡ የሚቀመጡበት ሁኔታ መፈጠር ይገባል፡፡

2.17.3 <u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብርና ታክስ</u>

በታክስና ግብር አዋጅ መሰረት ባለስልጣኑ ተጨማሪ የታክስ ውሣኔ የሰጠ እና የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው ማስታወቂያው በደረሰው በ30 ቀን ውስጥ እንዲከፍል ወይም በውሣኔው ላይ ቅሬታ ካለው ይግባኝ ማለት ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በግብር አወሣሰንና በኦዲት ውዝፍ ግብር፣ ወለድ እና ቅጣት እንዳለባቸው የግብር አወሳሰን ከተሰራላቸው ውስጥ

- ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 193,627,712.36፣
- ምሥራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ብር 5,296,214.51 እና
- ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 13,759,780.52

ውዝፍ ያልተሰበሰበ ግብር በድምሩ ብር 212,683,707.39 አቤቱታ ቀርቦ በወቅቱ ምላሽ ባለማግኘቱ ገቢ ያልሆነ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በአቤቱታ አፈታት ላይ የተዘረጋው ሥርዓት በአፋጣኝ ለተገልጋዩ ምላሽ ለመስጠት የማያስችል እንዲሁም በወቅቱ ውሣኔ በመስጠት ለመንግስት ገቢ መሆን ያለበት ገንዘብ እንዳይገባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ግብር ከፋዩ የሚያቀርበው አቤቱታ ምላሽ የሚሰጥበት ስርዓትን በማሻሻል በአፋጣኝ ውሣኔ በመስጠት ገቢ መሆን ያለበት ውዝፍ ዕዳ ለመንግስት በወቅቱ ገቢ እንዲሆን የሚያስችል መሆን እንዳለበት በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

<u>የማኔጅመንቱ አስተያየት</u>

- የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት እና የምስራቅ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር ተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የተቀበለው ሲሆን፣ በአቤቱታ አጣሪ እጅ የተወዘፉትን ቅሬታዎች በአፋጣኝ ለማጠናቀቅ ተጨማሪ ኮሚቴ የሚመድብ መሆኑን፣ ከደብረ ብርሃን ብርድ ልብስ ፋብሪካ የሚፈለገውን ውዝፍ ዕዳ በተመለከተ ዕዳውን ከኢትዮጵያ ባለአደራ ቦርድ ድርጅት ለመሰብስብ ጥረት የሚደረግ መሆኑን፣

- የባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት በተሰጠውን አስተያየት መሰረት ብር 13,749,613.86 ከጥቁር አባይ ትራንስፖርት ድርጅት በአሁኑ ሰዓት ውዝፍ ዕዳው ሙሉ በሙሉ የተሰበሰበ ሲሆን ቀሪውን ለመሰብሰብ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በመሆኑም ችግሩን ለመፍታት እየተደረገ ያለውን ጥረት አጠናክሮ በመቀጠል መሰብሰብ ሚገባውን የመንግስት ገቢ በወቅቱ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

## 2.17.4 የግብርና ታክስ በወቅቱ ያላሣወቁ ግብር ከፋዮች መቀጫና ወለድ ያልተሰላ መሆኑ

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 74 መሰረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግብር ገቢ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ዘግይቶ በተሰበሰበ የደመወዝ ገቢ ግብር እና የቅድመ ታክስ በድምሩ ብር 3,033,014.15 በወቅቱ ገቢ ባላደረጉ ግብር ከፋዮች ላይ ቅጣትም ሆነ ወለድ ያልተጣለባቸው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ለመንግስት ገቢ መሆን ያለበት ገንዘብ በወቅቱ እንዳይገባ እንዲሁም መንግስትን ለተጨማሪ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

መንግስት ወጪን ለመሸፈን በዋናነት የሚጠቀመው ከአገር ውስጥ ከሚሰበስበው ገቢ በመሆኑና ወጪን መሸፈን ሲያቅተው የአገር ውስጥ ብድር ለመበደር የሚገደድ በመሆኑ ግብር በወቅቱ በማይከፍሉት ላይ ተገቢው ክትትል እየተደረገ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ በመሆኑም ገቢው ለዘገየበት ጊዜ በአዋጁ መሰረት ወለድ እንዲሁም መቀጫ እንዲከፍሉ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

ቅ/ጽ/ቤቱ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

## 2.17.5 የታክስ ተቀናሽ ቅፅ ሣይቀርብ ተቀናሽ የተደረገ ተጨማሪ እሴት ታክስ

ግብር ከፋዮች በየወሩ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲያስታውቁ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ማስታወቂያ በማቅረብ መስተናገዳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ግብር ከፋዮች በግብዓት ላይ የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተቀናሽ ማስታወቂያ ሳያቀርቡ

ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ላይ ተቀናሽ የተደረገላቸው ግብር ከፋዮች ተገኝተዋል፡፡

የተቀናሽ ሂሣብ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

በመመሪያው መሰረት ማናቸውም የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋይ በየወሩ ከሚያቀርቡት ማስታወቂያ ጋር በአንድነት የታክስ ተቀናሽ ቅፅ ሞልተው እንዲያቀርቡ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

የባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ተሰጠውን የማሻሻያ ሀሣብ ተቀብሎታል፡፡ በዚህም መሰረት የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ላይ መሆኑ ተገልጿል፡፡

### 2.17.6 <u>ግብርና ታክስ በወቅቱ ያላሣወቁ ግብር ከፋዮችን በተመለከተ</u>

ኤክሳይዝ ታክስ፣ በተጨማሪ እሴት ታክስ እና በገቢ ግብር አዋጆች መሰረት ግብር ከፋዮች ታክስ በሚገባ ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሚሆነውን መረጃን የሚያሣይ መግለጫ በየ30 ቀኑ የሚያቀርቡ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡

- በምሥራቅ አዲስ አባባ ቅ/ጽ/ቤት 12 ግብር ከፋች የኤክሣይዝ ታክስ፣
- በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት 4 ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ከፋዮች፣

በአዋጁ መሰረት ሪፖርት ያላደረጉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

በወቅቱ ያላሣወቁ ግብር ከፋዮች ክትትል የሚደረግበት የቁጥጥር ሥርዓት ደካማ በመሆኑ ምክንያት ለመንግስት ገቢ መሆን የሚገባው ገንዘብ በወቅቱ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

በኤክሣይስ ታክስ አዋጅ ቁጥር 307/1995 አንቀፅ 8 (ለ) እና በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀፅ 26 (2) እና በገቢ ግብር አዋጅ መሰረት ሪፖርት ያላቀረቡ ግብር ከፋዮችን በወቅቱ በመለየት እና

ክትትሉን በማጠናከር ሪፖርት እንዲያቀርቡ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ቅ/ጽ/ቤቶቹ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብለውታል፡፡ በዚሁ መሰረት ተገቢው እርምጃ እንደሚወሰድ ተገልጿል፡፡

### 2.17.7 <u>የንግድ እቃዎች የክምችት ሂሳብ መነሻ ከወጪ ቀሪ ያለአግባብ ከፍ እንዲል በመደረጉ ታክስ የሚሰላበት ገቢ ዝቅ ብሎ ስለመገኘቱ</u>

በምእራብ አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤት በሂሳብ መዝገብ አያያዝና አመዘጋገብ መርህ መሰረት በሂሳብ ዓመቱ መጨረሻ በክምችት ያሉ ያልተሸጡ የንግድ እቃዎች (Ending Inventory) ከወጪ ቀሪ ወደ ቀጣዩ አመት የንግድ እቃዎች ክምችት መነሻ (Beginning Inventory) ከወጪ ቀሪ በትክክል የዞረ መሆኑ ሲጣራ ሁለት ድርጅቶች ካለፈው አመት የዞረውን የክምችት ሂሳብ ከወጪ ቀሪ በትርፍና ኪሳራ መግለጫ ላይ  አስበልጠው በመያዛቸው ምክንያት ታክስ የሚሰላበት ገቢ በብር 581,753.86 ዝቅ ያለ በመሆኑ ሊሰበሰብ የሚገባው የንግድ ትርፍ ገቢ በዚሁ መሰረት ዝቅ የሚል መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣ ይችላል፡፡ አሰራሩ ግብርን ለመደበቅ የተደረገ ሊሆን ይችላል፡፡

በንግድ ትርፍ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 2/መ/ እና /ሠ/ መሰረት ትክክለኛ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ መቅረቡ እየተረጋገጠ ግብር መሰብሰብ ያለበት ሲሆን ትክክለኛ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ያላቀረቡት የንግድ ድርጅቶች ያልከፈሉት ግብር፣ ወለዱ እና መቀጫው ተሰልቶ ሂሳቡ ገቢ መደረግ እንዳለበት በላነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

የማጣራት ስራው የሚከናወነው በታክስ ኦዲተሮች በመሆኑ በኦዲት ወቅት ችግሩ ሊደርበት ይችል ነበር በማለት ተገልጿል፡፡ የታክስ ኦዲሮች ስህተቱን ሊደርሱበት ይችላሉ በሚል የሂሳብ መግለጫ ሳይጣራ ተቀባይነት የሚገኝ ከሆነ ፣ የታክስ ኦዲተሮ ሽፋን ደግሞ አነስተኛ ከመሆኑ አንጻር ስህተቱ ሳይደረስበት የመቅረት እድሉ የሰፋ ነው፡፡ በመሆኑም አሰራሩ ጎላ ያሉ ችግሮችን ለመለየት በሚያስችል መልኩ ሊስተካከል ይገባል፡፡

# 3. ወጪ ሂሣብ በተመለከተ

## 3.1 በዋና መ/ቤት

### 3.1.1 የሂሣብ ማስተካከያ ሲሰራ የምዝገባ ማዘዣ የማይዘጋጅ መሆኑ

የሂሳብ እንቅስቃሴ ላይ ምዝገባ ለማከናወን በቅድሚያ የምዝገባ ማዘዣ ተዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ትክክለኛነቱ እየተረጋገጠ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በባለሥልጣን መ/ቤቱ የሂሣብ ማስተካከያ ሲደረግ ከታች በተገለፀው መሰረት የምዝገባ ማዘዣ /JV/ ሣይዘጋጅ በመዝገብ ላይ የምዝገባ ማዘዣ ቁጥር ተጠቅሶ ተመዝግቦ ተግኝቷል፡-

| ቀን | JV ሣይዘጋጅ በመዝገብ የተገኘ | የሂሣብ መደብ | የገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|
| 14/04/2002 | 064442 | 6243 | 18,215.87 |
| 01/07/2002 | 064739 | 6241 | 8,000.00 |
| 20/07/2002 | 064877 | 6241 | 6,970.15 |
| 28/11/2001 | 37060 | 6217 | 37,836.00 |
| 23/10/2002 | 11281 | 6213 | 103,438.37 |
| 17/10/2002 | 11236 | 6217 | 30,000.00 |
| 13/12/2001 | 37134 | 6256 | 181,802.60 |
| 26/02/2002 | 073383 | 6241 | 13,720.00 |

የባለሥልጣኑ የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በሂሣብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ የሚመዘገብ ሂሣብ አስፈላጊው የምዝገባ ማዘዣ እየተዘጋጀ በሚመለከተው አካል እየተረጋገጠ መመዝገብ ይገባዋል፡፡ በመሆኑም የሂሣብ ማስተካከያ ሲደረግ የምዝገባ ማዘዣ በማዘጋጀት ማስተካከያው ያስፈለገበት ምክንያት በመግለፅ እንዲሁም ትክክለኛነቱ በማረጋገጥ ሊከናወን እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ ተቀብሎታል፡፡

### 3.1.2 የችሮታ ጊዜ ተከፋይ ሂሣብን በተመለከተ

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/1989 አንቀፅ 27 መሰረት የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለታዘዙና ለተረከባቸው ዕቃዎች፣ ለተሰጡ አገልግሎቶች የበጀት ዓመቱ ከማለቁ በፊት ለቀረበለት የክፍያ ጥያቄ፣ እስከ ሀምሌ 30 ማናቸውም የክፍያ መከፈል ያለበት ሲሆን በዚሁ መሰረት የችሮታ ጊዜ ክፍያዎች አዋጁን የተከተለው የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ከ2000 በጀት ዓመት የዞረ ብር 3,864,313.29 የችሮታ ጊዜ ተከፋይ እስከአሁን ድረስ ክፍያ አለመፈጸሙ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም አገልግሎት ወይም ዕቃው ለመ/ቤቱ አገልግሎት የዋለ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ላልተገኘ አገልግሎት ወይም ተገዝቶ ለመ/ቤቱ አገልግሎት ላልዋለ እቃ ሂሳቡ ያለአግባብ ሊመዘገብ ይችላል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱም ያለአግባብ ባለእዳ ያደርጋል፡፡

ለችሮታ ጊዜ ክፍያ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ገንዘቡን በጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ወስጥ እንደሚለቅና ባለስልጣን መ/ቤቱም በዚያው ወር ውስጥ ክፍያውን መፈጸም ነበረበት፡፡ ሆኖም ሂሳቡ ሳይከፈል ከ2 አመት በላይ የሆነውና አገልግሎት ሰጪው አካልም የክፍያ ጥያቄ ያላቀረበ በመሆኑ ሂሳቡ ተከፋይ ሳይሆን የምዝገባ ስህተት ሊሆን ስለሚችል ሁኔታው ተጣርቶ የሂሳብ ማስተካከያ ሊደረግበት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

ችግሩ የተፈጠረው ከሶስቱ መ/ቤቶች ውህደት በፊት ከቀድሞው የጉምሩክ ባለስልጣን የዞረ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑንና በቀጣይ በዝርዝር ተጣርቶ ተገበው የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወሰድ ገልጸዋል፡፡ ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት በአፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

### 4.1. ትክክለኛ የሂሳብ ሚዛን የማያሳዩ የሂሳብ መደቦች

በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማእቀፍ መሰረት የሂሳብ ምዝገባ የሚከናዎን መሆኑ እና የሂሳብ ቋቶችም ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን የሚሳዩ መሆኑን ለማጣራት

ኦዲት ሲደረግ በዋና መ/ቤት የተጣራ ሀብት የክሬዲት ሚዛን ማሳየት ሲገባው የዴቢት ሚዛን ብር 2,083,680.30 የሚያሳይ መሆኑ እና የደመወዝ ተከፋይ ደግሞ የክሬዲት ሚዛን ማሳየት ሲገባው የዴቢት ሚዛን ብር 174,093.47 የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል፡፡ እንዲሁም በአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማ/ቅ/ቤት መደበኛ ሂሣብ ላይ ተሰብሣቢና የባንክ ሂሣብ የደቢት ሚዛን ማሣየት ሲገባቸው የክሬዲት ሚዛን በብር 10,565.48 እና በብር 2,469.84 እንዲሁም የተጣራ ሃብት ክሬዲት ሚዛን ማሳየት ሲገባው ደቢት ሚዛን በብር 159,729.99 የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል፡፡

የባለሥልጣኑ የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ትክክለኛውን መረጃ እንዳይሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የሒሳብ ቋቶች ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ከሆነ በተላያዩ የሂሳብ አርእስቶች ላይ የሂሳብ ምዝገባ ስህተት መኖሩ አመላካች በመሆኑ ስህተቱ የተፈጠረበትን በጀት ዓመትና ወር በመለየት ለተፈጠረው ስህተት ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባና ለወደፊቱም ስህተቱ በተፈጠረ ጊዜ የሒሳብ እንቅስቃሴው ሳይበዛና ከበጀት ዓመቱ ሳይዘል ወዲያው ማስተካከያ ሊደረግለት የሚገባ መሆኑን አሳስበናል፡፡

የዋና መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጠውን የማሻሻያ ሀሳብ የተቀበለው ሲሆን በቀጣይ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ሂሳብ የሚስተካከል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ዕቃዎች ማ/ቅ/ጽ/ቤት ስራ አመራር ችግሩ ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ እየዞረ የመጣ በመሆኑ አጣርቶ ምላሽ ለመስጠት በቂ ጊዜ የሚፈልግ በመሆኑ በቀጣይ ሂሣቡን በማጣራት ምላሽ የሚሰጡ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

## 4.2. <u>ለተቋሞችና ድርጅቶች ዕርዳታ መዋጮና ድጎማ በሚል የሂሳብ መደብ ተመዝግቦ ስለተገኘው የቀረጥና ታክስ ተመላሽ ሂሣብ</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 66 መሰረት በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ሲደረግ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ መሰረት መመዝገቡን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በ2002 በጀት አመት መላሽ የተደረገ ሂሳብ

ለተቋሞችና ድርጅቶች ዕርዳታ መዋጮና ድጎማ በሚል የሂሳብ መደብ (6412) ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም በዚህ የሂሳብ መደብ የተመዘገበው ሂሳብ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያለመመዝገቡና ትክክለኛውን መረጃ የማይሰጥ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለግብር ከፋዮች የተመለሰው ገንዘብ የራሳቸው ሆኖ ሳለ እርዳታ ወይም ድጎማ እንደተደረገላቸው አድርጎ መመዝገብ አጠቃላይ በፌዴራል መንግስት ደረጃ የተሰጠን የድጋፍና ድጎማ ሂሳብ የተዛባ ያደርገዋል፡፡

ተመላሹ ሂሰብ በሂሳብ መደብ 6419 ቢመዘገብ ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲያሳይ ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም አሰራሩ በዚህ መልኩ ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የስራ አመራሩ የተሰጠውን የማሻሻያ ሃሳብ ተቀብሎታል፡፡ በዚህም መሰረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር እርምጃ እንደሚወሰድ ገልጸዋል፡፡

4.3. <u>የንብረት አያያዝንና አጠባበቅን በተመለከተ</u>

በመንግሥት ንብረት መመሪያ ቁጥር 6/1991 አንቀጽ7 (1) እና 19 መሠረት ቋሚም ሆነ አላቂ እቃ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ቆጠራ እየተካሄደ ከንብረት መዝገብ ጋር መገናዘብ መገናዘቡንና ልዩነትም ካለ የማስተካከያ እርምጃ መወሰዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ በአዳማ ቅ/ጽ/ቤት፡

- የቋሚ እና አላቂ እቃቆች መዝገብ ያላቋቋመ መሆኑ፣
- አንድ ፎርክሊፍት መኪና፣ የሞተር ቁልፍ እና የጎማ መፍቻ፣ ለበከልቻ ትራንስፖርት በነፃ ተሰጥቶ የተገኘ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

የንብረት መዝገብ ካልተቋቋመ ንብረቶች ቢጠፉ አይታወቅም ሰራተኞችንም ተጠያቂ ማድረግ አይቻልም፡፡ ሊወገዱ የሚጋባቸው ንብረቶችም በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሰረት ካልተወገዱ የመንግስት ንብረት ያለአግባብ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

የቋሚና አላቂ እቃዎች መዝገብ እንዲቋቋም በማድረግ በየበጀት አመቱ መጨረሻ ቆጠራ ተደርጎ ከወጪ ቀሪው የሚገናዘብበት አሰራር ሊዘረጋ ይገባል፡፡ የንብረት አወጋገድ መመሪያን ሳይከትል ለበከልቻ ትራንስፖርት አክሲዮን ማህበር የተሰጠውም ፎርክሊፍት ተመላሽ እንዲሆን በማድረግ ንብረቱ ለጽ/ቤቱ አስፈላጊ ካልሆ በመመሪያው መሰረት ሊወገድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

የቋሚና አላቂ አቃዎችን አስመልክቶ የተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ ቅ/ጽ/ቤቱ የተቀበለው ሲሆን፣ ፎርክሊፍቱ በተመለከተ ለዋና መ/ቤት በደብዳቤ አሳውቀናል የተባለ ቢሆንም ደብዳቤው አልቀረበልንም፡፡

በመሆኑም የንብረቱ ጉዳይ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት የሚመለስበት ወይም በሽያጭ መልክ ወደ ድርጅት የሚተላለፍበት መንገድ መፈለግ አለበት፡

# ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

## የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር

## የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሣቦች

የበጀት ዓመቱ ኦዲት ዝርዝር የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ፣

- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማይደረግና በሂሣብ ክፍል ከሚገኘው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ሌጀር ጋር የማይመዛዘን መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

  ጥሬ ገንዘብ በተወሰነ ጊዜ ቆጠራ ለማድረግ የጥሬ ገንዘብ ሌጀር ከሚያሳየው ከወጪ ቀሪ ጋር የማይታረቅ ከሆነ ለጥሬ ገንዘብ ጉድለትና ለምዝበራ ይጋለጣል፡፡

  የፋይናንስ ክፍሉ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ እያደረገ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ እንዲያዘጋጅ ጥብቅ መመሪያ ሊደርሰው ይገባል፡፡

የወጪ ሂሣብ፣

- ብር 17,162.03 የሚያወጡ ወጪዎች በበላይ ኃላፊ ሳይፀድቁ በወጪ ሂሣብ መያዛቸው ተረጋግጧል፡፡

  ውሎ አበል (6231)ብር 2,244.02 የተሽከርካሪ እድሳትና ጥገና (6241) 9,918.01ስልክ (6258) 1,800.00ትራንስፖርት (6232) 3,200.00

  ወጪ በሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ፀድቆ ክፍያ የማይፈፀም ከሆነ የገንዘብ ቁጥጥር ስርአቱን ከማላላቱ ባሻገር ወጪውን ተአማኒ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

  በፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ወጪውን የማፅደቅ ኃላፊነት ባለው ሰው መፈረም ይኖርበታል፣ ስለሆነም ለወደፊቱ እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይከሰት ጥብቅ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

- ለተሽከርካሪዎች እድሳትና ጥገና በሚል ለኢትዮ ኒፓን አ.ማ ብር 65,000.00 ወጪ የተደረገው የቅድሚያ ክፍያ በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በወጪ አርዕስት ተይዞ

የተገኘና መሰብሰብ የሚገባው ብር 7,681.00 ያልተወራረደና ያልተመዘገበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የተሰብሳቢ ሂሣቦች በወጪ የሂሣብ መደብ መያዛቸው አንዱን የሂሣብ መደብ ከፍ (Overstate) ሌላውን ዝቅ (Understate) እንዲል ከማድረጉ ባሻገር መወራረድ የነበረባቸው ተመላሽ ሂሣቦች ባግባቡ እንዳይወራረዱ ያደርጋል፡፡

ማንኛውም ሂሣብ መንግስት ባስቀመጠው የሂሣብ አያያዝ ስርአት መቀመጥ ይኖርበታል፤ በመሆኑም ለተጠቀሰው ሂሣብ ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

- ለቢሮ ዕቃ ግዥ ወጪ ከተደረገው ጠቅላላ ብር 40,156.94 ውስጥ በብር 1,480.00 ግዥ የተፈፀመው ዝቅተኛ የዋጋ ማወዳደሪያ ካላቀረበው ድርጅት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

  የዕቃ ግዥ በግዥ ማወዳደሪያ ደንብ መሰረት አለመፈፀሙ ውጤታማና ኢኮኖሚያዊ የሆነ የግዥ ስርአት እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

  ማንኛውም ግዥ በግዥ ደንብና መመሪያ መሰረት መፈፀም ይኖርበታል፤ ስለሆነም ለወደፊቱ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

- ለትራንስፖርት ወጪ የተደረገው ብር 258.00 በሂሣብ መደብ 6232 መያዝ ሲገባው በስህተት በውሎ አበል ሂሣብ መደብ (6231) ተመዝግቦ የተገኘና ክፍያውም የ12 ቀን መሆን ሲገባው የ15 ቀን በሚል በ3 ቀን (በብር 51.60) በብልጫ ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

  ሂሣቦች በተገቢው የሂሣብ መደባቸው ካልተያዙ አንዱን የወጪ ሂሣብ ከፍ (Overstate) ሌላውን ዝቅ (Understate) እንዲል ያደርገዋል፤ በተጨማሪም የክፍያዎቹ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ ከሆነ የወጪ ሂሣቦቹ ተአማኒ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

  ማንኛውም ሂሣብ መንግስት ካስቀመጠው የሂሣብ አያያዝ ስርአት ሊቀመጥና መ/ቤቱም የክፍያዎችን ትክክለኛነት በሚገባ ሊያረጋግጥ ይገባል፤ ስለሆነም ለተጠቀሰው ሂሣብ ተገቢውን እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ለተሽከርካሪዎች እድሳትና ጥገና ወጪ ከተደረጉት ጠቅላላ ሂሣቦች ውስጥ፡-

- ብር 31.09 የሆነ Withholding tax የተቆረጠ ቢሆንም ምዝገባ ያልተደረገለት ስለመሆኑ፣
- ብር 1,372.00 የሆነ Withholding tax ያልተቆረጡ መሆናቸው፣
- ብር 91,763.23 ለሆኑ ሂሣቦች የገቢ ደረሰኝ (GRN) ያልተቆረጠላቸው ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- ለዕቃ ግዥ ዋጋቸው ከብር 10,000.00 በላይ ለሆኑና ለአገልግሎት ከብር 500.00 በላይ ለሆኑ ግዥዎች 2% Withholding ተቆርጦ ሪፖርት አለመደረጉ መንግስት ማግኘት የነበረበትን ገቢ ከማስቀረቱም ባሻገር ሂሣቡ የተሟላ እንዳይሆን ያደርገዋል፤ ተገዝተው ለመጡ እቃዎችም GRN ያለመቆረጡ ዕቃዎቹ ለምዝበራና ብክነት ይጋለጣሉ፡፡

  በፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት ለአገልግሎት ከብር 500.00 በላይ እንዲሁም ለዕቃ ግዥ ከብር 10,000.00 በላይ 2% ታክስ ተሰብስቦ ፈሰስ መደረግ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት ሂሣብ ተጣርቶ ንብረቱ ገቢ እንዲሆን ወይም ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም መ/ቤቱ ተገቢውን የእርምት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

- ብር 115,834.70 የሆነ የደመወዝ ተከፋይ በበላይ ኃላፊ ሳይፀድቅ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡

ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት በበላይ ኃላፊ ካልፀደቀ የገንዘብ ቁጥጥር ስርአቱን ከማላላቱ ባሻገር የሂሣቡን ተአማኒነት ይቀንሰዋል፡፡

በፋይናንስ ህግና ደንብ መሰረት ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ወጪውን የማፅደቅ ኃላፊት ባለው ሰው መፈረም ይኖርበታል፤ ስለሆነም ለወደፊቱ እንደዚህ አይነት ስህተት እንዳይከሰት ጥብቅ ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

ንብረት

- ንብረቶች በአይነት በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል አያያዝ እንዲኖር እና ለጥበቃ አመቺ እንዲሆን ለማድረግ የመደርደሪያና በቂ የንብረት መጋዘን አለመኖሩ፣

አገልግሎት የማይሰጡና የተበላሹ እንዲሁም አገልግሎት የሚሰጡ ንብረቶች በአንድ ቦታ መጠበቃቸውና መወገድ የሚገባን ንብረት ለስራ አመራሩ ጊዜውን የጠበቀ መረጃ የማይደርስ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የንብረት አያያዝ ስርአቱ አመቺ ባለመሆኑ የመ/ቤቱ ንብረት ለምዝበራና ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

በግዥና ንብረት አስተዳደር ህግና ደንብ መሰረት ንብረቶች በአገልግሎታቸው ተለይተው አስፈላጊውን ምዝገባና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም ለንብረት አስተዳደር አመቺ በሆነ መንገድ ተደርድረው አስፈላጊው መረጃ ለበላይ አካላት መድረስ ይኖርበታል፡፡

ልዩ ልዩ

- የማጠቃለያ ሂሣብ ኦዲት ለማከናወን ተሞክሮ የሂሣብ መግለጫዎች ያልተዘጋጁና ለኦዲት ያልቀረቡ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ በዚህም የተነሳ ኦዲት በማድረግ የኦዲት አስተያየት መስጠት አልተቻለም፡፡

  በፋይናንስ ሂሣብ ደንብ መሰረት በወቅቱ ሂሣብ ካልተዘጋ የፋይናንስ ደንቡን የሚፃረርና በወቅቱ ኦዲት እንዳይከናወን ያደርጋል፡፡

  በፋይናንስ ሂሣብ ደንብ መሰረት ማንኛውም መ/ቤት የሂሣብ መግለጫዎችን በጀት ዓመቱ እንደጠናቀቀ ባሉት ሶስት ተከታታይ ወራት ውስጥ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቱ በደንቡ መሰረት ሂሣቡን ዘግቶ ለኦዲት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

- የሚኒስቴር መ/ቤቱ የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር ካርዱን በአግባቡ ስራ ላይ የማያውል መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በመ/ቤቱ የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር ካርድ ተዘጋጅቶ በአግባቡ ስራ ላይ የሚውልበት ሁኔታ ካልተመቻቸ መ/ቤቱ በጀቱን ባግባቡ ሊጠቀምበት ላይችልና መንግስት ያለውን ውስን ሀብት ለብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለወደፊቱ የበጀት መቆጣጠሪያ ሌጀር ካርድ በማዘጋጀት ስራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ሊያስቀምጥ ይገባል፡፡

- የውስጥ ኦዲት በበቂ የሰው ኃይል ካለመደራጀቱም በተጨማሪ በክፍሉ የተከናወነ ሥራ ለመኖሩ ማረጋገጫ አልቀረበም፡፡

የውስጥ ኦዲት ስራው ወጥ በሆነ መልኩ እቅድና ፕሮግራም ተይዞለት በትግበራ የማይውል ከሆነ የመ/ቤቱ ገንዘብና ንብረት በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ካለመቻሉም በላይ ጠንካራ የሆነ የውስጥ ቁጥጥር ለመገንባት አያስችልም፡፡

የመ/ቤቱ የበላይ አመራሮች በውስጥ ኦዲት ላይ የታየውን ድክመት በመገንዘብ ተገቢውን እርምጃና ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

# የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

# የ2002 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

## ሀ. መግቢያ

መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ሙሉ በሙሉ በመ/ቤታችን መተግበር ከተጀመረ ከየካቲት 2002 ዓ.ም. እስከ ጥር 2003 ዓ.ም. ድረስ ያለውን የአንድ ዓመት የሥራ እንቅስቃሴ ለማመላከት የተዘጋጀ ሪፖርት ነው፡፡ ሪፖርቱም ከተዘጋጀው ዕቅድ አንፃር የተከናወኑትን የኦዲት ሥራዎች ከማመላከቱም ባሻገር፣ የተገኙትን ዋና ዋና ግኝቶች አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡

## ለ. የተከናወኑ የኦዲት ሥራዎች

በ2002 በጀት ዓመት የኦዲት ጊዜያት 30 መ/ቤቶችን ለማከናወን ለዳይሬክቶሬቱ የሰው ኃይል ተመድቦ ወደ ሥራ የተገባ ሲሆን፣ የተወሠኑ ኦዲተሮች ሥራው ከተጀመረ በኋላ ሥራ በመልቀቃቸው ከፍተኛ ጫና ተፈጥሮ ነበር፡፡ ሆኖም ያሉትን ችግሮች ሁሉ በተቻለ መጠን በመቋቋም የሠላሣውም መ/ቤቶች የኦዲት ሥራ ተጠናቆ ሪፖርቱ ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤቶች ተልኳል፡፡ የመጨረሻ የኦዲት ሥራ ለማከናወንና የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ከተኬሄደባቸው ሠላሣ መ/ቤቶች ውስጥ ጅጅጋ ዩኒቨርስቲና የጥቁር አንበሣ አጠቃላይ ልዩ ሆስፒታል ሂሣባቸውን ባለመዝጋታቸው የሥራ አመራር ሪፖርት ብቻ እንዲደርሣቸው ተደርጓል፡፡ ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር ሲተነተኑ፣

- አልፎ አልፎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion) 18 መ/ቤቶች፣
- የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse opinion) የተሰጠባቸው 5 መ/ቤቶች፣
- አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean opinion) የተሰጠባቸው 1 መ/ቤት፤
- አቋም መውሰድ ያልተቻለባቸው 4 ሂሳቦች፤ እንዲሁም

- ሂሳባቸውን ባለመዝጋታቸው የኦዲት አስተያየት ያልተሰጠባቸው 2 መ/ቤቶች ሲሆኑ ዝርዝር ሁኔታው ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

## በኦዲት ሥራው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

በኦዲት ሥራው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች

የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያ የማያዘጋጁ፣ እንዲሁም የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የማያደርጉ /የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ አድርገናል ቢሉም ማስረጃ ያላቀረቡ/ እና የጥሬ ገንዘብ ቆጠራውን ከሂሣብ ቋት (ሌጀር) ጋር የማያመዛዝኑ መ/ቤቶች ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው ፡፡

- ሐዋሣ ጤና ሣይንስ ኮሌጅናሪፈራል ሆስፒታል
- አዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ
- የጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
- ጎንደር ዩኒቨርስቲ
- ባህርዳር እንጂነሪንግ ፋካልቲ
- መቀሌ ዩኒቨርስቲ
- ዲላ ዩኒቨርስቲ
- ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ
- አክሱም ዩኒቨርስቲ
- ወሎ ዩኒቨርስቲ
- አርባምንጭ ዩኒቨርስቲ
- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ
- ሠመራ ዩኒቨርስቲ

የባንክ ሂሣብ ማስታረቂያና የጥሬ ገንዘብ ሂሣብን በተመለከተ ያሉትን ሥጋቶች በመዘርዘርና መወሠድ ያለበትን ዕርምጃ በገለፅነው መሠረት ለማስተካከል እየተንቀሣቀሡ መሆኑን ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ገልፀዋል፡፡

2. **ተሰብሣቢ ሂሣብ**

ለዕቃ ግዥና ለተለያዩ ሥራዎች ወጪ ተደርገው (ከተሰጠው አገልግሎት ያልተሰበሰበ ገቢ) በፋይናንስ ደንቡ መሠረት ያልተወራረዱ ተሰብሳቢ ሂሣቦች ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው፡፡

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | ሃዋሣ ጤና ሣይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል | 1,236,078.00 |
| 2 | ጅማ ዩኒቨርስቲ | 4,476,947.83 |
| 3 | ጎንደር ዩኒቨርስቲ | 78,633,824.18 |
| 4 | ባህርዳር ኢንጂነሪግ ፋካልቲ | 1,482,779.81 |
| 5 | አዳማ ዩኒቨርስቲ | 412,512.33 |
| 6 | መቀሌ ዩኒቨርስቲ | 25,031,311.07 |
| 7 | የኢትዮጵያ ስቪል ሰርቪስ ኮሌጅ | 1,247,988.79 |
| 8 | ሐዋሣ ዩኒቨርስቲ | 8,204,630.65 |
| 9 | ትምህርት ሚኒስቴር | 340,921,554.76 |
| 10 | አርባምንጭ ዩኒቨርስቲ | 321,745.43 |
| 11 | መደወላቡ ዩኒቨርስቲ | 640,035.40 |
| 12 | ሠመራ ዩኒቨርስቲ | 1,194,725.42 |
| 13 | የትምህርትና የባህርይ ጥናት ኮሌጅ | 9,409,691.57 |
| | ድምር | 473,213,825.24 |

መሰብሰብ የሚችለው ሂሣብ ሣይዘገይ እንዲሰበሰብ ማድረግ፣ ከአቅም በላይ የሆኑትን ደግሞ የፋይናንስ ደንቡን ተከትሎ እንዲሠረዝ ማድረግ እንደሚገባ ለሰጠነው አስተያየት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ክትትል በማድረግ ዕርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3. <u>ተከፋይ ሂሣብ</u>

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሣብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከተው (ረጅም ዘመን ያስቆጠሩ ይገኙበታል) ተከፋይ ሂሣብ ቀጥሎ በየመ/ቤቶቹ አንፃር ተመልክቷል፡፡

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | ሃዋሣ ጤና ሣይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል | 1,468,212.73 |
| 2 | ጎንደር ዩኒቨርስቲ | 56,996,348.83 |
| 3 | ባህርዳር ኢንጂነሪግ ፋካልቲ | 259,065.62 |
| 4 | አዳማ ዩኒቨርስቲ | 2,583,797.71 |
| 5 | መቀሌ ዩኒቨርስቲ | 26,996,825.72 |
| 6 | ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ | 290,767.71 |
| 7 | ሐዋሣ ዩኒቨርስቲ | 5,845,591.16 |
| 8 | ትምህርት ሚኒስቴር | 28,150,012.56 |
| 9 | ወሎ ዩኒቨርስቲ | 3,069,362.53 |
| | ድምር | 25,659,984.57 |

የተከፋይ ሂሣቦቹን ዓይነት በመዘርዘር መወሠድ ስላለበት ዕርምጃ የሰጠነውን አስተያየት አብዛኛዎቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የተቀበሉት መሆኑን በሰጡት ምላሽ አስታውቀዋል፡፡

4. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

4.1. <u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ ገቢ</u>

በበጀት ዓመቱ ከሰበሰቡት የውስጥ ገቢ ቀጥሎ የተመለከቱት መ/ቤቶች ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ አላካተቱም፡፡

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | ሃዋሣ ጤና ሣይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል | 2,603,652.35 |
| 2 | አዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ | 3,492,982.11 |
| 3 | ጅማ ዩኒቨርስቲ | 10,659,642.48 |
| 4 | ጎንደር ዩኒቨርስቲ | 11,360,279.68 |
| 5 | አዳማ ዩኒቨርስቲ | 7,639,818.52 |
| 6 | አክሱም ዩኒነቨርስቲ | 2,624,756.54 |
| | ድምር | 38,381,131.68 |

በሠንጠረዡ ከተመለከተው ሌላ የገንዘቡ መጠን የማይታወቅ የውስጥ ገቢ የሚሰበሰቡ ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ፤ ወሎ ዩኒቨርስቲ ፤መደወላቡ ዩኒቨርስቲና ሠመራ ዩኒቨርስቲ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ አላካተቱም፡፡

የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ደግሞ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብር 7,423,800.00 የሰበሰበ መሆኑን ቢገልፅም የውስጥ ገቢ ሂሣቡን አልመዘገበም፣ ከወጪ ቀሪም የሚያሣይ መዝገብ የለም፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚዘጋጁት ሂሣብ መግለጫዎች ከተለያዩ ምንጮች የተገኙትን ገቢዎች አካቶ መያዝ እንዳለበት ለሰጠነው አስተያየት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የተቀበሉት መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

4.2. በገቢ አሠባሰብ ላይ የታዩ የአሠራር ድክመቶች

- የጎንደር የሕክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ከተለያዩ ምንጮች የሚሰበስበውን የውስጥ ገቢ፣ የልዩ ፋርማሲ የመድኃኒት ሽያጭ ገቢና የፕሮጀክት ፈንድ ለይቶ መዝግቦ አልያዘም፡፡ በተጨማሪም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጁ መሠረት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈቃድ ሣያገኝ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝና ሌሎች ቫውቸሮችን አሣትሞ በመጠቀም ላይ ይገኛል፡፡
- የጎንደር ዩኒቨርስቲ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ማኒስቴርን ሣያሣውቅና ፈቃድ ሣያገኝ ብዛቱ 5000 ጥራዝ የውስጥ ገቢ የገንዘብ መቀበያ ደረሠኝ አሣትሞ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡
- በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ገቢ ተደርጎ የተገኘው ብር 789,611.92 የገቢውን ዝርዝር ሁኔታ የሚያስረዳ ማስረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡

ተቋማቱ በመንግሥት የሚወጡ አዋጆችንና ደንቦችን በመከተል ደረሠኝ ከማሣተም በፊት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማስፈቀድ እንዳለባቸው በተጨማሪም ምንጩ ያልታወቀውን ገቢ በማጣራት መመዝገብ እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ ኦዲት ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

## 5. የወጪ ሂሣብ

### 5.1. በወጪ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ

በበጀት ዓመቱ ከሰበሰቡት የውስጥ ሂሣብ ውስጥ ወጪ አድርገው በዓመቱ ባዘጋጁት የወጪ ሂሣብ መግለጫ ውስጥ ያላካተቱ መ/ቤቶች ቀጥለው የተመለከቱት ናቸው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሃዋሳ ጤና ሣይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል | | ብር 1,827,526.97 |
| አክሱም ዩኒቨርስቲ | | 1,334,512.77 |
| | ድምር | 3,162,039.74 |

በተጨማሪም የሠመራ ዩኒቨርስቲ በብር 602,203.86 የገዛውን የተለያየ ንብረት በወጪ ባለመመዝገቡ የተዘጋጀው የወጪ ሂሣብ ሪፖርት በዚሁ መጠን አንሶ ይታያል፡፡

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ከውስጥ የተገኘውን ገቢ መዝግበው ሪፖርት እንዲያደርጉ፣ ወጪ የተደረገውም ሂሣብ በሪፖርት ውስጥ መካተት እንዳለበት አስተያየት የሰጠን ሲሆን፣ በአስተያየቱ መሠረት ጉዳዩን በማጣራት የእርምት ዕርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

### 5.2. የሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ የተከናወኑ ምዝገባዎች

የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሣይጠብቁ ተመዝግበው የተገኙ የወጪ ሂሣቦች ቀጥለው ተመልክተዋል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሣይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር | ብር | 61,488.96 |
| ጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻለይዝድ ሆስፒታል | ” | 575,111.42 |
| ባህርዳር ኢንጂነሪንግ ፋካልቲ | ” | 55,850.00 |
| ሠመራ ዩኒቨርስቲ | ” | 156,380.00 |
| የትምህርትና የባሕርይ ጥናት ኮሌጅ /ሥነ-ትምህርት ፋካልቲ/ | ” | 862,400.00 |
| ድምር | ” | 1,711,230.38 |

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ አለመመዝገብ ከበጀት አጠቃቀም አንፃር ተፅዕኖ ሊፈጥር ስለሚችል (ከበጀት በላይ ወይም በታች የመጠቀም) ተገቢው ጥንቃቄ እንዲወሰድ

አስተያየት ሰጥተናል፡፡ በዚሁ መሠት ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንደሚያደርጉ መ/ቤቶቹ አስታውቀዋል፡፡

## 5.3. የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ

በወጪ የተመዘገቡት ሂሣቦች የተሟላ መረጃ ቀርቦላቸው በወጪ ለመመዝገባቸው ሲጣራ ቀጥሎ የተመለከቱት ግኝቶች ተከስተዋል፡፡

- የጐንደር የሕክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ ለዕቃዎች ግዥ ብር 2,068,049.54 ለፈፀመው ክፍያ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ማስረጃ የለም፡፡
- አክሱም ዩኒቨርስቲ ለክረምት ተማሪዎች ለፈፀመው ክፍያ ብር 476,160.00 የተማሪዎች ዝርዝር ከማቅረብ ውጭ ለክፍያው በቂ ማስረጃ ማቅረብ አልቻለም፡፡
- ትምህርት ሚኒስቴር ለጂቲዜድ የፈፀመው ክፍያ ብር 1,420,803,252.15 በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚየሣይ ዝርዝር መረጃ የተደገፈ አይደለም፡፡
- ከገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ለሥልጠና ተብሎ ለወሎ ዩኒቨርስቲ የተላለፈው ተጨማሪ በጀት ብር 2,365,730.00 ማስረጃ ሣይኖረው በቀጥታ በወጪ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በድምሩ ብር 1,503,562.53 ክፍያ የያዙ የወጪ ሠነዶች ለኦዲት አልቀረቡም፡፡
- የትምህርትና የባህርይ ጥናት ኮሌጅ በብር 308,990.50 ለገዛው የማባዣ ወረቀትና ፎቶ ኮፒ ማሽን ያቀረበው ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሠኝ ነው፡፡

የየመ/ቤቱ ሥራ አመራር የሰጠነውን ማሻሻያ ተቀብሎ ችግሩ እንዳይደገም ክትትል እንደሚያደርግና ለሚመለከተውም ክፍል መመሪያ እንደሚያስተላልፍ ገልጿል፡፡

## 5.4. የግዥ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ሣይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

- የጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለቀዶ ጥገና የሚሆኑ የእጅ ጓንቶችን አነስተኛ ያቀረበውን ድርጅት በመተው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው በብር 84,750.00 በግዥ ፈፅሟል፡፡

- ወሎ ዩኒቨርስቲ የምግብ ጥሬ ዕቃዎችን በብር 3,408,211.29 ግዥ ሲፈፅም ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበውን ድርጅት በመተው ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው ግዥ ፈፅሟል፡፡

ጨረታ ሣይወጣና ያለውድድር ግዥ የፈፀሙ መ/ቤቶች ቀጥለው ተመልክተዋል፡-

| | | |
|---|---|---|
| - ጐንደር የሕክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ | ብር | 370,126.41 |
| - ጅማ ዩኒቨርስቲ | " | 912,109.00 |
| - ጐንደር ዩኒቨርስቲ ጀኔሬተር እና የምግብ አቅርቦት | " | 5,517,442.23 |
| - መቀሌ ዩኒቨርስቲ /ቃና አገልግሎት/ | " | 1,489,410.02 |
| - ዲላ ዩኒቨርስቲ (ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎችና መደርደሪያዎች | " | 257,318.25 |
| - ሐዋሣ ዩኒቨርስቲ (ለሠራተኞችና መምህራን መኖሪያ ሕንፃ ግንባታ ) | " | 11,940,422.19 |
| - ትምህርት ሚኒስቴር (ለአምቦ ዩኒቨርስቲ ማስፋፊያ ግንባታና የኮምፒዩተር ግዥ) | " | 27,807,686.83 |
| - ወሎ ዩኒቨርስቲ (ለተማሪዎች እንጀራና ዳቦ ግዥ) | " | 8,925,134.73 |
| - አርባምንጭ ዩኒቨርስቲ (የተሽከርካሪ ጥገናና ግንባታ) | " | 3,591,233.21 |
| ድምር | " | 60,810,882.87 |

ለወደፊቱ ግዥዎች ሲፈፀሙ የመንግሥትን አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ መከተል እንዳለባቸው በሰጠነው አስተያየት መሠረት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገለፀዋል፡፡

### 5.5. በኃላፊ ሣይፈቀድ የተፈፀመ ክፍያ

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች የፈፀሙት ክፍያ በሚመለከታቸው ኃላፊዎች የፀደቀ ለመሆኑ፣ ሲታይ፣ የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ለተፈፀመው ክፍያ

ብር 1,682,850.00 በኃላፊ ሣይፀድቅ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ማንኛውም ክፍያ በመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ መፅደቅ እንዳለበት ያሣሰብን ሲሆን፣ በወቅቱ የኃላፊነት ዝውውር በመደረጉ ሳይፈረም መቅረቱን ኮሌጁ በሰጠው ምላሽ ገልጿል፡፡

## 5.6. ቅድሚያ ክፍያን በወጪ መመዝገብ

- የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ ከሐምሌ 2002 እስከ ታህሣስ 2003 ዓ.ም ድረስ ለፈፀመው የቢሮ ኪራይ የቅድሚያ ክፍያ ብር 1,460,419.60 እንደበጀት ዓመቱ ወጪ በመቁጠር በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የጅማ ዩኒቨርስቲ ለህንፃ ግንባታ ለሥራ ተቋራጮች በቅድሚያ የከፈለውን ብር 37,530,291.84 ቀጥታ በወጪ መዝግቦታል፡፡
- አርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ ለሌተር ኦፍ ክሬዲት /ቋሚ ንብረት ግዥ/ መክፈቻ የከፈለውን ብር 71,458,389.93 እና ለሥራ ተቋራጭ ቅድሚያ ክፍያ ብር 40,602,298.67 በድምሩ ብር 112,060,688.60 በተሰብሣቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በጥሬ ገንዘብ ሂሣብ አያያዝ መሠረት ገንዘቡ በተከፈለበት ጊዜ መያዝ እንጂ የተከፋይና የተሰብሣቢ ሂሣብ መያዝ እንደማይቻል የገለፀ ቢሆንም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ሂሣብ አያያዝ ግን ተከፋይም ተሰብሣቢም ሂሣብ መያዝ እንዳለበት ስለሚያስገነዝብ ክፍያው ተስተካክሎ እንዲያዝ ማሳሰቢያ ሰጥተናል፡፡ የተቀሩት መ/ቤቶች ግን የማሻሻያ ሃሣቡን ተቀብለው የማስተካከያ እርምጃ እንደሚወስዱ በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

## 5.7. የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበበት የወጪ ሂሣብ

በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተገዙት ዕቃዎች በሙሉ ለየመ/ቤቶቹ ገቢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ሲሞከር፣ የጅማ ዩኒቨርስቲ በብር 1,340,219.93 የገዛውን ቋሚ ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ አልቆረጠለትም፡፡ በመሆኑም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ያልተደረጉት ዕቃዎች ዝርዝር ሁኔታ ተጣርቶ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊቆረጥለት

እንደሚገባ አስተያየት የሰጠን ሲሆን፣ የሥራ አመራሩም ሃሣቡን ተቀብሎ ማስተካከያ እንደሚያደርግ ገልጿል፡፡

5.8. ከበጀት ዓመቱ ውጭ ተመዝግቦ የተገኘ

- የአምቦ ዩኒቨርስቲ ለሰኔ ወር 2001 ዓ.ም. ለመምህራን የቤት ኪራይ አበል የከፈለውን ብር 59,900.00 በ2001 በጀት ዓመት ውስጥ መጠቃለል ሲገባው በ2002 በጀት ዓመት በወጪ መዝግቦታል፡፡ በመሆኑም ሂሣቡ አገልግሎቱ በተገኘበት በጀት ዓመት ተስተካክሎ መመዝገብ እንዳለበት ያሣሰብን ሲሆን፣ ሥራ አመራሩም የማሻሻያ ሃሣቡን ተቀብሎታል፡፡
- የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ በ2001 በጀት ዓመት ለፈፀመው የደንብ ልብስና ጫማ ግዥ ብር 147,152.33 እና የምግብ ግዥ ብር 616,970.72 በድምሩ ብር 764,123.05 በ2002 በጀት ዓመት በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ያለፈው ዓመትን ወጪ ወደ 2002 በጀት ዓመት ማምጣት ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀምን ሊያስከትል ስለሚችል የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ በሰጠነው ማሻሻያ ሃሣብ መሠረት እንደሚፈፀም ከተሰጠው ምላሽ መረዳት ይቻላል፡፡

5.9. ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ

- የዲላ ዩኒቨርስቲ የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ብር 336,370.70 ክፍያ የያዘ የወጪ ሠነድ ለኦዲት ባለመቅረቡ የሂሣቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ክፍያ የተፈፀመባቸው ሠነዶች ቀርበው ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥ ካልተቻለ ክፍያው ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ይህን በተመለከተ ዩኒቨርስቲው በሰጠው ምላሽ የሂሣብ ማስተካከያ ምዝገባ በማከናወን ከመዝገብ እንዲሠረዙ መደረጉን ገልጿል፡፡

5.10. ያለአግባብ ወይም ከውሉ በላይ የተፈፀመ ክፍያ

- የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ብር 3,808.00 ደመወዝና የቤት አበል ለትምህርት ወደውጪ ሀገር ለተላኩ የዩኒቨርስቲው መምህር ከደንብ ውጭ ከፍሏቸዋል፡፡ በመሆኑም ያለአግባብ የተከፈላቸው ደመወዝና የቤት አበል ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የሰጠን ሲሆን፣ ዩኒቨርስቲውም አስተያየቱን የተቀበለ መሆኑን ገልጿል፡፡

- የትምህርት ሚኒስቴር እ.ኤ.አ በ30/08/2005 እና እ.ኤ.አ በ22/04/2008 አሥራ ሦስት ዩኒቨርስቲዎችን ለማስገንባት በተገባው ውልና ከ1998 እስከ 2002 በጀት ዓመታት ድረስ በተፈፀመው ክፍያ መካከል ብር 441,155,353.46 ከውሉ በላይ ክፍያ ተፈፅሟል፡፡ክፍያው በውለታው መሠረት ለታለመለት ዓላማ ለመዋሉ መረጋገጥ እንዳለበት በሰጠነው ማስገንዘቢያ መሠረት፣ የሚገነቡት ሕንፃዎች ስፋት በውሉ ላይ ከተመለከተው በመጨመሩና ውሉ ከተፈረመ በኋላ የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ በከፍተኛ ደረጃ በመጨመሩ ልዩነቱ ሊታይ መቻሉን መ/ቤቱ በሰጠው መልስ አመልክቷል፡፡ ሆኖም ልዩነቱ( ከውሉ በላይ የተፈፀመው ክፍያ) በጣም ከፍ ያለ ስለሆነ ሂሣቡ ከመጀመሪያ አንስቶ በዝርዝር እንዲታይ አሣስበናል፡፡

6. <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር</u>

ቋሚም ሆኑ አላቂ ዕቃዎች በተቀመጠለት ሥርዓት ተመዝግቦ መያዙን ለማረጋገጥ ሲሞከር፣ ቀጥሎ የተመለከቱት መ/ቤቶች የቋሚ ንብረት መመዝገቢያና መቆጣጠሪያ መዝገብ አቋቁመው (ያቋቋሙትም ቢሆን ምዝገባውን አጠናቀው ) ከወጪ ቀሪያቸውን ወይም ያሉትን ዕቃዎች የሚያውቁበት መንገድ አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

- ሃዋሣ ጤና ሣይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል
- የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር
- የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ
- አዳማ ዩኒቨርስቲ
- ዲላ ዩኒቨርስቲ
- ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ
- አክሱም ዩኒቨርስቲ
- ትምህርት ሚኒስቴር
- ወሎ ዩኒቨርስቲ
- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ
- መደወላቡ ዩኒቨርስቲ

- የአዲስ አበባ ንግድ ሥራ ኮሌጅ በብር 331,000.00 የገዛውን ፕሮጄክተር በቋሚ ዕቃ መዝገብ ላይ ሣይመዘግብ ተገኝቷል ፡፡
- በባህርዳር ኢንጂነሪንግ ፋካልቲ ሊወገዱ ወይም እንደአስፈላጊነቱ አገልግሎት ላይ ሊውሉ የሚገባቸው በርካታ ንብረቶች በፋካልቲው ቅጥር ግቢ ውስጥ ተከማችተዋል፡፡
- የሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ ለተማሪዎች ምረቃ በዓል በሚል በብር 15,200.00 ለገዛው ጨርቅ በንብረት ደረሠኝ ገቢና ወጪ ያልተደረገና በትክክል ሥራ ላይ የዋለ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በመደወላቡ ዩኒቨርስቲ የሚገኙ አላቂ ዕቃዎች በቆርቆሮ በተሠራ ግምጃ ቤት ውስጥ በቀላሉ ሊበላሹ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ስለሆኑ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል ፡፡
- በትምህትና ባህርይ ጥናት ኮሌጅ (ሥነ-ትምህርት ፋካልቲ) ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ በርካታ ዕቃዎች ተከማችተው (የዕቃ ግምጃ ቤቱን አጣበው ) ይገኛሉ፡፡

በቋሚ ዕቃነት መመዝገብ ያለባቸው እንዲመዘገቡ፣ ሥራ ላይ ሊውሉ የማችሉት ከማይችሉት እንዲለዩ፣ ዕቃዎች እንዳይበላሹ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሠድ፣
አላቂና ቋሚ ዕቃዎች የንብረት ገቢና ወጪ ደረሠኝ ተዘጋጅቶለት /ለቋሚ ዕቃ ወጪ ማድረጊያ ማዋሻ ቅፅም ሊሆን ይችላል/ ተመዝግበው ከወጪ ቀሪያቸው በትክክል መታየት እንዳለበት ለሠጠነው አስተያየት አብዛኛው መ/ቤቶች ተግባራዊ እንደሚየደርጉት በሠጡት ምላሽ አስታውቀዋል፡፡

7. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

ለየመ/ቤቶቹ የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ሂሣብ ጋር ሲነፃፀር ከበጀት በላይ መውጣቱና ሥራ ላይ ያልዋለም ሂሣብ ተመልክቷል፡፡

| ተ.ቁ | ተቋም | ከበጀት በላይ የወጣ | ያልተሠራበት በጀት /ሥራ ላይ ያልዋለ/ |
|---|---|---|---|
| 1 | ጐንደር የህክምናና ጤና ሣይንስ ኮሌጅ | 390,011.71 | 1966,094.56 |
| 2 | የከፍተኛ ትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል | | 582,509.05 |
| 3 | አምቦ ዩኒቨርስቲ | 3,342,658.90 | 7,533,460.89 |
| 4 | የጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | 118,630.47 | |
| 5 | የመገናኛናኢንፎርሜሽን ቴክግሎጂ ሚኒስቴር | 17,957,556.72 | |
| 6 | ጐንደር ዩኒቨርስቲ | 15,170,700.66 | |
| 7 | የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ | | 1,459,969.65 |
| 8 | አዳማ ዩኒቨርስቲ | 1,520,808.36 | 24,181,915.43 |
| 9 | ዲላ ዩኒቨርስቲ | 70,810.00 | 10,429,593.69 |
| 10 | ሚዛን ቴፒ ዩኒቨርስቲ | 760,810.18 | 2,971,181.69 |
| 11 | የኢትዮጵያ ስቪል ሰርቪስ ኮሌጅ | | 14,014,303.15 |
| 12 | ሐዋሣ ዩኒቨርስቲ | 21,737,754.65 | 17,871,481.57 |
| 13 | ትምህርት ሚኒስቴር | 693,657,348.33 | 408,000,511.44 |
| 14 | ወሎ ዩኒቨርስቲ | 295,450.86 | 1,296,633.15 |
| 15 | ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ | 19,968.66 | 2,621,718.88 |
| 16 | መደወላቡ ዩኒቨርስቲ | 75,270.84 | 5,241,874.83 |
| 17 | ሠመራ ዩኒቨርስቲ | 5,654.35 | - |
| | ድምር | 130831824.69 | 498,171,247.98 |

ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም የበጀት ሕግን ከመጣስ ባሻገር መንግሥት ያለውን ውስን ሃብት ለብክነት እንደሚያጋለጥና የታወጀን በጀት አለመጠቀሙ መ/ቤቱ ሊደርስበት ካቀደው ግብ እንዳይደርስ ከማድረጉም ባሻገር ሀገሪቱ ያላትን ውስን ሃብት በአግባቡ ሥራ ላይ እንዳይውል ስለሚያደርግ ዕቅድን ከክንውን

ማጣጣም እንደሚገባ አስተያየት የሰጠን ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አስፈላጊውን ክትትልና ማሻሻያ እንደማያደርጉ በሰጡት መልስ ገልፀዋል፡፡

8. <u>ልዩ ልዩ</u>

የሃዋሣ ጤና ሣይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል ኦዲት በተደረገበት ወቅት ከአካባቢ ብክለት ጋር የተያያዙ ነገሮችን ተመልክተን በወቅቱ ሪፖርት አድርገናል፡፡

- ሆስፒታሉ ከሃዋሣ ሐይቅ አጠገብ የተሠራ በመሆኑ ከሆስፒታሉ ላቦራቶሪ፣ኤክስሬይና ከሌሎች ክፍሎች የሚወጣው ፍሣሽ ወደሐዋሣ ሐይቅ የሚለቀቅ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የሆስፒታሉ ደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ ኢንሲነሬተር (Incinerator) አገልግሎት አይሰጥም፡፡
- ለደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ የሚሆን ጉድጓድ ያልተዘጋጀ በመሆኑ የሕክምና ደረቅ ቆሻሻና ታካሚዎች ተመግበው የሚተርፈው የምግብ ትርፍራፌ በገላጣ ሜዳ ላይ የሚደፋ ሲሆን፣ በዚሁ አካባቢ ሆስፒታሉ አጥር የሌለው በመሆኑ ሰዎች /በተለይም ሕፃናት/ እና የተለየዩ እንስሣት ሊያገኙት በሚችሉበት ሁኔታ ተጋልጦ ተገኝቷል፡፡
- ከማዋለጃና ከቀዶ ጥገና ክፍል በሕክምና ምክንያት የሚወገድ የሰውነት አካላት ክዳን በሌለው ጉድጓድ ውስጥ የሚጣሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ከላይ ለተጠቀሱት ነጥቦች አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደረግ ለሰጠነው አስተያየት፣ በኦዲት ሪፖርቱ ላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመቅረፍ ደረቅ ቆሻሻዎችን በኮንትራት ለማስወገድ ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣ ኢንሲኔሬተሩን ለመጠገን እየተሞከረ መሆኑን፣ ለጊዜያዊ የቆሻሻ መጣያ ባለክዳን ጉድጓድና አጥር የተዘጋጀ መሆኑን፣ ፍሳሹ ወደሐይቁ ለመሄዱ ግን የቀረበ ማረጋገጫ ስላገኘን ምክክር በማድረግ ተገቢው አመራር እንደሚሰጥበት ሥራ አመራሩ በሰጠው ምላሽ አስታውቋል፡፡

የጅማ ዩኒቨርስቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ /ኢንሲነሬረተር/ አገልግሎት የማይሰጥ በመሆኑ የደረቅ ቆሻሻ ክምችት በማስከተሉ በአካባቢያዊ አየር ላይ አሉታዊ ተፅእኖ እያስከተለ ለመሆኑ ለሰጠነው አስተያየት፣ በተደጋጋሚ

የሚመለከተውን ክፍል በደብዳቤ መጠየቃቸውንና ለደብዳቤውም ምላሽ ያላገኙ መሆኑን ሥራ አመራሩ ገልጿል፡

የወሎ ዩኒቨርስቲ ከተማሪዎች ካፌቴሪያ የሚወጣው ፍሣሽ ወደወንዶች መኝታ ቤት አካባቢ የሚፈስ በመሆኑ መጥፎ ጠረን የፈጠረና ለጤና አስጊ ደረጃ ላይ የደረሠ መሆኑን፣ በቆርቆሮ የተሠሩ የወንዶችና የሴቶች ሽንት ቤቶች የሞሉ በመሆኑ የጤና ችግር በሚፈጥሩበት ደረጃ ላይ የደረሡ መሆኑን አሣስበናል፡፡ የሥራ አመራሩ የኦዲት ግኝቱንና የማሻሻያ ሃሣቡን ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ እየተንቀሣቀሠ መሆኑን ገልጿል፡፡

## የልማትና ማኅበራዊ ኦዲት ዳይሬክቶሬት

## የ2002/2003 በጀት ዓመት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን፣ እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ፣ 31 መ/ቤቶች የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብን ኦዲት አድርገናል፡፡

ለመ/ቤቶቹ በሙሉ ለሥራ አመራር የተዘጋጀውን ሪፖርት የላክን ሲሆን፣ ከኢትዮጵያ የምግብ፣ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን በስተቀር ሌሎቹ መ/ቤቶች ለሪፖርቱ በሰጡት መልስ ውስጥ ስለማሻሻያ ሃሣቦች ያላቸውን አስተያየት የገለፁ ሲሆን፣ ለሁሉም መ/ቤቶች ኦዲት በተደረገው ሂሣባቸው ላይ ያለንን አስተያየት የያዘ ሪፖርት ተልኳል፡፡ ሪፖርቶቹ ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር ሲተነተኑ፣

- አልፎ አልፎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion) 12 መ/ቤቶች፣
- የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse opinion) የተሰጠባቸው  መ/ቤቶች፣
- አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean opinion) የተሰጠባቸው 15 መ/ቤቶች እንዲሁም
- 1 መ/ቤት ደግሞ ሂሣቡን በወቅቱ ባለመዝጋቱና ለኦዲት ባለማቅረቡ በሂሣብ መግለጫዎቹ ትክክለኛነት ላይ አቋም ለመውሰድ ያልቻልን መሆናችን የሚገለፅ አስተያየት ሰጥተናል፡፡

### በኦዲት ሥራው  የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

በኦዲት ሥራው  የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ</u>

1.1 <u>የገንዘብ ቆጠራ ስለአለመደረጉ</u>

የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን እና የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ. ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
- የአማኑኤል አእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
- የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድሐኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን
- የብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር እና
- የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ

የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ቆጠራ ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡

የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ በየወሩ ተቆጥሮ ከመዝገብና በሂሣብ ማመዛዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር ሊመዛዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

1.2 <u>ከገንዘብ ያዥ ቢሮ ገንዘብ ስለመሰረቁ</u>

በኢትዮጵያ የምግብ፣ መድሐኒትና ጤና ክብካቤ ባለሥልጣን፣ የገንዘብ ያዥ ቢሮ መስታወት ተነቅሎ የበሩ እጀታ ተሰብሮ መገኘቱን በመግለፅ በ19/02/2002 ዓ.ም ለቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 ፖሊስ ጣቢያ የተፃፈውን ደብዳቤ መሠረት በማድረግ፣ ለገንዘቡ ጥንቃቄ እንዳልተደረገ ላቀረብነው ጥያቄ፣ የመሥሪያ ቤቱ ካዝና ቁልፉ ስለማይሠራ በጠረጴዛ መሳቢያ ውስጥ በመቀመጡና እንዲሁም ገንዘቡ የጠፋበት ዕለት ዓርብ ስለነበረ ባንክ ገቢ ለማድረግ ባለመቻሉ ምክንያት ገንዘቡ ለስርቆት መጋለጡን ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

የጠፋው ገንዘብ ተጣርቶ ለመንግሥት እንዲተካ እና ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 1.3 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ስለመገኘቱ

በማዕድንና ኤነርጂ ሚኒስቴር በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ፣ በሣጥን ውስጥ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ በመዝገብ ከተመለከተው ጋር ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ የውስጥ ኦዲተሮች ምርመራ ሲያደርጉ ብር 1,672.33 እንደጎደለ ለማወቅ ችለዋል፡፡

የጎደለው ገንዘብ እንዲተካና ወደፊትም ተገቢው ቁጥጥር እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

## 1.4 የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ልዩነት ስለመገኘቱ

በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬቱ የጥሬ ገንዘብ ማመዛዘኛ ሲሰራ ብር 20,106.02 የጥሬ ገንዘብ ልዩነት በማነስ ተገኝቷል፡፡ ዳይሬክቶሬቱ ሁኔታውን አጣርቶ ጉዳዩ ከሚመለከተው ገንዘብ ያዥ ገንዘቡን እንዲያስተካ እንዲሁም፣ ለወደፊቱ በጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ላይ ተገቢው ቁጥጥር እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

## 1.5 በሂሣብ ማመዛዘኛው ሪፖርት ላይ የተመለከተው ሂሣብ ከተቆጠረው ጥሬ ገንዘብ የሚያንስ ስለመሆኑ

በመንግሥት ደንብ መሠረት በ2002 በጀት ዓመት መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን እና የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ ጋር ለመመሳከሩ ኦዲት ሲደረግ በብሔራዊ የሰው ሠራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተቆጠረው ገንዘብ ከመዝገብ (ሌጀር) ከተመለከተው ጋር ሲነፃፀር በብር 8,768.90 በልጦ ተገኝቷል፡፡ የዚህም ምክንያት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ የተሰበሰበው ገቢ ብር 8,768.93 በቀጣዩ በጀት ዓመት እንዲመዘገብ በመደረጉ እንደሆነ ታውቋል፡፡ ገቢው በተገቢው የበጀት ዓመት ውስጥ ያለመመዝገብ ስህተት መሆኑና ለወደፊቱ ተመሳሳይ የአሠራር ግድፈት እንዳይኖር ጥንቃቄ እንደሚያደርግ መ/ቤቱ በላከልን መልስ ገልፆልናል፡፡

## 1.6 የባንክ ሂሣብ

በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት በዜሮ የባንክ ሂሣብ ቁጥር ገቢ ለሆኑ ሂሣቦች፣ የገቢ ደረሰኝ እየተቆረጠላቸው የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ባንክ ገቢ ለሆነ ብር 38,340.10 በድጋሚ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት በገቢ የተመዘገበ መሆኑ፣
- ባንክ ገቢ ለሆኑ የተለያዩ ሂሣቦች ብር 51,809.33 ደግሞ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸውና ያልተመዘገቡ እንደሆኑና፣
- በሌላ የባንክ ሂሣብ ገቢ የሆነ ብር 6,591.24 በዜሮ የባንክ ሂሣብ ሌጀር እንደተመዘገበ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም በዜሮ የባንክ ሂሣቡ ቁጥሩ የተመለከተው ከወጪ ቀሪ ሂሣብ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይደገም መ/ቤቱ በባንክ ሂሣቡ ላይ ተገቢውን ቁጥጥር እንዲያደርግ በተለይም ወርሃዊ የባንክ የሂሣብ ማስታረቂያ እንዲያዘጋጅ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 2. <u>ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

### 2.1 <u>በተገቢው ጊዜ ያልተወራረደ</u>

በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሣብ በወቅቱ እንደተወራረደ፣ መመለስ በማይቻለው ላይ ደግሞ አስፈላጊው እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

| | <u>ብር</u> |
|---|---|
| • በሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር | 125,757.00 |
| • በኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ | 1,551,578.00 |
| • በማዕድን ሚኒስቴር | 2,008,880.00 |
| • በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን | 9,759,000.00 |
| • በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት | 899,542.51 |
| • በሕብረት ሥራ ኤጀንሲ | 38,514.92 |
| • በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት | 12,322,509.11 |
| • በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ | 121,706,484.20 |
| • በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ | 112,775.96 |

ለተለያዩ ሠራተኞችና ድርጅቶች ተሰጥቶ በተገቢው ጊዜ ያልተወራረደ ገንዘብ ተገኝቷል፡፡

ከላይ የተመለከተው ከፍተኛ ውዝፍ ሂሳብ፣ ከሚመለከታቸው ግለሰቦችና ድርጅቶች እንዲሰበሰብ፣ መሰብሰብ በማይችለው ላይ ደግሞ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብ መሠረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

## 2.2 <u>አግባብ ባለው የሂሣብ መደብ ያልተያዘ</u>

የተሰብሳቢ ሂሣብ የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሣብ አያያዝ ደንብ መሠረት የሚመዘገቡ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ምርመራ ሲደረግ፣

- በቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣ በጤና ጥበቃ ሚ/ር የውስጥ ኦዲተሮች ኦዲት በ1986 የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 3,780.25 ይኸ ኦዲት እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ ያልተተካና በ4202 የሒሳብ መደብ መያዝ ሲገባው በተሰበሳቢ የሂሣብ መደብ (4203) ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ደግሞ፣
  - በግዥ ቅድሚያ ክፍያ በሂሣብ መደብ 4211 እና በሰነድ መክፈያ በሂሣብ መደብ 4201 መያዝ የነበረባቸው ሂሣቦች፣ አለአግባብ ለሠራተኛ ቅድሚያ ክፍያ መመዝገቢያ በሚያገለግለው የሂሣብ መደብ 4203 እንደተመዘገቡ ለማወቅ ተችሏል፡፡
  - በ2002 በጀት ዓመት በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት ለሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ በሂሣብ መደብ 4203 የመነሻ ሂሣብ ብር 353,381.72 እንዲሁም ለአቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ በሂሣብ መደብ 4253 የመነሻ ሂሣብ ብር 714,561.97 የተመለከተ ሲሆን ሰነዱ ለኦዲት ሊቀርብ ባለመቻሉ ምክንያት የመነሻ ሂሣቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በብሔራዊ ሜቴሮሎጂ ኤጀንሲ በተደረገው ኦዲት፣
  - በ4201 የሂሣብ መደብ (በልዩ ልዩ ቅድሚያ ክፍያዎች) ላይ መመዝገብ የነበረበት ሂሣብ በ4203 (ለሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ መመዝገቢያ) ላይ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

- ሌሎች የቅድሚያ ክፍያዎች መመዝገቢያ ለሚያገለግለው የሂሣብ መደብ 4210 ላይ ብር 10,636.54 በብልጫ የተከፈለ የቅድሚያ ንግድ ትርፍ ግብር ተመዝግቦለት ተገኝቷል፡፡
- ከግለሰቦችና ከግል ድርጅቶች የሚሰበሰብ ሂሣብን ለመመዝገብ በተመደበው የሂሣብ መደብ 4273 ላይ ከተመዘገበው ብር 22,005.74 ውስጥ የብር 16,579.93 ሠነድ ለኦዲት ሊቀርብ ባለመቻሉ የሂሣብን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በክልል ለሚገኙ ቅ/ጽ/ቤቶች ለመደበኛና ለካፒታል በጀት መላኪያ በሚያገለግለው በሂሣብ መደብ 4274 የተመለከተው ብር 187,148.10 ሲሆን በቅ/ጽ/ቤቱ ተቀጽላ ሌጀር ተመዝግቦ የተገኘው ደግሞ ብር 148,060.67 ብቻ በመሆኑ የብር 39,087.43 ልዩነት ተገኝቷል፡፡

- በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ደግሞ ከ1956 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1994 ድረስ የቆየና ለደሞወዝና ሥራ ማስኬጃ የተከፈለ ብር 83,656.74 በተገቢው የሂሣብ መደቦች (4210) ሳይሆን በ4201 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የተሰብሳቢ ሂሣብ በተገቢው የሂሣብ መደብ፣ ካልተመዘገበ የተሰብሳቢና ሌሎች የሂሣብ መግለጫዎችን የሚያሳዩት የተጠቃለለ ሂሣብ ትክክል እንዲሆን ስለሚያደርግ፣ በኦዲቱ የተገኙት ስህተቶች እንዲታረሙ ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

## 3. <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

### 3.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በሙሉ በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር በሰኔ 30/2002 በተከፋይ ሂሣብ ከተያዘው ገንዘብ ውስጥ ብር 9,765.06 "ለሠራተኞች የሚከፈል ደሞወዝ" ተብሎ የተያዘ ቢሆንም ገንዘቡ ለነማን እንደሚከፈል እንደማይታወቅና እንዳልተለየ ለመረዳት ተችሏል፡፡ አሠራሩ ከደንብ ውጪ ሲሆን፣

ምክንያቱም በIBEX ሶፍትዌር ችግር እንደሆነ ታውቋል፡፡ የሶፍትዌሩ ችግር ተወግዶ ሂሣቡ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

- በሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ከ10 ዓመታት በላይ አለአግባብ የተያዘና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ ብር 10,776. ተገኝቷል፡፡ በሂሣቡ ላይ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡
- በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ለጡረታ ተከፋይ የሂሣብ መደብ 5003 ላይ ከሚታየው ገንዘብ ብር 14,107.73 ውስጥ ብር 6392.43 ለረጅም ጊዜ ለሚመለከተው አካል እንዳልተከፈለ ለቀሪውም ብር 7,715.30 ማስረጃ ስላልቀረበ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በቅዱስ ጴጥሮስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የ2001 በጀት ዓመት በተከፋይ ሂሣብ ሪፖርቱ ላይ የተመለከተው የችሮታ ጊዝ ተከፋይ ሂሣብ ብር 30,299.59 በ2002 በጀት ዓመት ውስጥም ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡
- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ በ2001 በጀት ዓመት በተከፋይ የሂሣብ መደብ 5003 የተመለከተው ገንዘብ ብር 125,146.77 በ2002 በጀት ዓመትም ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ቀርቷል፡፡

3.2 <u>ያልተመዘገበ የተከፋይ ሂሣብ</u>

- በአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለቅድሚያ ቀረጥ ብር 596.00 የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,765,044.88 ተሰብስቦ በመዝገብና በሌጀር ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡
- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 209,223.17 ተሰብስቦ ለገቢዎችና ለጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ የተደረገ ቢሆንም ሂሣቡ በመዝገብ፣ በሌጀር ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም ለኮሌጆች የተከፈለም ተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 1,621,472.48 በመዝገብና በሌጀር እንዳልተመዘገበ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር ከተጨማሪ እሴት ታክስና ከቅድሚያ ታሪፍ ግብር ከጨዋታዎች እና ከልዩ ልዩ በጎ አድራጊ ድርጅቶች

የተሰበሰበ ብር 408,451.84 ለሚመለከተው አካል የተከፈለ ቢሆንም ሂሣቡ እንዳልተመዘገበ ለማወቅ ተችሏል፡፡

3.3 <u>አለአግባብ የተያዘ የተከፋይ ሂሣብ</u>

- በአማኑኤል የአእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 10,000.00 የተከፋይ ሂሣብ የወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር ተጠቅሶ በሌጀር ላይ ተመዝግቦ የሚገኝ ቢሆንም፣ የተጠቀሰው ሠነድ ሊቀርብ ባለመቻሉ የሂሣብ አያያዝ አጠራጣሪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮጀክት ማስተባበሪያ ኮሌጆች ከውስጥ ገቢያቸው ወጪ በማድረግ ከፈፀሙት የዕቃና የአገልግሎት ግዢ ቀንሰው ያስቀሩት ግብር 107,103.32 በሂሣብ መደብ 5035 በተከፋይነት መያዝ ሲገባው በሂሣብ መደብ 1489 አለአግባብ በገቢ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

- በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት ላይ በሂሣብ መደብ 4203 ብር 23,665.99 እና በተከፋይ ሪፖርት ላይ ደግሞ በሂሣብ መደብ 5035 በዴቢት ባላንስ ብር 23,487.72 ተይዞ ተገኝቷል፡፡

  መ/ቤቱ የሚዛን ልዩነቱ ሊከሰት የቻለው በአመዘጋገብ ስህተት ሳይሆን ከኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በመነሻነት የተረከበው ሂሣብ መሆኑን ገልጿል፡፡

ተከፋይ ሂሣቦች ለሚመለከተው አካል እንዲከፈሉ፣ የአሠራር ግድፈቶቹ እንዲስተካከሉና ለወደፊትም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ</u>

4.1 <u>ያልተሰበሰበ ታክስ</u>

በመንግሥት ደንብ መሠረት የመንግሥት መ/ቤቶች፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የንግድ ትርፍ ግብር መክፈል ከሚገባቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች አገልግሎት

ወይም ዕቃ ሲገዙ ታክሱን ሰብስበው በወቅቱ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- ከግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮጀክት ማስተባበሪያ ከተለያዩ የግል ድርጅቶች ልዩ ልዩ ዕቃዎች በተገዙበት ወቅት በድምሩ ብር 42,978.50 ታክስ ያልተቀነሰ ሲሆን፣ ከምግብ አቅርቦት ክፍያ ላይ የተቀነሰው ታክስ ደግሞ ተገቢው ደረሰኝ ሳይቆረጥለት በነጭ ወረቀት የተሰበሰበ ከመሆኑም በላይ ገንዘቡም ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ አልተደረገም፡፡
- የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል ብር 24,117.91 ከብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ደግሞ ብር 553,875.74 በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ ድርጅቶች የዕቃና የአገልግሎት በገዙበት ጊዜ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሳይቀንሱ ለሻያጮቹ መክፈላቸውን ታውቋል፡፡ በተጨማሪም የብሔራዊ ሰው ሠራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ለምክር አገልግሎት ከከፈለው ክፍያ ውስጥ ብር 1,383.88 የቅድሚያ ንግድ ትርፍ ግብር ቀንሶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ ሲገባው ታክሱን እንዳልቀነሰ ታውቋል፡፡
- ከኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትም ተቀንሶ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ገቢ መሆን የነበረበት ብር 1,802.00 የቅድሚያ ንግድ ትርፍ ግብር እንዲሁም ብር 9,680.00 የተጨማሪ እሴት ታክስ ተገኝቷል፡፡

### 4.2 ተገቢ ያልሆኑ ደረሰኞች

የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ለሬዲዮ አገልግሎት ከከፈለው ገንዘብ ውስጥ ብር 15,000.00 እንዲሁም የሆልቲካልቸራል ኤጀንሲ ፊልም ለማሠራት ከከፈለው ገንዘብ ውስጥ ብር 8,234.08 ለተጨማሪ እሴት ታክስ እንደተከፈለ የሚገልፁ ደረሰኞች የቀረበ ቢሆንም ደረሰኞቹ ለተጨማሪ እሴት ታክስ መክፈያ የተዘጋጁ ሆነው አልተገኙም፡፡

ለወደፊቱም የተጨማሪ እሴት ታክስና የቅደሚያ ንግድ ግብር ተሰብስቦ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል በወቅቱ ፈሰስ መደረግ እንዳለበት፣ እንዲሁም ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ማስረጃነት የሚቀርቡ ደረሰኞች ሁሉ ለተጨማሪ

እሴት ታክስ መሰብሰቢያ የተፈቀዱት ብቻ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

5. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

5.1 <u>በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ ገቢ</u>

በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኘሮጀክት በ2001 በጀት ዓመት ከአርዳይታ የግብርና ኮሌጅ የተሰበሰቡ ብር 474,840.44 ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ የተደረገው በየካቲት 2002 ዓ.ም እንደሆነ ታውቋል፡፡

5.2 <u>በዕቅድ ያልተያዘ ገቢ</u>

የሚሰበሰበው ገቢ በዕቅድ የሚያዝ መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት፣

- የሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር
- የቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
- የአማኑኤል አእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
- የኢትዮጵያ የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር እና
- የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

የሰበሰቡት ገቢ በቅድሚያ በተዘጋጀ ዕቅድ መሠረት ያለመሆኑ ታውቋል፡፡

5.3 <u>የገቢ ደረሰኝ ሳይዘጋጅ የተሰበሰበ ገቢ</u>

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ የተሰበሰበው ብር 10,000.00 ተገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥለት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶቹ ገቢያቸውን በዕቅድ እንዲሰበስቡ፣ የሰበሰቡትን በተገቢው ጊዜ ፈሰስ እንዲያደርጉ እንዲሁም ለሰበሰቡት ገቢ የገቢ ደረሰኝ እንዲያቀርቡ አሳስበናል፡፡

6. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

6.1 <u>ያለጨረታ የተፈፀመ ግዢ</u>

ሐምሌ 1997 በወጣው የግዥ አፈፃፀም መምሪያ መሠረት ከብር 100,000 በላይ ለሚያወጣ ግዥ በግልፅ ጨረታ መፈፀም እንደሚገባው ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ፣

- በአማኑኤል አእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለሕሙማን የሚሆን ልዩ ልዩ ምግቦች በብር 448,648.67 የተፈፀመ ቢሆንም በጨረታ የተፈፀመ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሰነዶች አልተገኙም፡፡
- በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖናሎጂ ኢንስቲትዩት ለእንስሳት መኖ የሚሆን ሣር በቤልር ለማሰር ግልፅ ጨረታ ሳይካሄድ ብር 100,332.75 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳሬክቶሬት የ2002 በጀት ዓመት ሊጠናቀቅ አንድ ወር ከአሥር ቀን ሲቀር፣ ለአደጋ ጊዜ መጠባበቂያ የሚሆኑ የክምችት ዕቃዎችን አስቸኳይ በሚል በአዋጅ ቁጥር 430/97 ምዕራፍ 4 አንቀፅ 27 "ፊ" መሠረት በማድረግ በጨረታ ኮሚቴ ውሳኔ የብር 3,911,098.70 የመጠባበቂያ ክምችት ዕቃዎች ግዢ ተፈፅሟል፡፡ ይሁን እንጂ ግዥው የተፈፀመው አስቸኳይ በመሆኑ ሳይሆን የሒሳብ መዝጊያ ወቅት በመድረሱ ምክንያት እንደሆነ የታወቀ ሲሆን፣ ግዥው በበጀት ዓመቱ ውስጥ በማንኛውም ጊዜ ሊከናወን ይችል እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

- በሆልቲካልቸራል ልማት ኤጀንሲ ለማሠልጠኛ ማዕከል ግንባታ ወጪ ሆኗል ተብሎ በወጪ የተመዘገበው ብር 1,399,318.10 ያለ ጨረታ መፈፀሙ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም ኤጀንሲው የዶክሜንተሪ ፊልም ለማሠራት ለከፈለው ብር 252,511.76 ጨረታ አላካሄደም፡፡በሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ለሬዲዮ የአየር ጊዜ ግዢ የተከፈለው ብር 855,995.00 ያለ ጨረታ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

መ/ቤቶቹ በመንግሥት የግዥ ደንብ መሠረት በጨረታ እንዲገዙና ደጋፊ ሰነዶችም በጥንቃቄ እንዲቀመጡ አሳስበናል፡፡

## 6.2 <u>ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ የተፈፀመ ግዢ</u>

በመንግሥት ደንብ መሠረት በዋጋ ማወዳደሪያ ለሚፈፀሙ ግዢዎች በቅድሚያ ከሦስት ያላነሱ ዕቃ ወይም አገልግሎት አቅራቢዎችን ዋጋ ማወዳደር እንደሚገባ

ያሳስባል፡፡ ሆኖም ከዚህ በታች በተመለከቱት መ/ቤቶች የተፈፀሙት ግዢዎች ያለዋጋ ማወዳደሪያ እንደሆነ በኦዲቱ ጊዜ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት ቀለምና ሲባጎ በብር 11,191.80 ሲገዛ፣

- በሆልቲካልቸራል ኤጀንሲ፣ በመንግሥት የግዥ መመሪያ የተደነገገውን በዕቅድ ውስጥ ያልተካተቱና ዋጋቸው ከብር 100 (አንድ መቶ ብር) ያልበለጡ ግዥዎችን ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ ለመግዛት እንደሚቻል የግዥው ድምር በአንድ በጀት ዓመት ከብር 4,000 (አራት ሺህ ብር) መብለጥ እንደሌለበት የሚገልፀውን ደንብ መሠረት በማድረግ ነው ተብሎ የብር 24,620.10 ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ የተገዙ ዕቃዎች ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ የተገዙት ዕቃዎች ከብር 100.00 በላይ የሚያወጡ ሆነው በመገኘታቸው፣ አሠራሩ የመንግሥት ደንብን የጣሰ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ለዶክመንተሪ ፊልም ለማባዣ ለአንድ ድርጅት የከፈለው ብር 16,928.00 ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ መሆኑ ታውቋል፡፡
- የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል፣ አንድ የመሥሪያ ቤቱን ተሽከርካሪ መኪና ለማስጠገን የተከፈለ ነው ተብሎ በወጪ የተያዘው ብር 146,809.51 በቅድሚያ የዋጋ ማወዳደሪያ ያልተሰበሰበ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡
- በግብርና ሚኒስቴር ለተሽከርካሪ ጥገና ተከፍሏል ለተባለው የብር 32,995.49
- በጤና ጥበቃ ሚ/ር
  - ለቀለም ቅብ ሥራ ተብሎ በወጪ የተመዘገበው ብር 3,000. እና
  - ለተሽከርካሪ መኪናዎች ጥገና ተብሎ የተከፈለው ብር 65,000. ያለዋጋ ማወዳደሪያ የተፈፀመ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በብር 26,000.03 ለተሽከርካሪ መኪናዎች ጥገና ተብሎ በወጪ የተያዘው ሂሣብም ሁለት የዋጋ ማወዳደሪያ ብቻ የቀረበለት ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በቅዱስ ጴጥሮስ ቲቤ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ጥገና የተከፈለው ብር 36,902.16 እንዲሁም በብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር

ለግንባታ ዕቃ ግዢና ለዕድሳት ሱፐርቪዥን የተከፈለው ብር 48,740.00 ያለ ዋጋ ማወዳደሪያ እንደሆነ ታውቋል፡፡

ለወደፊቱም ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶቹ በመንግሥት ደንብ መሠረት የዕቃና የአገልግሎት ግዢዎችን ዋጋ በማወዳደር እንዲፈፅሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 6.3 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት</u>

ማንኛውም ዕቃ ሲገዛ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል 19 እንዲቆረጥለት ዕቃ ግምጃ ቤት እንዲገባ የመንግሥት ደንብ ያዛል ይሁን እንጂ በሆልቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ በብር 8,510.00 ለተገዛው ኬብል የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ንብረቶቹ ደረሰኝ እንዲቆረጥላቸው ለወደፊቱም ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

## 6.4 <u>ተገቢ ባልሆነ የወጪ ሂሣብ መደብ የተያዙ ሂሣቦች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ምርመራ ሲደረግ፣

| | ብር |
|---|---|
| - በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት | 5,231.00 |
| - በሕብረት ሥራ ኤጀንሲ | 51,905.60 |
| - በሆልቲካልቸራል ልማት ኤጀንሲ | 69,516.60 |
| - በኢትዮጵያ ቴሌኮምንኬሽን ኤጀንሲ | 26,881.45 |
| - በጤና ጥበቃ ሚ/ር | 19,537.00 |
| - በግብርና ሚኒስቴር | 14,322.50 |
| - በውኃና ኤነርጂ ሚኒስቴር | 31,806,939.15 |
| - በአማኑኤል አእምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል | 13,532,010.71 |
| - በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና | 212,883.73 |

- በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ
  25,451.91
- በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ማከፋፈያ ማዕከል 1,516.90
- በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር 2,133.98

የሆኑ ሂሣቦች በትክክለኛ የወጪ ሂሣብ መደባቸው ሳይመዘገቡ ተገኝተዋል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

## 6.5 ያለበጀት ዓመቱ የተያዘ

በአንድ የበጀት ዓመት የተፈፀመ ወጪ በበጀት ዓመቱ ሂሣብ ውስጥ እንዲካተት የመንግሥት ደንብ ያዛል፡፡ ሆኖም፣

- በጤና ጥበቃ ሚ/ር ለጄኔተሮች መግዣ
  በ2001 በጀት ዓመት የተከፈለው ብር 1,653,717.55 ፣
- በግብርና ሚኒስቴር በ2001 በጀት ዓመት
  ወጪ ለተደረገ " 146,597.07፣
- የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ዳይሬክቶሬት በ2001 በጀት
  ዓመት የተለያዩ ዕቃዎችን ለመግዛት ወጪ ያደረገው " 1,144,500.00 ፣
- የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ በ2001 በጀት ዓመት ያወጣው " 78,794.68

ወጪው በ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ውስጥ አለአግባብ ተካቶ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶቹ ለወደፊት የበጀት ዓመቱን ወጪ በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብቻ ለማካተት ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

## 6.6 ያለ ማስረጃ የተመዘገበ የወጪ ሂሣቦች

በወጪ የተመዘገበው ሂሣብ ሁሉ ተገቢው የወጪ ማስረጃ ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት፣

- በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት በቼክ ወጪ ለሆነ ብር 4,726.00 ማስረጃ አልቀረበም፤ በተጨማሪም ለብር 5,749.00 ወጪ፣ ከወጪ ቫውቸሩ ጋር ማስረጃው ተያይዞ አልተገኘም፡፡

- በሕብረት ሥራ ኤጀንሲ የብር 13,376.00 ያለማስረጃ እንደተመዘገበ ለማወቅ ተችሏል፡፡

መ/ቤቶቹ ተመሣሣይ ስህተት እንዳይደገም ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

## 6.7 የመንግሥት ደንቦችን እና መመሪያዎችን ያላሟሉ የኮንትራክታዊ አገልግሎት ክፍያዎች

ኦዲት የተደረጉት መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ ውስጥ የተለያዩ ሥራዎችን ለማሠራት ለኮንትራክተሮች የከፈሉት ገንዘብ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያዎችና ደንቦች መሠረት የተከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት መጋዘኖችን ለማሠራት ኃይሉ ባሬሎ ከተባለው ድርጅት ጋር የብር 550,977.94 ኮንትራት ተዋውሎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣
  - ድርጅቱ በዋጋ ማወዳደሪያ ካቀረበው ዝርዝር ሥራ (ስፔስፍኬሽን) ውጪና ሥራው እንዲሠራ በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቀድ ድርጅቱ ተጨማሪ ሥራ ለሠራበት ተብሎ ብር 108,330.00 (የጠቅላላው ዋጋ 18.6% ) አለአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
  - የሥራ ተቋራጩ ድርጅት በወቅቱ በሠራው ሥራ መጠን ልክ በተቆጣጣሪ መሐንዲስ በተረጋገጠ የምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት) መሠረት መከፈል ሲገባው ያለሠርተፊኬት ብር 48,000 ተከፍሎታል፡፡
  - በገ/ኢ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት የቅድሚያ ክፍያ መተኪያ 20% ሳይቀነስ ለድርጅቱ ተከፍሏል፡፡
  - በውሉ ድርጅቱ ውሉ በተፈረመ በዘጠና ቀናት ውስጥ (በሦስት ወር) ሥራውን አጠናቆ መጋዘኖችን ለማስረከብ ግዴታ ገብቶ የነበረ ቢሆንም፤ ርክክቡ ሳይደረግ ከ1 ዓመት ከ4 ወር በላይ ያለፈው መሆኑ ታውቋል፡፡
- የውኃና ኤነርጂ ሚኒስቴርም በውኃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ላሠራው ሥራ ከደንብ ውጪ የተሠራው ሥራ መጠን በምስክር ወረቀት ሳይረጋገጥ ብር

112,510,639.47 እንዲሁም ከክፍያ መቀነስ የነበረበት ብር 20,199,930.11 በድምሩ ብር 132,710,589.58 ለባለሥልጣኑ ከፍሏል፡፡

- የሆልቲካርቸራል ልማት ኤጀንሲ የመ/ቤቱን ሕንፃ ፖርቲሽን ለማሠራት ታደሰ በርሄ የሕንፃ ሥራ ተቋራጭ ከተባለው ድርጅት ጋር ሳይፈቀድና የተጨማሪ ሥራ የውል ስምምነት ሳይኖር ተቋራጩ ባቀረበው ዋጋ መሠረት ብቻ "ለተጨማሪ ሥራ ማሠሪያ" ተብሎ ብር 29,239.00 ከዋናው ውል 180% በላይ ለድርጅቱ ተከፍሏል፡፡ በተጨማሪም ለሚያሠራው የሥልጠና ማዕከል ግንባታ ለምክር አገልግሎት በብር 60,720. በለስ ኮንሰልቲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ከተባለው ድርጅት ጋር ተዋውሎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የአገልግሎት ግዢው የተፈፀመው ስለሚሠራው ዝርዝር ሥራ (specification) በኤጀንሲው በጽሁፍ ሳይዘጋጅ ከመሆኑም በተጨማሪ አሸናፊው ድርጅት የተመረጠው የቴክኒካል ውድድርን ሳያካትት በአቀረበው የገንዘብ መጠን ብቻ በመሆኑ እንዲሁም የውል ማስከበሪያ ዋስትና ብር 6,072 እንዲያዝ ባለመደረጉ ክፍያው የመንግሥትን ደንብ ያልተከተለ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- የብሔራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል ሊያስገነባ ለአሰበው ሕንፃ ዲዛይን እንዲሠራለት ከኮንስራክሽን ዲዛይን አክሲዮን ማኅበር ጋር በገባው ውል መሠረት፣ የጥናትና የአፈር መርምር ሥራ እንዳለቀ 30% ለመክፈል ቀሪውን ደግሞ ሥራው እንደተጠናቀቀ ክፍያውን ለመፈፀም ስምምነት ላይ ተደርሶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ሥራው ለመጠናቀቁ ማስረጃ ሳይቀርብ ለድርጅቱ ሙሉ ገንዘቡን ብር 199,996.60 እንደከፈለ ታውቋል፡፡
- የውኃና ኤነርጂ ሚኒስቴር ስለተሠራው ሥራ መጠንና ጥራትና በሚያረጋግጥ ሕጋዊ በሆነ አማካሪ ድርጅት የተዘጋጀ የክፍያ የምስክር ወረቀት ሳይኖር ለትግራይ ውኃ ኮንስትራክሽን ድረጅት ብር 17,103,372.07 መክፈሉ ታውቋል፡፡
- ብሔራዊ ሰው ሠራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ለኮርማዎች መዝናኛ ብረት ግንባታ ከዳኛቸው ገመቹ ጠቅላላ ብረታ ብረት ሥራ ከተባለው ድርጅት ጋር ተዋውሎ የነበረ ቢሆንም፣

- በውሉ መሠረት ከጠቅላላው ዋጋ ብር 89,916.00 ውስጥ ድርጅቱ የሠራው ሥራ 50% ሲጠናቀቅ ብር 44,958.00 መከፈል ሲገባው ብር 65,650 እና
- በውሉ ውስጥ ስለተጨማሪ ሥራ የተቀመጠ ስምምነት ሳይኖር እና አግባብ ባለው ባለሥልጣን ሳይፈቀድ ተጨማሪ ሥራ ድርጅቱ ለሠራበት ተብሎ ብር 36,662 (የዋናው ዋጋ 41 %) በመከፈሉ

ወጪው ከደንብ ውጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ባወጣው መመሪያ መሠረት ለፕሮጀክቶች ግንባታ ቅድሚያ ገንዘብ ሊከፈል ወደፊት የሥራ ተቋራጩ በሚያቀርባቸው የክፍያ የምስክር ወረቀት መሠረት እየተቀነሰ፣ ተመላሽ የሚሆን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

  - የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ዳይሬክቶሬት አድማስ ጄኔራል ትሬዲንግ ለተባለው ተቋራጭ የከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ብር 2,035,419.40 እንዲሁም እያሱ መኩሪያ ለተባለው ተቋራጭ የከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ብር 754,349 እንዲሁም በብር 1,121,400.15 ለእንስሳት ህክምና አገልግሎት የሚውሉ መድሃኒቶች ግዥ የፈፀመ ቢሆንም መድሃኒቶቹ ለተፈለገው ዓላማ ለመዋላቸው ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
  - የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር ለፕላስቲክና የፒቪሲ ፕሮፋይል ፋብሪካ፣ ለተገጣጣሚ የሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት እንዲሁም ለሴንቴክ ኢትዮጵያ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የከፈለውን የቅድሚያ ክፍያ ብር 3,518,725.92 በወጪ መዝግቧል፡፡
  - የሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል ለኤን.ዋይ.ጂ አጠቃላይ ኮንትራክተር ለተባለው ድርጅት የከፈለው የቅድሚያ ክፍያ ብር 3,769,066.30 በወጪ እንዲመዘገብ ተደርጓል፡፡
  - የውኃና ኤነርጂ ሚኒስቴርም በተሰብሳቢነት መያዝ የሚገባቸውን የቅድሚያ ክፍያዎች ብር 115,692,327.25 በወጪ መዝግቦ ተገኝቷል፡፡
  - የሆልቲካልቸራል ልማት ኤጀንሲ ደግሞ ለደጀን አቪሽን ኢንጅነሪንግ የከፈለው ቅድሚያ ክፍያ ብር 554,692.00 በደንቡ መሠረት 30% ሳይሆን

50% እንደሆነ ታውቋል፡፡ ኤጀንሲው ክፍያውን በወጪው ከመመዝገቡም በላይ ድርጅቱ ከቅድሚያ ክፍያው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ዋስትና እንደያቀርብ አልተደረገም፡፡

ከላይ የተመለከቱት መንግሥታዊ መ/ቤቶች ለወደፊቱ ለልዩ ልዩ ተቋራጮች የሚከፍሉት ገንዘብና የሂሣብ አያያዝ በመንግሥት ደንብ መሠረት እንዲፈፀም ከፍተኛ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ አሳስበናል፡፡

## 6.8 ሌሎች ከደንብ ውጪ የተፈፀሙና የተመዘገቡ ክፍያዎች

ስለ ልዩ ልዩ የወጪ ሂሣቦች አከፋፈልና አያያዝ የወጡ ደንቦችን ያላሟሉ የሚከተሉት ሁኔታዎች በተለያዩ ኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ውስጥ ተገኝተዋል፡፡

- በኢትዮጵያ ኤነርጂ ማዕከል የተከናወነው የብር 6,900.00 የካዝና ግዢ በጀት ያልተያዘለት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህም ሌላ ማዕከሉ የተለያዩ ወንበሮችን በብር 22,535.00 ሲያስጠግን ጥገናው በትክክል የተከናወነ በመሆኑ ሳይረጋገጥ ክፍያውን ፈጽሟል፡፡ ከዚህም ሌላ ከታህሣሥ 1 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ለለቀቁ ሠራተኞች የጥርና የየካቲት ወር አበል ብር 3,657.30 እንዲሁም ለሦስት ሠራተኞች "የዕድገት ጭማሪ" ተብሎ ብር 440.00 በድምሩ ብር 4,103.30 አለአግባብ እንደተከፈለ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- በሆልቲካርቸራል ኤጀንሲ በብር 13,879.50 የተገዛው 75 ኩንታል ሲሚንቶ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ የተደረገ ቢሆንም፣ ሲሚንቶው ወጪ የተደረገው ሥልጣን በተሰጠው ኃላፊ ሳይፀድቅና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል 22 ሳይቆረጥለት ነው፡፡
- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣኖች መከፈል ስላለበት ጥቅማ ጥቅምና አበል ባወጣው መመሪያ ውስጥ ከተቀመጠው ተመን በላይ፣
  - ለቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ እና የምግብ ዋስትና ማስተባበሪያ ከፍተኛ ኃላፊና ሾፌራቸው በመስክ ሥራ ለቆዩበት ጊዜ ብር 1,327.60 በብልጫ ተከፍሏቸዋል፡፡

- ለትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ር ከፍተኛ ኃላፊና አጃቢያቸው ለመስክ ሥራ ብር 3,016.31 በመመሪያው ከተቀመጠው በላይ ተከፍሏል፡፡ ከዚህም ሌላ ሌሎች የሚኒስቴር መ/ቤቱ ልዩ ልዩ ኃላፊዎች ለተጠቀሙበት የስልክ አገልግሎት ከተከፈለው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,642.70 ከመመሪያው ተመን በላይ እንደሆነ ታውቋል፡፡ ለሌሎች ሁለት የመ/ቤቱ ሠራተኞች ደግሞ ወደ ውጭ አገር በሄዱበት ጊዜ ከመንግሥት ከተፈቀደው አበል በላይ 320 (ሦስት መቶ ሃያ) የአሜሪካን ዶላር ተከፈሏል፡፡

- የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል ሠራተኞች ቅዳሜ፣ እሑድ፣ ምሽትና በበዓል ቀናት ለሠሩበት የትርፍ ሰዓት ሥራ ተብሎ ብር 79,404.92 ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል ሳይፈቀድ ተከፍሎ ተገኘቷል፡፡
- በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት ከባንክ ወጪ የተደረገ ገንዘብ ብር 88,655.87 ከባንክም ከሳጥንም ወጪ እንዲሆን ተደርጎ በድጋሚ አለአግባብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የውኃና ኤነርጂ ሚ/ር ለውኃ ኮንስትራክሽን ባለሥልጣን ሚያዝያ 30 ቀን 2001 ዓ.ም ብር 30,000,000 ብድር የሰጠ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይሁን እንጂ ሂሣቡ በሙሉ በተሰብሳቢ ሂሣብነት መያዝ ሲገባው በበጀት ዓመቱ መዝጊያ ብር 18,898,369.61 ሳይመለስ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የሕብረት ሥራ ኤጀንሲ ለደብረዘይት ሥራ አመራር ኢንስቲዩት በብልጫ የከፈለውን ገንዘብ ብር 14,900 ማስመለስ ሲገባው አላስመለሰም፡፡
- ለሆልቲካልቸራል ልማት ኤጀንሲ ሠራተኞች ቅዳሜና እሁድ ለሠሩበት ተብሎ ብር 2,750 የትፍር ሰዓት ክፍያና እንዲሁም ለመስተንግዶ ተብሎ ብር 2,271.33 የተከፈለው ክፍያው ከደንብ ውጭ ለመሆኑ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም አንድ የኤጀንሲው ሠራተኛ አዋሳ መስክ ሥራ ላይ በነበሩበት ጊዜ የብር 1000 ነዳጅ የቀዱበት ማስረጃ አቅርበው ሂሳቡ የተወራረደ መሆኑ፣ እንዲሁም ሌላ አንድ የኤጀንሲው ሠራተኛ ለውሎ አበልና ለነዳጅ ለተከፈላቸው የቀረበው የብር 1,940.10 ማስረጃዎች ግለሰቡ የውሎ አበል ቅጽ

ላይ ከሞላቸው ቦታዎች ጋር የማይጣጣም ስለሆነ የክፍያውን ትክክለኛነት (አግባብነት) ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የኢትዮጵያ ቴሌኮምኒኬሽን ኤጀንሲ የመንግሥት መመሪያ ከሚፈቅደው በላይ ለውኃና ለምግብ ተብሎ ለሠራተኞች 5,266.83 ከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም ከላይ የተገለፁትን የአሠራር ግድፈቶችን በተመለከተ ኦዲት የተደረጉት መ/ቤቶች ተመላሽ መሆን የሚገባውን ገንዘብ እንዲያስመልሱ፣ መስተካከል የሚገባውን አሠራር እንዲያርሙ እንዲሁም ተመሳሳይ ከደንብ ውጪ የሆነ አሠራር እንዳይደገምና እንዲጠናቀቁ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 7. ንብረት

### 7.1 የንብረት ቆጠራ

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት የመንግሥት ንብረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ተቆጥሮ በመዝገብ ከተመለከተው ከወጪ ቀሪ ጋር መመሳከር አለበት፡፡ ይሁን እንጂ፣

- በሆልቲካልቸራል ልማት ኤጀንሲ
- በሕብረት ሥራ ኤጀንሲ
- በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ
- በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ
- በቡና ጥራት መቆጣጠሪያ ማዕከል
- በፈንድ አስተዳደር ጽ/ቤት
- በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
- በብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ኢንስቲትዩት
- በውሃ ልማት ፈንድ ጽ/ቤት
- በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን
- በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት
- በብሔራዊ የእንስሳት ጤና ምርምር ማዕከል

የንብረት ቆጠራ እንዳልተካሄደ ታውቋል፡፡

በቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የቋሚ ንብረት ሙሉ በሙሉ እንዳልተቆጠረ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በብሔራዊ ሜትሮሎጂ የቋሚ ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ቆጠራው ከመዝገብ (ሌጀር) ጋር አልተመሳከረም፡፡ በብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር ደግሞ ቋሚ ቆጠራ ተደርጎ ከመዝገብ ጋር የተመሳከረ ቢሆንም በብልጫና በማነስ ታዩት ዕቃዎች ላይ እርምጃ አልተወሰደም፡፡

## 7.2 <u>ስለተሽከርካሪ መኪናዎች</u>

### 7.2.1 <u>በብልሽት ለረጅም ጊዜ የቆሙ ተሽከርካሪዎች</u>

- በሠራተኛና ማኀበራዊ ጉዳይ ሚ/ር 18
- በኢትዮጵያ ጂዮሎጂካል ሰርቬይ 34
- በብሐራዊ የእንስሳት ጤና ምርመር ማዕከል 1
- በማዕድን ሚ/ር 5
- በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ 8
- በጤና ጥበቃ ሚ/ር 9
- በቅዱስ ጴጥሮስ ቲቪ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል 5 /1 ሞተር ሳይክል/
- በብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፖዎች አስተዳደር 2
- በኢትዮጵያ የምግብ መድሃኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር 4
- በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ 13
- በወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር 9
- በኢትዮጵያ የገጠር ልማትና ኤጀንሲ ማዕከል 8

ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ለረጅም ጊዜ ቆመው እንደሚገኙ ታውቋል፡፡

### 7.2.2 <u>የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው</u>

በመሥሪያ ቤቱ ስም የሚገለፅ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ሳይኖራቸው በብሔራዊ የእንስሳትና ጤና ምርምር ማዕከል 11፣ በኢትዮጵያ ስጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት 8 ፣ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር 2 ፣ በብሔራዊ ሰው ሠራሽ የእንስሳት ማራቢያ ማዕከል 7 ትራክተሮችና 4 ሞተር ብስክሌቶች ተሽከርካሪዎች ተገኝተዋል፡፡

7.2.3 <u>የቻሲና የሞተር ቁጥራቸው የማይታወቅ</u>

- በብሔራዊ የመጠባበቂያ ነዳጅ ዴፓዎች አስተዳደር 2
- በቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ሆስፒታል 8

ተገኝተዋል፡፡

## 7.3 <u>ያለአግባብ የቀመጡ ንብረቶች</u>

አገልግሎት ላይ መዋል፣ መሸጥ ወይም መወገድ የሚገባቸውና አለአግባብ የተቀመጡ ንብረቶችም በሚከተሉት መ/ቤቶች ውስጥ ተገኝተዋል፡፡

- በአላጌ ግብርና ቴክኒክ ኮሌጅ ከ1973 ጀምሮ መጋዘን ውስጥ የተቀመጡ በተቀደደ ጆንያ ተቀምጦ እየቀለጠ ያለ ስኳር ፣ልዩ ልዩ የመመገቢያ ዕቃዎች ከ1,000 በላይ የሚሆኑ የስፌት መኪናዎችና አልጋዎች ተገኝተዋል፡፡
- በቅድሚያ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ዳይሬክቶሬት በሕብረት ሥራ ኤጀንሲ፣ በከተማ ልማት ሚ/ር በትራንስፖርትና መገናኛ ሚ/ር፣ በኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኤጀንሲ የተለያዩ የተሽከርካሪ መኪናዎች፣ የመለዋወጫ ዕቃዎች፣ ኮምፒዩተሮችና አክሰሰሪዎች ጎማዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ የፋክስ ማሽኖች፣ ፕሪንተሮች፣ የፎቶኮፒ ማሽኖችና የመሳሰሉት አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች እንዲወገዱ ሳይደረግ ተቀምጠው ተገኝተዋል፡፡
- በብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል፣ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ 1 የሣር ማሠሪያ ማሽን፣ 5 ትራክተሮች ለወተት ምርት የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ መሣሪያዎች፣ ማቀዝቀዣ፣ ፍሪጅ የመሳሰሉት የለአገልግሎት ከአሥር ዓመት በላይ ተቀምጠው ተገኝተዋል፡፡

## 7.4 <u>ተመላሽ ያልተደረገ ንብረት</u>

በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲና በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል መ/ቤቶችን የለቀቁ ሠራተኞች በውሰት የወሰዱትን ንብረት ተመላሽ እንዳላደረጉ ታውቋል፡፡

### 7.5 ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያለመሰጠቱ

በሆልቲካልቸራል ልማት ኤጀንሲ፣ በከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚ/ር በመጠባበቂያ የምግብ ክምችት አስተዳደር በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ (በከፊል) የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ሳይሰጣቸው ተገኝተዋል፡፡

### 7.6 የንብረት ገቢና ወጪ ያልተቆረጠላቸውና በንብረት መዝገብ ያልተመዘገቡ ንብረቶች

በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል በብር 8,868,553.64 የተገዛ ቋሚ ዕቃ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለትና በንብረት መዝገብ ያልተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ መሥሪያ ቤት ብር 25,313.13 የተገዛ ዩኒፎርምና በብር 40,560 የተገዛ ነዳጅ በንብረት መዝገብ እንዳልተመዘገበ ታውቋል፡፡

ኦዲት የተደረጉት መ/ቤቶች በመንግሥት ደንብ መሠረት መወገድ የሚገባቸውን ዕቃዎች እንዲያስወግዱ፣ ዓመታዊ ቆጠራ እንዲያካሂዱና ሌሎችም በደንቡ የተቀመጡትን እና ተግባራዊ መሆን የሚገባቸውን ሁኔታዎች ሁሉ እንዲያከናውኑ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 8. የበጀት ሂሣብ

### 8.1 ከበጀት በላይ የወጣ፣

የመንግሥት መ/ቤቶች በየበጀት አርዕስቱ (የሂሣብ መደብ) ከተመደበላቸው በጀት በላይ እንዳይጠቀሙ የመንግሥት የበጀት ደንብ ይደነግጋል፡፡ ሆኖም የጤና ጥበቃ ሚ/ር፣ የሂሣብ መደቡ ከተፈቀደለት በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 90,104.95 ከካፒታል በጀት ደግሞ ብር 3,023,108.37 በድምሩ ብር 3,113,212.82 ፣ የአማኑኤል አእምሮ ሆስፒታል ብር 1,091,220.03፣ የነዳጅ ዲፖዎች አስተዳደር ብር 565,044.47 የብሔራዊ ሜትሮሎጂ አጀንሲ ብር 62,322.05 እና የግብርና ሚኒስቴር ከካፒታል በጀት ብር 451,533.81 ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ እንዳወጡ በተካሄደው ኦዲት ተረጋግጧል፡፡

## 9 የውስጥ ኦዲት ድክመት

ኦዲት የተደረገት መ/ቤቶች ለዘረጉት የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያደርገው የውስጥ ኦዲት፣ ያለበት ሁኔታ ሲገመገም፣

- በቅዱስ ጴጥሮስ ቲቢ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል እና በኢትዮጵያ የምግብ መድሐኒትና ጤና ክብካቤ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን የውስጥ ኦዲት ክፍል የተቋቋመ ቢሆንም፣ ክፍሎቹ የኦዲት ባለሙያ እንደሌላቸው ታውቋል፡፡
- በአማኑኤል አእምሮ ሰፔሻላይዝድ ሆስፒታል የውስጥ ኦዲት ክፍሉ ለ2002 በጀት ዓመት የኦዲት ዕቅድ ያዘጋጀ ቢሆንም ዕቅዱ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

የውስጥ ኦዲት ክፍሎች የሰው ኃይል እንዲመደብላቸውና የተዘጋጀ ዕቅድ ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባው አሳስበናል፡፡

# ንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች

# ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2002/2003

# የኦዲት ዕቅድ ክንውንና ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን፣ እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ፣ የ35 መ/ቤቶች የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብን ኦዲት አድርገናል፡፡

ለሁሉም መ/ቤቶች ኦዲት በተደረገው ሂሣባቸው ላይ ያለንን አስተያየት የያዘ ሪፖርት ተልኳል፡፡ የተሰጠው አስተያየትም ሪፖርቶቹም ከግኝታቸው ባህርይ አንፃር ሲተነተኑ፣

- አልፎ አልፎ ሊጠቀሱ ከሚችሉ ጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ ያለበት አስተያየት የተሰጠባቸው (Except for Opinion) 4 መ/ቤቶች፣
- የጎላ ችግር ያለባቸው ሆነው በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት (Adverse opinion) የተሰጠባቸው 4 መ/ቤቶች፣
- አጥጋቢ ሆነው በመገኘታቸው ነቀፌታ የሌለበት አስተያየት (Clean opinion) የተሰጠባቸው 23 መ/ቤቶች እንዲሁም
- በሂሳባቸው ላይ አቀም መውሰድ ያልተቻለ በመሆኑ ----------- 4መ/ቤቶች ናቸው፡፡

## በኦዲት ሥራው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች

በኦዲት ሥራው የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ</u>

<u>የጥሬ ገንዘብ የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች</u>

**በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር**

- በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ መግለጫ ያልተደገፈ ብር 5,743,395.35
- በበጀት ዓመቱ በባንክ የተገኘ ገንዘብ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ ማድረግ ሲገባ ከመመሪያ ውጭ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የተደረገ " 27,818,846.01

በውጭ መልዕክተኞች /የውጭ ጉዳይ ሚ/ር/

- በውጭ ምንዛሪ ባንክ ያለ ገንዘብ /4102/ ተብሎ ሪፖርት የተደረገውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የባንክ ሂሣብ መግለጫ ያልቀረበለት " 159,179,199.23
- በ4103 የሂሣብ መደብ የባንክ የሂሣብ መግለጫ ያልቀረበለት " 139,149.59
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ መግለጫ ያልቀረበለት " 1,255,963.36

በቀድሞ ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ ሂሣብ መግለጫ ዜሮ ከወጪ ቀሪ እየታየ አላግባብ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የተደረገ " 1,226,057.00
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በቆጠራ ከተገኘው በማነስ ሪፖርት የተደረገ፡-
    - በፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት " 285,043.74
    - በኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ " 173,842.54

ከላይ ከተገለጹት 5 መ/ቤቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የሚገኝ ጥሬ ገንዘብ በውስጥ ኦዲተር ተቆጥሮ ማረጋገጫ ሊቀርብለት እንደሚገባ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት ላይ ለተመለከተው የባንክ ሂሣብ መግለጫዎቹ ለኦዲት በማስረጃነት መቅረብ እንደሚባቸው ጠቅሰን ይህም ባለመደረጉ የሂሣቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ ገልጾልናል፡፡ እንዲሁም በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ ያለ ገንዘብ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ /Blok/ መደረግ ሲገባው ከመመሪያ ውጭ ገንዘቡ ብሎክ ሳይደረግ ሪፖርት መደረጉ አግባብ አለመሆኑን፣ ለወደፊቱም አሰራሩ እንዲስተካከል በማነስ እና በባንክ ሳይኖር እንዳለ ሪፖርት ያደረጉት መ/ቤቶች የሂሣብ ማስተካከያ እንዲያደርጉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

- የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የጥሬ ገንዘበ ቆጠራ በስምንት የመ/ቤቱ ቅርንጫፎች ብር 5,743,395.35 ቆጠራ አለመደረጉን ጠቅሶ የኦዲተሮች እጥረት እንዳለበትና ለወደፊቱ አሠራሩን እንደሚያስተካክል ከላይ ስለተጠቀሰው ብር 27,818,846.01 በተመለከተ ብር 12,818,678.96 ከተሰዉ የሠራዊት አባላት ኪስ የተገኘ ገንዘብ ንብረት ሽያጭ ገንዘብ መሆኑን፣

ቀሪው ብር 14,671,646.41 ለገ/ኢ./ል/ሚ/ር ፈሰስ ያልተደረገና በ2003 ፈሰስ እንደማይደረግ ገልጿል፡፡ መ/ቤቱ ለላክነው የሥራ አመራር ሪፖርት በወቅቱ መልስ ባለመሰጠቱ በኦዲቱ ጊዜም ከአባላት ተገኘ የተባለውን ገንዘብ ማጣራት አልተቻለም፡፡ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውጭ መልዕክተኞች እና የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳዮች ዋና መምሪያ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት መልስ አልሰጡም፡፡ የቀድሞው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የመጨረሻው ሪፖርት ከተላከለት በኋላ በሰጠው መልስ ለወደፊቱ ሰኔ 30/2003 ባንክን በመጠየቅ የሚከናወን መሆኑን፣ የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ከሰኔ 28 እስከ ሐምሌ 5/2002 በፊት ወጪ አድርጐ በሣጥን ማስቀመጡን፣ ወጪው የ2002 በጀት ዓመት መሆኑን፣ ለበላይ ኃላፊዎች ሁኔታውን በማሳወቅ ሂሣቡ በ2002 መመዝገቡን ገልጿል፡፡

2. <u>ተሰብሳቢ ሂሣቦች</u>

2.1. <u>ውዝፍ የሠነድ /ተሰብሳቢ/ ሂሣብ</u>

| | | |
|---|---|---|
| በሀገር መከላያ ማኒስቴር | በድምሩ ብር | 117,063,096.11 |

ከ5-19 ዓመታት በተሰብሳቢ የተያዘ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

ዝርዝሩም፡-

| | | |
|---|---|---|
| - ከ1984 ጀምሮ ከ19 ዓመታት በላይ የቆየ | ” | 15,220,653.43 |
| - ከ1998 ጀምሮ ከ5 ዓመታት ከዕዞችና ምዝገባ የተመለከተ | ” | 19,840,719.35 |
| - በዕዞች መምሪያዎች ወዘተ የተመለከተ | ” | 287,466.99 |
| - በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ለተሰዉ የሠራዊት አባላት ቤተሰቦች ለ5 ክልሎች ከ1992-1996 በሰነድ የተሰጠ | ” | 1,327,070.34 |
| - በሚ/ር መ/ቤቱ ሥር ለሚገኙ ሶስት ድርጅቶች አላግባብ ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ /ያልተከፈለ ደመወዝ/ በብድር ተሰጥቶ በተሰብሳቢ የተያዘ | ብር | 79,278,186.00 |

- የውጭ መልዕክተኞች በሀገር መከላከያ ሚ/ር ስም በተሰብሳቢ የያዘውን ሂሣብ ሚ/ር መ/ቤቱ የማያውቀው መሆኑን ማረጋገጫ የሰጠበት ብር 3,321,728.46
- በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከ1995-2002 ለምርጫ ሥራ በሰነድ ተሰጥቶ ያልተወራረደ ”114,315,716.26
- በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ” 53,653.87
- በፌደራል ፖሊስ ” 134,149.50
- በፌደራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዘርፍ ” 541,610.40
- በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ” 1,341,609.86
- በብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ” 26,349.60
- በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት ” 129,520.74
- የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ” 86,022.13
- የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት ” 5,220.00

ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ፣ የውጭ መልዕክተኞች በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ስም የያዘው ተሰብሳቢ ሂሣብ ሚ/ር መ/ቤቱ ስለሂሣቡ የማያውቀው መሆኑ፣ በተለይ ሂሣቡ ለረጅም ዓመታት የቆየ በመሆኑ ሚ/ር መ/ቤቱ እንዲያውቀው አለመደረጉ የሚሲዮኖች ተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርቱ ትክክለኛውን ሁኔታ እንደማያሳይ፣ በተጠቀሰው የገንዘብ መጠን ያህል በሂሣብ አሠራር ማዛባት የመንግሥት ገንዘብ ለግል ጥቅም ሊውል እንደሚችል ጠቅሰን ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወስድ አሳሰበናል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚ/ር የሚ/ር መ/በቱ የአስተዳደርና ፋይናንስ መምሪያ በተሰብሳቢ ሂሣበ ከታየው ከውጭ ጉዞ አበል ጋር ተያይዞ ሰነድ ያለባቸው ከደመወዛቸው 1/3 እየተቀነሰ እነደሚገኝ ሌሎቹን በተመለከተ በተሰጠው የማሻሻያ ሃሣብ መሠረት እርምጃ እንደሚወስድ ዘግይቶ በላከው መልስ ገልጿል፡፡ እንዲሁም ለሶሰት የሚ/ር መ/ቤቱ ድርጅቶች ከሠራዊቱ ደመወዝ ተመላሽ ብድር

መሰጠቱ አግባብ እንዳልሆነ ተቀብሎታል፡፡ ሆኖም ተቋማቱ የሚ/ር መ/ቤቱ በመሆናቸው የጥሬ ዕቃ መግዣ ያ ስለ አጠራቸው በሚ/ር መ/ቤቱ የበላይ አመራር አካላት ውሣኔ ብድሩ እንደተሰጠ በላከው መልስ ተገልጿል፡፡ በእኛ በኩል አሠራሩን አልተቀበልነውም፡፡ የውጭ መልዕክተኞች /የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር/ መልስ አልሰጠም፡፡ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሠነድ ያለባቸው እንዲያወራርዱ እና ይህን ካልፈጸሙ በሕግ ለመጠየቅ በዝግጅት ላይ መሆኑ፣ በሂሣብ ክፍል ለማወራረድ የቀረበ በርካታ ሠነዶች መቅረባቸውንና ይህም በአጭር ጊዜ ለመጨረስ በጽ/ቤቱ የፋይናንስ መምሪያ ካለው የሰው ኃይል በላይ መሆኑን በመጥቀስ ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር በቂ ባለሙያ በዘመቻ መልክ እንደሚያሰማራ የሥራ አመራር ሪፖርት በላከው መልስ ገልጿል፡፡

## 2.2. <u>በተሰብሳቢ ሂሣብ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተሰብሳቢ ሂሣብ ሪፖርት ያደረገው በተቀጽላ ሌጀሮች ድምር ከታየው ብር 2,091,202.29 አንሶ መገኘቱንና ይህ ባለፉት ኦዲቶችም የታየ ልዩነት መሆኑን በመግለጽ ሁኔታው እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

- በውጭ መልዕክተኞች የጄኔቭ ኢምባሲ ለሠራተኞች ብድር ከሰጠው የሰበሰበውን የብድር ተመላሽ ብር 86,935.69 በክሬዲት ባለመመዝገቡ ተሰብሳቢ ሂሣቡ በተጠቀሰው የገንዘብ መጠን አላግባብ ከፍ ማለቱን በመጥቀስ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት በላከው መልስ በውጭ ባለሙያ እንዲጣራ ለማድረግ በሂሣብ ላይ እንደሚገኝ በላከው መልስ ገልጿል፡፡ የውጭ መልዕክተኞች ምላሽ አልሰጠም፡፡

# 3. <u>ተከፋይ ሂሣቦች</u>

## 3.1. <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

- በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰኔ 30/2002 ከሠራዊት ደመወዝ ተመላሽ ተብሎ ሪፖርት የተደረገው ብር 117,314,864.62 የሠራዊቱ አባላት ደመወዝ ባለመውሰዳቸው ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ሂሣብ የተያዘና ሂሣቡም በወጪ የተመዘገበ መሆኑን በመጥቀስ አሠራሩ ከመንግሥት የሂሣብ አሠራር

ውጭ በመሆኑ እንደማንኛውም የፌደራል መንግሥት መ/ቤት ያልተከፈለ ደመወዝ በቀጣዩ ወር መጀመሪያ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ እንዳለበት ደመወዝ ካልተከፈላቸው አባላት ጥያቄ ሲቀርብ ከገ/ኢ/ል/ማ/ር እየተጠየቀ እንዲከፈል አሳስበናል፡፡ እንዲሁም ከዚህ ሂሣብ ውስጥ ከላይ በ2.1. እንደተጠቀሰው በሥሩ ለሚገኙት 3 ድርጅቶች ብር 79,278,186.00 ብድር መሰጠቱ አግባብ አለመሆኑን ገልጸናል፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ ሪፖርቱ ከተላከለት በኋላ በሰጠው መልስ የሚ/ር መ/ቤቱ የሠራዊት አባላት በመላ ሀገሪቱ ተበትነው የሚገኙ መሆኑንና ለእነኚህ አባላት በሰኔ ወር የመጨረሻ ሳምንት የሚለቀቀውን ደመወዝ በአሥር ቀናት ውስጥ ከፍሎ ተራፊውን ፈሰስ ለማድረግ እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን፤ ደመወዝ ያልተከፈላቸው የሠራዊት አባላት የደመወዝ ጥያቄ በሚቀርብበት ወቅት እንደሌሎች ባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ከዘመኑ በጀት ላይ ክፍያ መፈጸም ለዘመኑ የተፈቀደው በጀት ላይ ከፍተኛ እጥረት እንዲፈጠር ከማድረጉም በላይ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆኑን ጠቅሶ፣ ከገ/ኢ/ል/ሚ/ር በተፈቀደው መሠረት ፈሰስ የማይሆን የተለየ የባንክ ሂሣብ ተከፍቶለት እንደሚቀመጥ በላከው መልስ ገልጿል፡፡ የተጠቀሰው በሰኔ 30/2002 ብቻ የተገኘ ያልተከፈለ ደመወዝ ሳይሆን ለዓመታት በተከፋይ የተያዘ ሲሆን፣ እንደተባለው እንደሌሎች ባለበጀት መ/ቤቶች በ10 ቀናት ውስጥ ከፍሎ፣ ያልተከፈለውን ፈሰስ ለማድረግ ጊዜ የሚጠይቀ ሊሆን ይችላል፡፡ ግን በሁለት ወር በሶስት ወር ፈሰስ ማድረግ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የሚፈጥረው ችግር የለም፡፡ የዘመኑንም በጀት አይነካም፡፡ ባልተከፈለበት ወራት ሂሣቡ በወጪ ሳይያዘ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ በማድረግ ጥያቄው ሲቀርብ ፈሰስ የተደረገበትን ማስረጃ በማጣቀስ ጠይቆ በማምጣት የዘመኑን የደመወዝ በጀት ሳይነካ ለአባሉ ከፍሎ በወጪ መመዝገብ ስለሚቻል እንደችግር የተጠቀሰውን አልተቀበልነውም፡፡

- የውጭ መልዕክተኞች በሀገር መከላከያ ሚ/ር ስም በተከፋይ የያዘው ብር 1,113,176.21 ሚ/ር መ/ቤቱ ስለዚህ ሂሣብ ምንም የሚያውቀው እንደሌለ በደብዳቤ እንዳረጋገጠልን በመግለጽ፤ በዚህም የሂሣብ ሪፖርቱ የተዛባ ሊሆን

እንደሚችል፣ አላስፈላጊ የሂሣብ ማስተካከያ ተሰርቶ ሊሆን እንደሚችል በመግለጽ ሁኔታው እንዲጣራ አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ መልስ አልሰጠም፡፡

- የውጭ መልዕክተኞች በኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳዮች ዋና መምሪያ ስም በተሰብሳቢ ሂሣብ ብር 1,077,730.06 በተከፋይ ሂሣብ ብር 1,969,190.40 በሂሣብ ሪፖርቱ የገለጸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ዋና መምሪያው በደብዳቤ የተጠየቀ ቢሆንም መልስ ባለመስጠቱ መ/ቤታችንም ብሔራዊ የመረጃና ድህንነት አገልግሎትንና የዋና መምሪያውን የ2002 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ባደረገበት ወቅት በውጭ ጉዳይ ሚ/ርም ሆነ በውጭ መልዕክተኞች ስም የያዘ ተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣቦች አለመኖሩን በመግለጽ የሂሣቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው እንዲፈጸም አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ መልስ አልሰጠም፡፡

በተጨማሪም፡-

| | |
|---|---|
| - በፌደራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዋና መምሪያ | 143,589.92 |
| - በቀድሞ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚ/ር | 774,451.83 |
| - በፌደራል ፖሊስ | 27,488.16 |

የተከፋይ ሂሣብ የተገኘ ሲሆን በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተገኘው ተከፋይ ሂሣብ ከ1997 ጀምሮ የተያዘ መሆኑን በመግለጽ ሂሣቡ ላይ ክትትል ተደርጐ ለባለጥቅሞቹ እንዲከፍል አሳስበናል፡፡

3.2. <u>በተከፋይ ሂሣብ የታየ የአሠራር ችግር</u>

የውጭ መልዕክተኞች በጄኔቭ ኤምባሲ የሎካል ሠራተኞች የደመወዝ ተከፋይ በዴቢት ብር 399,274.92 በክሬዲት ብር 196,156.24 ሳይመዘገብ መገኘቱን በዚህም ምክንያት የሂሣብ ሪፖርቱ የተዛባ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰን ለሂሣቡ የማስተካከያ ምዝገባ እንዲሠራ አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ ምላሽ አልሰጠም፡፡

## 4. የገቢ ሂሣብ

### 4.1. በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ያልተደረገ

- የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ብር 295,574.07
- የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት " 790,531.44
- የፕራይቤታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ " 503,828,732.51

በሂሣብ ሪፖርታቸው ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር አለመቅረባቸው ታውቋል፡፡ ሁለቱ ፍ/ቤቶች በስማቸው አንጻር የተገለጸውን ገንዘብ ድሬደዋ የሚገኙት የፌደራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶች የሰበሰቡት ገቢ አዲስ አበባ በሚገኙት ሁለት ፍ/ቤቶች የወጪ በጀት የሚላከላቸው ሲሆን፣ የወጪ ሂሣብ ሪፖርት እየተደረገ ገቢው ግን ለድሬደዋ ገቢዎች ቢሮ እንደሚገባ መታወቁን በመግለጽ አሠራሩ እንዲስተካከል፤ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሰው ኤጀንሲ የሰበሰበውን ገቢ በገቢ ሂሣብ ሪፖርቱ አለማካተቱ አግባብ ባለመሆኑ በሪፖርቱ እንዲያካትት አሳስበናል፡፡ ፍ/ቤቶቹ በላኩት መልስ ከመ/ቤቶቹ ጋር በመነጋገር እንደሚያስተካክሉ ገልጸዋል፡፡ የፕራይቤታይዜሽንና የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በሰጠው ምላሽ በገ/ኢ/ል/ሚ/ር የታተመው የገቢ ደረሰኝ ተጨማሪ እሴት ታክስን የማያካትት በመሆኑ ደንበኞች ለሂሣብ ማወራረድ የማያስችል መሆኑን በዚህም ምክንያት ደረሰኝ አሳትመው ገቢውን እንዲሰበስቡ ከሚ/ር መ/ቤቱ ጋር በመነጋገር እልባት ላይ መድረሳቸውን የሽያጭ ገቢው በሚ/ር መ/ቤቱ ተፈቅዶ በተከፋይ የባንክ ሂሣብ በማዛወር የሚዘጋ መሆኑ ተገልጿል፡፡

### 4.2. የገቢውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ

- ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 11,124.71
- የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ " 257,570.06

ከማን እንደሚሰበሰብ ሳይገለጽ በኮድ በመሰብሰቡ የተሰበሰበው ገቢ መሰብሰብ በሚገባው ልክ መሆኑን ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ፣ አሠራሩ ተስተካክሎ ማስረጃ በማቅረብ ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ አሳስበናል፡፡ መ/ቤቶቹ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት መልስ አልሰጡም፡፡

4.3. <u>ፈሰስ ያልተደረገ የውስጥ ገቢ</u>

- የብረታ ብረት ኢንድስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከውስጥ ገቢ የሰበሰበው ብር 348,871.71 በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከወጪ ቀሪ ሆኖ የተገኘ ሲሆን፣ ይህ ገቢ ከውስጥ ገቢው እንዲጠቀም ከተፈቀደለት ጣሪያ በላይ ከወጪ ቀሪ የሆነ በመሆኑ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ መደረግ ሲገባው አለመደረጉን በመግለጽ ፈሰስ እንዲሆን አሳስበናል፡፡ ኢንስቲትዩቱ በላከው መልስ ደንበኞች በቅድሚያ እንዲመረትላቸው የከፈሉት በትዕዛዙ መሠረት ሊመረቱ ላልቻሉት ከተጠቀሰው ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን በመታሰቡ ፈሰስ አለመሆኑ ተገልጿል፡፡
- ሆቴሎችና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከማታው ትምህርት ሥልጠና የሰበሰበውን ገቢ ወጪ የሚያደርግ ሲሆን፣ ከውስጥ ገቢው ወጪ ያደረገው በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድለት መሆኑን በመጥቀስና በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 መሠረት ከገቢው ለመጠቀም ፈቃድ ማግኘት እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.4. <u>በተገቢው የገቢ አርዕስት ያልተመዘገበ</u>

- የቀድሞ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በበጀት ዓመቱ ከአገለገሉ ዕቃዎችና ልዩ ልዩ ገቢዎች የሰበሰበውን ብር 121,469.98 በሂሣብ መደብ 1459 መሰብሰብና ሪፖርት ማድረግ ሲገባው በ5054 በተከፋይ ሂሣብ መዝግቦ መገኘቱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ አሠራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

5. <u>የወጪ ሂሣብ</u>

5.1. <u>ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ</u>

| | |
|---|---|
| - የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት | 4,775,950.00 |
| - የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በ6251 የሂሣብ መደብ በውል ለሚፈጸም አገልግሎት | 6,970,000.00 |
| - የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ዋና መ/ቤት የአለም አቀፍ አባልነት | 2,748,700.00 |
| - የውጭ መልዕክተኞች ለሂውተንና ለሰያት | 76,400.00 |
| - የፌደራል ልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት | 27,823.43 |

የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ተቋም ከኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ጋር በገባው ውል መሠረት ለዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የሰጠው ከላይ ተጠቅሰው ገንዘብ ሥራ ላይ መዋሉን የሚገልጽ የወጪ ማስረጃ ሣይቀርብ በወጪ መዝገቦ መገኘቱ፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር መረጃ አገልግሎት ወጪ የተደረገ መሆኑን የውጭ መልዕክተኞች ለተጠቀሱት ሚሲዮኖች ያለበቂ ማስረጃ በወጪ ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑን በመጥቀስ ለሂሣብ ማስረጃ እንዲቀርብ አሳስበናል፡፡ የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት በቀጥታ በወጪ መዝገቡ አለመሆኑንና ለወደፊቱ እንደሚያስተካክል የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ኦዲቱ እየተካሄደ የፋይናንስ ሥራ አመራር ዘርፉ ኃላፊ ለወታደራዊ መረጃ አገልግሎት ወጪ መደረጉንና ለማን እንደተከፈለ ከሚስጥራዊነት አኳያ ማስረጃ ሊቀርብለት እንደሚችል ፡፡ የውጭ መልዕክተኞች ለተላከለት የሥራ አመራር ሪፖርት መልስ አልሰጠም፡፡

5.2. <u>አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተል የተፈጸመ</u>

| ተ.ቁ | የመ/ቤቱ ስም | የገንዘቡ ልክ |
|---|---|---|
| 1 | ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | 2,828,244.34 |
| 2 | የፌደራል ፖሊስ | 398,000.00 |
| 3 | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት | 316,088.00 |
| 4 | የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የውጭ መልዕከተኞች | 458,400.00 |
| 5 | የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም | 69,723.87 |
| 6 | የፕራይቬታይዜሽንና የመ/ል/ጽ/ተ/ኤጀንሲ | 295,483.24 |
| 7 | የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት ከኢትዮ.ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ጋር ከገባው ውል /ስምምነት/ ውጭ የተከፈለ | 1,275,750.00 |
| | ድምር | 5642689.45 |

የፌደራል መንግሥት የግዥ ሕግ፣ደንብ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲን መመሪያ መ/ቤቶች ከገቡት ውል ውጭ ክፍያ መፈጸማቸው አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ አሠራሩ እንዲስተካከል አሳስበናል፡፡

- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለወደፊት ለሚካሄድ ምርጫ በቅድሚያ በጀት በመጠየቅና በማስፈቀድ የታየውን ችግር እንዲወገድ እንደሚያደርግ፣ የፌደራል ፖሊስ ለመኪና ጥገና ያለ ጨረታ ማወዳደሪያ ለተፈጸመ የአገልግሎት ግዥ በተመለከተ የፌ/ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዘርፍ የአድማ መቆጣጠሪያ ውሃ የሚረጩ መኪናዎች ሲሆኑ፣ ተሽከርካሪዎቹ አስመጪ ካምፖኒ የሌላቸው ከመሆኑም በላይ የተለየ ባህሪ ያላቸው በመሆኑ ተሽከርካሪዎቹን ለመጠገን የሚችል ተወዳዳሪ ማግኘት ባለመቻሉና የውሃ መርጫ መኪናዎቹን ሊጠግን የሚችል ብቸኛው ጋራዥ መሆኑንና ለወደፊትም ተመሳሳይ

5.3. <u>የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ</u>

በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መ/ቤቶች የፈጸሙት ክፍያ ትክክለኛነት ኦዲት ሲደረግ፡-

| | |
|---|---|
| - የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ለሠራዊቱ ደመወዝ፣አበልና ማበረታቻ ወጪ ያደረገው | ብር1,708,115,690.49 |
| - በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር በሰሜን እና ማዕከላዊ ዕዝ ጠቅላይ መምሪያዎች ወጪ የተደረገውን የሥራ ማስኬጃ ለማጣራት የፈራሚዎች ስምና የፊርማ ናሙና ባለመቅረቡ | ” 165,686,455.58 |
| - የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ | ” 24,167,053.26 |
| - የብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት | ” 2,150,783.17 |
| - የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ | ” 38,575,487.91 |
| - የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል | ” 208,405.21 |
| - የፌደራል ልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት | ” 24,202.00 |
| - የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት | ” 43,581.39 |

ተገኝቷል፡፡ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ለደመወዝ፣ አበልና ማበረታቻ ወጪ የተደረገው ከጠቅላላ ወጪው 43% ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ አዲስ የተቀጠሩ በተለያየ

ምክንያት ከመ/ቤቱ የለቀቁ በጡረታ የተሰናበቱ የሠራዊቱ አባላት የስም ዝርዝር ተጠይቆና ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ማሕደሮች ተጠይቆ ባለመቅረቡ፤ የሶስቱ የደህንነት መ/ቤቶች ለደመወዝ ለነዳጅና ለስልክ ወዘተ... ወጪ ያደረጉት ሂሣብ ለማረጋገጥ በኮድ የተከፈለውን ደመወዝ የሠራተኞቹ ኮድ የመኪኖች ታርጋ የስልክ ዝርዝሮች እንዲቀርቡ ተጠይቆ ባለመቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ መ/ቤቶቹ ለተላከላቸው የሥራ አመራር ሪፖርት መልስ አልሰጡም ሆኖም በመውጫ ስብሰባ ወቅት የደህንነት መ/ቤቶቹ ከመ/ቤታቸው የሥራ ፀባይ አኳያ መረጃዎቹን ለመስጠት እንደማይችሉ ገልጸዋል፡፡

የሀገር መከላከያ ሚ/ር ዘግይቶ በላከው መልስ ከወታደራዊ ሚስጥራዊነት አንጻር የተሰጪ የሰራዊት አባላትና አዲስ የተቀጠሩት ሠራዊት አባላትን ከደህንነት አንጻር ችግር ያለበት መሆኑን፣ ለወደፊቱም ቢሆን እንደዚህ አይነት ወታደራዊ ሚስጥር አሳልፎ መስጠት አስቸጋሪ መሆኑ ተገልጿል፡፡

5.4 <u>በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ወጪ</u>

| | | |
|---|---|---|
| የፌፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ | ብር | 162,000.00 |
| የፍትህና የሕግ ሥርአት ምርምር ኢንስቲትዩት | ” | 46,289.74 |
| | ድምር | 208,289.74 |

በባለሥልጣን ሳይጸድቅ ወጪ የተደረገ ሲሆን የወንጀል ምርመራ ዘርፍ በአፋር ክልላዊ መንግስት ፖሊስ ኮሚሽን ለምርኮኞች ማቋቋሚያ በባንክ በኩል ልኮ የቀረበው የደመወዝ መክፈያ /ሞ/33/ ለሚመለከተው `ላፊ ያልጸደቀ መሆኑን፤ በፍትሕና የሕግ ሥርአት ምርምር ኢንስቲትዩት ለሆቴል አገልግሎት ወጪ ሲደረግ ከተጠየቀው ቆይታ ጊዜ በላይ በሆቴሉ ተገልግለናል በሚል በ`ላፊ የተፈቀደበት ማስረጃ ሳይኖር ወጪ መደረጉ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ አሠራሩ እንዲታረም አሳስበናል፡፡

5.6 <u>አለአግባብና በግል የተከፈለ ሂሳብ</u>

- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለሚያሰራው ሕንጻ ሂሳቡን ሁለት ጊዜ በመያዝ ወጪ የተደረገ ብር 491,860.00
- የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ክፍያ material on site አለኝ ብሎ ተቋራጩ ባስረከበው መሠረት ተከፍሎት በኮንስትራክሽን ሕግ መሠረት ይህ ሂሳብ በቀጣዩ የክፍያ ጥያቄ መቀነስ ሲገባው ሳይቀነስ በሁለተኛው የክፍያጥያቄ አላግባብ የተከፈለ " 499,667.75
- የፌዴራል ፖሊስ በሂሳብ ስሌትና በስምምነቱ ከተቀመጠው ዋጋ በማስበለጥ የተከፈለ " <u>55,055.77</u>

ድምር <u>1,046,583.52</u>

ሁለቱ መ/ቤቶች ለሚያሠሩት የግንባታ ሥራ አለአግባብ በብልጫ በስሌት ስህተትና ደንብን በመተላለፍ የከፈሉትን ሂሳብ ተመላሽ እንዲያደርጉ ለወደፊቱም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ምላሽ በአማካሪ ድርጅቱ በኩል ተጣርቶ ከቀጣይ ክፍያ እንደሚያስመልስ፣ የፌዴራል ፖሊስ የተወሰነውን ቀንሶ ገቢ ማድረጉን ቀሪውን በቀጣይ ክፍያ እንደሚቀንስ በላኩት መልስ ገልጸዋል፡፡

5.7 <u>ለኦዲት ተጠይቆ ያልቀረቡ የወጪ ማስረጃዎች</u>

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ2002 በጀት ዓመት በወጪ መዝገቦ በሪፖርት የገለጸውን ብር 1,174,580.85 የወጪ ማስረጃ እና ቫቸሮች ለኦዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ ባለማቅረቡ ማስረጃ ሳይኖረው የተመዘገበው ወጪ ለግል ጥቅም ሊውል ስለሚችል በአስቸኳይ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡ የባርዱ ጽ/ቤት በሰጠው ምላሽ ወጪው በDIP የሚሸፈን ሆኖ ከበጀት ሂሳብ በብድር መስጠቱን ማስረጃው DIP እንደሚገኝ ተገልጿል፡፡ ሆኖም የሂሳብ አሠራሩ በሚፈቅደው መሠረት የሚተካ መሆኑ ከታወቀ በተሰብሳቢ ሂሣብ መያዝ ሲገባ ከሌላ አካል ይተካል የተባለን ሂሳብ በወጪ መመዝገቡ አግባብ አለመሆኑን ሁለቱም ቦታ ተመዝግቦ ሊሆን እንደሚችል በመግለጽ እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

5.8 <u>በሂሳብ መዝገብ ያልተመዘገበ እና የሂሳብ መደቡን ሳይጠየቅ የተገዘገበ ወጪ</u>

| | | |
|---|---|---|
| - በውጭ መልዕክተኞች በጄኔቭ ኤምባሲ በወጪ ያልተመዘገበ | ብር | 2,656.29 |
| - በፍትሕና የሕግ ሥርአት ምርምር ኢንስቲትዩት በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ | | 350,424.63 |
| ድምር | | 353,080.92 |

ያልተመዘገበው እንዲመዘገብ በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበው እንዲስተካከል በላከነው ሪፓርት አሳስበናል፡፡

5.9 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረቡባቸው ወጪዎች</u>

| | | |
|---|---|---|
| - ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ | ብር | 279,101.07 |
| - የሀገር መከላከያ ሚኒሰቴር | ብር | 79,058.42 |
| ድምር | | 358,159.49 |

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ECG machine ለመግዛት ከላይ የተጠቀሰው ገንዘብ የተከፈለና ሂሳቡ በወጪ የተመዘገበ ቢሆንም ዕቃው ለመገዛቱ ሞ/19 አልቀረበለትም እንዲሁም የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በ1984 የትምህርት መሣሪያዎች የህትመት ወረቀት ገዝቶኝ አልተከፈለኝም ብሎ ለጠየቀው ቦርዱ ይህ ሂሳብ እንዳለበት በዕዳ የሚያሣይ ምዝገባ የለውም የተጠቀሱት ዕቃዎችም በወቅቱ ገቢ ለመሆኑ የሚያረጋገጥ ሞ/19 ባለማቅረቡ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አለመቻሉን በመግለጽ ሁኔታው ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በወቅቱ ከድርጅቱ ጋር ወረቀት እንደገዛ በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ እንዳላደረገ፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ንብረቱ ገቢ አለመሆኑን ጠቅሶ በዕቃው ላይ ክሌም (Claim) ስለነበራቸው ከድርጅቱ ጋር ተጻጽፌው ገቢ ለማድረግ ክትትል እየተደረገ መሆኑን በላኩት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

5.10 <u>የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር</u>

ግዳታውን ባለመወጣት የተጣለ ቅጣት፣ ያልተሰበሰበ ወይም ያልተላከ የጉዳት ካሣ ያለበቂ ምክንያት ውል እንዲቋረጥ ሲደረግ የጉዳት ካሣ ባለመጠየቁና በመሳሰሉት የታዩት ግኝቶች ቀርበዋል፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. | መ/ቤቱ Omnipol a.s ከተባለ ድርጅት ጋር የጦር መሣሪያ ገዝቶ ግዴታውን ባለመወጣቱ የተከፈለ | ብር 5,830,717.50 |
| 2. | መ/ቤቱ ከቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ጋር ለሠራዊቱ የመኖሪያ ግንባታ አካሄዱ በወቅቱ ባለመጨረሱ የሠራዊቱን ቤተሰቦች ትምህርት ቤት ለማጓጓዝ የኮንስትራክሽን ውል በማስመሰል ለቃሊቲ ኮንስትራክሽን የተከፈለ | ” 234,098.25 |
| 3. | መ/ቤቱ ከቃሊቲ ኮየኮ/ዕቃዎች ማምረቻ ድርጅት ጋር በደብረ ዘይት የጋራ መኖሪያ ለማስገንባት ውል ገብቶ ተቋሙ ማስረከብ ከሚገባው ጊዜ በላይ 272 በመቆየቱ ሊከፈል የሚገባው የጉዳት ካሣ አለመሰበሰቡ | ብር10,204,859.78 |
| 4. | ከላይ በተራ ቁጥር 3 ለተጠቀሰው ግንባታ ለብር 3,414,853.23 ከድርጅቱ ጋር መ/ቤቱ ውል ገብቶ ብር 8,310,741.15 ወጪ በመደረጉ ያለተጨማሪ ውል ከኮንስትራክሽን ደንብ ውጭ የተከፈለ ( 143.66% ) | ” 4,905,887.92 |
| 5. | መ/ቤቱ ከመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንጂነሪንግ ድርጅት ጋር ከአዋሽ አርባ ከተማ እስከ ማሰልጠኛ ካምፕ ያለውን መንገድ በብር 13,207,074.70 አስፋልት ለማድረግ ውል ገብቶ የመጀመሪያ ርክክብ ከተደረገ በኋላ የዲዛይን ችግር አለ በሚል ውል በብር | ” 5,720,284.07 |

6,743,113.95 በመግባቱ ያስከተለው ወጪ

ለዚሁ ተጨማሪ ውል አማካሪ መሀንዲሱ ለብር 4,792,775.06 የመ/ቤቱን ስምምነት ጠይቆ የፈቀደ ቢሆንም ስምምነቱ አማካሪ መሀንዲሱ ከጠየቀው ውጭ በብር 6,743,113.95 በመፈረሙ ከድርጅቱ ጋር ብልጫ ( 40%) የተደረገ ውል " 1,950,338.89

6. መ/ቤቱ ኖሪኮን ላሊበላ ከተባለ ድርጅት ጋር በደብረ ዘይት አየር `ይል ግቢ ባንከርና ታክሲ ዌይ ለማሰገንባት በብር 171,133,008 ውል ገብቶ ብር 155,077,658.19 (90.44) ወጪ ካደረገ በኋላ ውሉ እንዲቁረጥ ሲደረግ የጉዳት ካሣ አልተጠየቀም፣ ለምን እንዳልተቆረጠ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ይህም መ/ቤቱን የሚጐዳ መሆኑን፣

- ድርጅቱ በውሉ መሠረት ባለማስረከቡ ላሳለፉበት ቀናት የጉዳት ካሣ መጠየቅ ሲገባ ይህ ሳይፈጸም ተገኝቷል፡፡

መ/ቤቱ በገባው የግዥ ውል መሠረት ግዴታውን ባለመወጣቱ መንግሥት ላይ ተጨማሪ ወጪ በማስከተሉ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግ፤ ከቃሊቲ ኮንስትራክሽንና የኮንስትራክሽን ማምረቻ ድርጅት ጋር ለገባው የግንባታ ሥራ ተቋራጩ የጊዜ ገደቡን በማሳለፉ የጉዳት ካሣውን እንዲሰበስብ ግዴታውን ባለመወጣቱ የሠራዊቱ አባላት ትምህርት ቤት ለማመላለስ መ/ቤቱ የትራንስፖርት ወጪ ያደረገውን በኮንሰትራክሽን ወጪ ማድረጉንና ግዴታውን ባለመወጣቱ ለተጨማሪ ወጪ ከዳረገው ድርጅት እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት አቅም ከሌለው ድርጅት ጋር ውል መግባቱ አግባብ አለሆኑን፣ መ/ቤቱ ይህን አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር ቀጥታ ውል ሊገባ እንደሚገባ ከኮንስትራክሽን ደንብ ውጭ ያለተጨማሪ ተቀጽላ ውል እና አማካሪ መሀንዲሱ ከጠየቀው የለውጥና ተጨማሪ ሥራ ውል ማድረጉ አግባብ እንዳልሆነ አሳስበናል፡፡ እንዲሁም ኖሪንኮ ላሊበላ ለገባው የግንባታ ሥራ ውል 90.44% ከተከፈለው በኋላ ውሉ ሲቁረጥ ቀሪው ሥራ ምን ያህል እንደሆነ በመ/ቤቱ ላይ ያስከተለው ጉዳት ለዚህም ካሣ እንዲከፍል እንዲሁም በቀኑ ባለማስረከቡ የጉዳት ካሣ ሊጠየቅ ሲገባ ይህ አለመደረጉ የመንግሥትን ጥቅም የሚጐዳ መሆኑን በመጥቀስ አሰራሩ

እንዲስተካከል አስፈላጊውም እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡ ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ቅጣቱ መከፈሉ የመ/ቤቱ ስህተት መሆኑን ይህም ኤል ሲ በወቅቱ ባለመከፈቱ እንደሆነ፣ ለወደፊቱ እንዲህ አይነት ስህተት እንዳይደገም አስፈላጊውን ክትትልና ጥንቃቄ እንደሚያቀርብ፣ ለኖሪንኮ ላሊበላ በበላይ ኃላፊ ውሣኔ እንዲቋረጥ መደረጉና ድርጅቱ የተቋቋመው 49% በመከላከያ ድርሻ በመሆኑ ያለጉዳት ካሣ እንዲቋረጥ መደረጉን በላከው መልስ ገልጿል፡፡ ሆኖም 51% ድርሻ ያላቸውን የቻይና ኩባንያ ተጠቃሚ እንደሚያደርግና መንግሥትን የሚጐዳ መሆኑን በላክነው ሪፖርት በመግለጽ አባባሉን አልተቀበልነውም፡፡

6. <u>የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ንብረት አስተዳደር</u>

የንብረት አስተደደር መንግሥት ባወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡

6.1 <u>ለቋሚ የዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልሰጡ መ/ቤቶች</u>

- ለፍትሕ ሚኒስቴር
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
- የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት
- የፌዴራል ፖሊስ የወንጀል ምርመራ ዘርፍ
- የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ

ሲሆኑ ንብረቶችን ለመቆጣጠር እንዲያስችል በመንግሥት የንብረት አስተዳደር መምሪያ መሠረት ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር እንዲሰጥ አሳስበናል፡፡

6.2. <u>ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ያላደረጉ</u>

- የኢትዮጵያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ
- የፌደራል ልዩ ዐቃቢ ሕግ ጸ/ቤት
- የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት
- የውስጥ ደህንነት ጥበቃ ዋና መምሪያ
- የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት

- የፌደራል ፖሊስ
- የፌደራል ፖሊስ ወንጀል ምርመራ ዘርፍ

6.3. <u>የቋሚም ሆነ የአላቂ ዕቃ ምዝገባ ያልተከናወኑ</u>

- የፌደራል ልዩ ዐቃቢ ሕግ ጽ/ቤት
- የፌደራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ዋና መምሪያ

6.4. <u>ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች</u>

<u>የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም</u>

- በዕቃ መጋዘን ውስጥ ከተቀመጡ አንድ ዓመት የሆናቸው ከዩ.ኤን.ዲ.ፒ በእርዳታ ተገኝተው ርክክብ ያልተፈጸመባቸውና የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው በርካታ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፣ መደርደሪያዎች፣ ሳፋዎችና የመሳሰሉት ንብረቶች መኖራቸው፣
- የቋሚና የአላቂ ንብረቶች ገቢና ወጪ በሞዴል 70/ሐ ካርዱን ኮፒ በማድረግ ብቻ የሚመዘግብ መሆኑና አልፎ አልፎ ወዲያው ገብተው ወዲያው ለሚወጡ መሆኑ፣
- አሮጌ የተሽከርካሪ መለዋወጫዎች የመመዝገቢያ ቅጽ ተዘጋጅቶላቸው በንብረት ገቢ ደረሰኝ ንብረት ክፍሉ ተረክቦ በማስቀመጥ በሽያጭ እንዲወገዱ፣

<u>የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት</u>

- በጽ/ቤቱ ለአገልግሎት ተገዝተው ገቢ የተደረገ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በንብረት መዝገብ /መ/70 ሀ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- በግ/ቤት የዕቃ መደርደሪያ ባለመዘጋጀቱ ተደራርበው እና ለአያያዝ በማያመች ሁኔታ መቀመጣቸው፣
- የአላቂ ዕቃ ቆጠራ ቢደረግም ምዝገባው ባለመካሄዱ ቆጠራው በስቶክ ካርድ ከሚታየው ከወጪ ቀሪ ጋር እየተመሳከረ ትክክለኛነቱ የማይረጋገጥ መሆኑ

**<u>የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዋና መ/ቤት</u>**

- ብዛት ያላቸው አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች እንዲወገዱ እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

**<u>የፌደራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር</u>**

- በዋናው መ/ቤት በሚገኘው የወዳደቁ መጋዘን ክፍል ውስጥ ያሉ ዕቃዎች የዕቃ መደርደሪያ የሌላቸውና ዓይነት በዓይነት ሳይለዩ በመሬት ላይ የተቀመጡ መሆኑ ታውቋል፡፡

**<u>የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት</u>**

- በፍ/ቤቱ አንድ ንብረት ክፍል ውስጥ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ ተገኝተዋል፡፡

**ቆጠራ ያላደረጉ መ/ቤቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት እንዲያካሂዱ፣ መዝገብ ያላቋቋሙት እንዲያቋቁሙ፣ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው እንዲቆረጥላቸው እንዲሁም በመንግሥት የንብረት አስተዳደር መሠረት ንብረቶቹን እንዲያስተዳድሩ አሳስበናል፡፡**

## 6.5. <u>የንብረት ጉድለትና የንብረት አስተዳደር ችግሮች</u>

**<u>የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ</u>**

- በውስጥ ኦዲት ግኝቶች ላይ ጽ/ቤቱ እርምጃ መውሰዱ ሲጣራ የጽ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት መምሪያ በሰኔ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በጽ/ቤቱ ድልድልና ክምችት ክፍል በተደረጉት ኦዲት በክምችት ክፍል ብር 881,846.17 በድልድል ክፍል ብር 692,288.71 በድምሩ ብር 1,574,134.88 የሚገመቱ ቁሳቁሶች /ንብረት/ በጉድለት የተገኘ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በዚሁ መሠረት ጽ/ቤቱ ምን የወሰደው እርምጃ እንዳለ ተጠይቆ ጉዳዩን የሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን መያዙን ከመግለጽ ውጭ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀ ሕዳር ወር 2003 የወሰደው እርምት አለመኖሩ ታውቋል፡፡ ጽ/ቤቱ የሚያስተዳድረውን ንብረት በመንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት ማስተዳደርና መጠበቅ ሲገባው ይህን ያህል ከፍተኛ ንብረት መጉደሉ ከቁጥጥር ማነስ መሆኑን በመግለጽ በውስጥ ኦዲት ሪፖርቱ

መሠረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡ ጽ/ቤቱም በላከው መልስ ወደፊት መሰል ችግሮች እንዳይከሰቱ የተጠናከረ የቁጥጥር ሥርዓት እንደሚዘረጋ ከላይ በጉድለት የታየውን በተመለከተ ለግል ጥቅም የዋለ ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ በሥነ ምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን እንደሚረጋገጥ ገልጿል፡፡

- ቦርዱ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የንብረት ቆጠራ ቢያደርግም ቆጠራውን ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያላመዛዘነ በመሆኑ የቆጠራውን አላማ ያልተከተለ መሆኑን በመግለጽ ቆጠሪው ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመሳክሮ የተገኘውን ውጤት ለውሣኔ ለሚመለከተው ኃላፊ መቅረብ እንዳለበት አሳስበናል፡፡ ጽ/ቤቱም በተሰጠው አስተያየት መሠረት እንደሚሠራ በላከው መልስ ገልጿል፡፡

6.6. <u>የተሽከርካሪ መኪናዎች</u>

**በፌደራል ፖሊስ**

- ካሉት ተሽከርካሪዎች 236 ተሽከርካሪ መኪኖችና ሞተር ሳይክሎች የባለቤትነት መቃወቂያ ደብተር /ሊብሬ/ የሌላቸው መገኘታቸውን፣
- 53 ተሽከርካሪዎች ደግሞ በጊዜያዊ ሊብሬ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፣
- ከላይ ከተጠቀሱት ተሽከርካሪዎች 70ዎቹ ከ6 ወር እስከ 10 ዓመት ከአገልግሎት ውጭ ቆመው መገኘታቸውን፣

**በፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት**

- በሁለት ተሽከርካሪ መኪኖች ሊብሬ ላይ የተመዘገበው የሻንሲና የሞተር ቁጥሮች የአንደኛው ከሌላኛው ተቀያይሮ ተመዝግቦ መገኘቱን፣

6.7. <u>የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም</u>

**የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም**

- ለነዳጅና ቅባቶች ግዥ ቅጽ ያልተዘጋጀና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

- የተቋሙ ንብረት የሆኑ ሁለት ሞተር ብስክሌቶች በ16/12/2000 ዓ.ም በቁጥር 082179 የንብረት ገቢ ደረሰኝ የተቀረጠላቸው ሲሆን ሞተር ብስክሌቶቹ የጠፉ መሆናቸው፣

ታውቋል፡፡

ስለዚህ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች መመዝገቢያ እስቶክ ካርድ እንዲያቋቁም፣ በደንቡ መሠረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ኮሚቴ በማዋቀር ዓመታዊ የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ በማድረግ የእያንዳንዱ ዕቃ ቆጠራ ከስቶክ ካርድ ከወጪ ቀሪ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ፣ ለነዳጅና ቅባቶች ግዥ ቅጽ ጠንካራ የቁጥጥር ስርዓት እንዲዘረጋ እና የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ጉድለቶች እንዲስተካከሉ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

## 6.8. <u>የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓትን በተመለከተ</u>

### 6.8.1. <u>የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች</u>

**የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም**

- ሰዓት መቆጣጠሪያ ሰነድ ላይ በሰዓቱ ባለመግባት ወይም በመቅረት በየጊዜው ምልክት የተደረገባቸው ሠራተኞች ቢኖሩም በዚህ ጉዳይ ላይ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፣

- ከመደበኛ በጀት ወጪ ተደርጐ ሂሣቡ በወጪ ከተመዘገበ በኋላ እንደገና ማስተካከያ ተሰርቶላቸው በዩ ኤን ዲፒ እንዲሸፈኑ በሚል ማስተካከያ የተሠራላቸው ወጪዎች አልፎ አልፎ መገኘቱ፣

- ግዥዎች ጨረታ በማውጣት የሚፈጸሙ ቢሆንም ዕቅድን መሠረት ባላደረገ መልኩ በተበታተነ ሁኔታ በፕሮፎርማ የሚፈጸሙ ግዥዎችም በኦዲቱ ወቅት በብዛት መገኘቱ፣

**የፌደራል ልዩ ዐቃቤ ሕግ ጽ/ቤት**

- የጽ/ቤቱ ሠራተኞች የረዥም ጊዜ ብድር የተሰብሳቢ ሂሣብ መቆጣጠሪያ ሌጀርና በሰኔ 30/2002 ዓ.ም ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የተደረገው ብር 65,513.88 ሲሆን፣ የተቀጽላ ሌጀሮች ድምር ደግሞ ብር 11,954.82 ያሳያሉ፡፡ በዚህም

ምክንያት በልዩነት ብር 53,559.06 ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የረዥም ጊዜ የደመወዝ ብድር ተከፋይ መቆጣጠሪያ ሪፖርት ደግሞ ብር 69,723.14 የሚያሳይ በመሆኑ ልዩት ብር 4,209.26 ተገኝቷል፡፡

- የቋሚም ሆነ የአላቂ ዕቃ ንብረት ከግምጃ ቤት ሲወጣ በኃላፊ የማይጸድቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

- የደመወዝ ወጪ የምዝባ ማዘዣ (Journal Voucher) ሲዘጋጅ ትክክለኛነቱን በሚያረጋግጠው ኃላፊ የማይጸድቅ መሆኑ ታውቋል፡፡

ከላይ የአፈጻጸምና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች እና ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.8.2. የውጭ መልዕክተኞች የተሰብሳቢ ሂሣብ መከታተያ ዝርዝር የተሰብሳቢ ሂሣቡን ዝርዝር መግለጫ የማያመለክት መሆኑ የመቼ በጀት ዓመት ሂሣብ እና ከማን እንደሚፈለግ ለማወቅ የማያስችል መሆኑ፣

- የተከፋይ ሂሣብ መከታተያ ዝርዝር የተከፋይ ሂሣቡን ዝርዝር መግለጫ የማያመለክት መሆኑ የመቼ በጀት ዓመት ሂሣብ እና ለማን እንደሚከፈል ለማወቅ የማያስችል መሆኑ፣

- በተሰብሳቢና ተከፋይ ሂሣብ መከታተያ ዝርዝር ውስጥ በርካታ ሂሣብ በኔጋቲቭ (Abnormal balance) ተመዝግቦ የተገኘ መሆኑ፣

- የቅድመ ክፍያ ሂሣቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚያስችል የመከታተያ ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣

- በከፊል ማስረጃ የቀረበላቸው እና ያልተወራረዱ ሂሣቦች በተሰብሳቢ ሂሣብ ውስጥ መገኘታቸው፣

- በኤምባሲዎች የሚገኙ የሂሣብ ሠራተኞች ቁጥር አነስተኛ መሆን፣ የሂሣብ ሥራ ሙያ የሌላቸው ወይም ሥልጠና ያልወሰዱ የሚገኙ

መሆኑ እንዲሁም የኢምባሲዎች ሂሣብ ምዝገባ በዋናው መ/ቤት አዲስ አበባ መከናወኑ በሂሣብ ሥራው ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣

በመግለጽ በተመለከቱት የአሰራር ሥርዓት ድክመቶች ምክንያት የዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖች ሂሣብ በአግባቡ ላይያዝና የመንግሥት ገንዘብ ለብክነት ሊጋለጥ ስለሚችል የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ሊጠናከር እንደሚገባ አሳሰበናል፡፡ መ/ቤቱ መልስ አልሰጠም፡፡

## 7. የበጀት አጠቃቀም

ኦዲት ለተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደው የመደበኛና የካፒታል በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲገናዘብ ሥራ ላይ ያልዋለውና ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 7.1. ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ የሆነ

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤት ሥም | ከበጀት በላይ ወጪ የሆን | |
|---|---|---|---|
| | | መደበኛ | ካፒታል |
| 1 | ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | 961,592.78 | - |
| 2 | የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች ማሰልጠኛ ማዕከል | 824,001.71 | - |
| | ድምር | 1,785,594.49 | |

7.2. <u>ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት</u>

| ተራ ቁጥር | የመ/ቤት ሥራ | ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት | |
|---|---|---|---|
| | | መደበኛ | ካፒታል |
| 1 | የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት | 1,358,510.74 | |
| 2 | የኢትዮጲያ ፖሊስ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ | 1,707,608.30 | |
| 3 | የፌደራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል | 8,606,894.30 | |
| 4 | ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት | 1,306,291.47 | |
| 5 | የሠነዶች ምዘገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት | 1,977,827.73 | |
| 6 | የኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳዮች ዋና መምሪያ | 1,337,844.00 | 2,750,521.48 |
| 7 | የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት | 3,601,270.89 | |
| 8 | ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር | 2,644,669.13 | 40,697,416.00 |
| 9 | የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት | 1,347,869.85 | 20,475,572.08 |
| 10 | ፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር | 1,577,023.88 | |
| 11 | ፍትሕ ሚኒስቴር | - | 2,714,459.39 |
| 12 | የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት | 1,626,716.47 | |
| 13 | የፍትሕ አካላት ባለሙያዎች ማስ.ማዕከል | 2,575,718.14 | 824,001.71 |
| 14 | የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ቴክኖሎጅ | 18,530,289.07 | |
| | ድምር | 48,198,533.97 | 67,461,970.66 |

የበጀት ዝግጅቱ በጥናት ላይ የተመሠረተ መሆን እንዳለበትና ከተፈቀደው በጀት በላይ መጠቀም በሕግ የሚያስቀጣ መሆኑን በመግለጽ የበጀት እጥረት ሲኖር በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የበጀት ዝውውር በመጠየቅ ማስፈቀድ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡ መ/ቤቶቹ በላኩት መልስ በክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኛ ለመቅጠር ተሞክሮ መሥፈርቱን የሚያሟሉ ሠራተኞች ባለመኖራቸው ሠራተኞች በመልቀቃቸው፣ የካፒታል በጀትን በተመለከተ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ከዓለም ባንክ ለንግድ አቅም ግንባታ በተገኘው የብድርና

ዕርዳታ ድጋፍ መሠረት ከመንግሥት ለMatching Fund የተያዘና ኘሮጀክቱ ጥያቄ ሲያቀርብ የሚከፈል በመሆኑ፣ የፍትሕና የሕግ ሥርዓት ምርምር ከአንድ የአሜሪካ ዩኒቨርስቲ ጋር ባለው ውል ለሠልጣኞችን የ2ኛ ድግሪ ትምህርት እየሰጠ መሆኑንና በዚህ በጀት ዓመት ዩኒቨርስቲው የክፍያ ጥያቄ ባለማቅረቡ ሥራ ላይ አለመዋሉን ገልጸዋል፡፡

8. <u>ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ</u>

8.1. የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዲኘሎማቲክ ሚሲዮን የ2000 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ተደርጐ፣

<u>የተሰብሳቢ ሂሣብ</u>

በ2000 በጀት ዓመት የውጭ መልዕክተኞች የተሰብሳቢ ሂሣብ

| | | | |
|---|---|---|---|
| - ኮፒ ደጋፊ ማስረጃ የቀረበለት | | ብር | 5,845,294.98 |
| - ደጋፊ ማስረጃ የሌለው | | ” | 9,445,831.56 |
| | በድምሩ | ” | 15,291,226.54 |

መገኘቱን በመግለጽ፣ ኮፒ ማስረጃ ለቀረበለት ዋናው፣ ምንም ማስረጃ ሳይኖረው ለተመዘገበው ማስረጃ እንዲቀርብለት እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በ2002 በጀት ዓመት ኦዲትም ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑን በመግለጽ ለሂሣቦቹ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡ መ/ቤቱ ለሥራ አመራር ሪፖርቱ መልስ አልሰጠም፡፡

<u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

በ2002 በጀት ዓመት የውጭ መልዕክተኞች የተከፋይ ሂሣብ ኮፒ ደጋፊ ማስረጃ

| | | | |
|---|---|---|---|
| - ያልቀረበለት በከፊል ማስረጃ የቀረበለት | | ብር | 4,979,694.56 |
| - ምንም አይነት ማስረጃ ያልቀረበለት | | ብር | 2,196,959.70 |
| | ድምር | ” | 7,176,654.26 |

በድምሩ ብር 7,196,654.26 በዚህ ኦዲትም ማስረጃ ያልቀረበላቸው መሆኑን በመግለጽ ማስረጃ እንዲቀርብላቸው በድጋሚ አሳስበናል፡፡

## 8.2. የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም

የተቋሙ ሠራተኛ አቶ ምኒሊክ አለማየሁ የሠሌዳ ቁጥር 412187 ሲያሽከረክሩ በራሳቸው ጥፋት በደረሰው አደጋ ከተቋሙ ሥራ ማስኬጃ በ2001 በጀት ዓመት ብር 32,816.88 ለካሣ ተከፍሎ በመገኘቱ ከሠራተኛው ሊተካ ስለሚባ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በዚህ በ2002 በጀት ዓመትም ገንዘቡ እንዳልተተካ በመግለጽ በድጋሚ እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

- በ2001 በጀት ዓመት በተቋሙ በተደረገ ኦዲት 2 ሞተር ብስክሌቶች የጠፉ በመሆኑ ክትትል ተደርጎ የንብረቶቹ ሁኔታ እንዲጣራ አሳስበናል፡፡ ሆኖም በ2002 በጀት ዓመት ኦዲት የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ እንዲታወቅ በመግለጽ በድጋሚ ክትትል ተደርጎ ሁኔታው እንዲጣራ አሳስበናል፡፡

ተቋሙ በላከው መልስ በሠራተኞች መቀያየር ምክንያት ክትትሉ ጠንካራ እንዳልነበረ ጠቅሶ ጉዳዩ እልባት እስኪያገኝ በቋሚነት የሕግ ባለሙያ መድቦ ክትትል እየተደረገ መሆኑ ተገልጿል፡

## ልዩ ኦዲት

የፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በቁጥር -/መመ-መ9 1935 በ30/4/2002 በፃፈው ደብዳቤ የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ኘሮጀክት ኦዲት ተደርጎ ሪፖርት እንዲቀርብለት በጠየቀው መሠረት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

በማረጋገጫ ስራው የተካተቱ ጉዳዮችና የሚሸፍነው ጊዜ፣

- ለኘሮጀክቱ ግዥ የተፈፀመው የሲሚንቶና የብረት መጠን (ከሞሶቦ፣ ሙገርና ሌሎች የግል አቅራቢዎች) ፣
- ትራንስፖርተሮች ወደ ኘሮጀክት ሲሚኒቶና ብረት ስለማድረሳቸው እንዲሁም ገቢ የሚያደርጉበት ሥርዓት፣
- የኘሮጀክቱ የንብረት ተረካቢ የመጋዘን ሠራተኞች የተረከቡትን ስሚንቶና ብረት ወደተለያዩ ሳይቶች ሥራ ላይ ያዋሉበትን ሥርዓት፣
- የማረጋገጫ ሥራው የሸፈነው ኘሮጀክቱ ከተጀመረበት ጥቅምት 1997 እስከ ነሃሴ 2001 ድረስ ያለውን ጊዜ ብቻ ነው፣
- ከላይ ለተገለፁት ጉዳዮች ሃላፊነት የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የሥራ አመራር ነው፣
- የተፈፀመ የሲሚንቶና የብረት ግዥ የሚገለፀው በመጠን (quantitative) ሲሆን ሌሎች ጉዳዮች ግን የውስጥ ሥርዓት ግምገማ (subjective) ናቸው፡፡

### የማረጋገጫ ሥራው መገምገሚያዎች፣

የማረጋገጫ ሥራውን ለመገምገም የተጠቀምነው የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት የዘረጋቸው የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቶች ናቸው፡፡

እነዚህ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቶች ጥቅም ላይ መዋላቸውን፣ በየዓመቱ ለውጥ መደረጉን /አለመደረጉን/ እና ውጤታማ መሆናቸውን ገምግመናል፡፡

ሥራው የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣንና ዓለም አቀፍ የማረጋገጫ ኢንጌጅመንት

ደረጃ 3000 መሠረት በማድረግ ቢሆን፣ ለሥራችን መሠረት የሆኑት ድርጅቱ ያቀረባቸው ሰነዶች የሂሣብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

ይህንን የኦዲት ደረጃ መከተል ሥራውን በሚገባ አቅደን ለማከናወን ያግዘናል፡፡

<u>የባህሪ ሥጋት፣</u>

ለዚህ ማርጋገጫ የተጠቀምንባቸው በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቶች በባሪያቸው ሥጋት ያለባቸው፣ ሙሉ በሙሉ ማረጋገጫ የማያስገኙና ቀደም ብሎ የተመዘገበን ክስተት ለመገምገም የተጠቀምንባቸው እንጂ የመ/ቤቱን የወደፊት ገፅታ የማያረጋግጡ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ይህ የማረጋገጫ ሪፖርት የተዘጋጀው ለፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ጥያቄ መልስ ለመስጠት ነው፡፡ ሌሎች ይህን ሪፖርት ያገኙ አካላት ሪፖርቱን መጠቀም አይችሉም፡፡

<u>የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሥራ አመራር ኃላፊነት</u>

የውስጥ የቁጥጥር ሥርዓት የመዘርጋትና ተግባር ላይ የማዋል ኃላፊነት የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት አመራር ነው፡፡

<u>የኛ ኃላፊነት፣</u>

ከፌዴራል ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በቀረበው ጥያቄ መሠረት የውስጥ ሥርዓቱን በመገምገም ውስን ማረጋገጫ መስጠት ነው፡፡

<u>የተከናወነው ሥራ ማጠቃለያ፣</u>

1. በ1997 በጀት ዓመት መጨረሻ የተንዳሆ ግድብና መስኖ ሥራ ፕሮጀክት ከዋናው መ/ቤትና ከሌሎች ፕሮጀክቶች ገቢና ወጪ ያደረገው ለባ 6 ሚ.ሜ ብረት የቆጠራና የመዝገብ ከወጪ ቀሪ ሲመዛዘን ቆጠራው በ900 ኪግ (በብር 5338.40) በጉድለት ተገኝቷል፡፡ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በሰጡት መልስ ጉድለት መገኘቱን አምነዋል፡፡
2. በ1998 በጀት ዓመት ከዋናው ዕቃ መጋዘን አዲስ አበባ ለተንዳሆ ግድብና መስኖ ፕሮጀክት የተላከው ሲሚንቶና የአርማታ ብረት ለፕሮጀክቱ ስለመድረሱ ሲጣራ፣

2.1. በዕቃ ማስተላለፊያ ሰነድ ቁጥር 32699 በ01/03/98 ብዛቱ 250 ኩንታል ፒፒሲ ሲሚንቶ ከዋናው ዕቃ ግምጃ ቤት ወጪ የተደረገው ለፕሮጀክቱ አለመድረሱ ታውቋል፡፡ የሚመለከታቸው ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ በውስጥ ኦዲት በቀረበው ማስታወሻና በኃላፊዎች በታዘዘው መሠረት የዋናው መ/ቤት ፋይናንስ ክፍል በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የተንዳሆ የግድብና መስኖ ፕሮጀክትን ሂሣብ ሲዘጋጅ የትራንስፖርት ድርጅቱ የይርጋ ተፈራ ኮንስትራክሽን መሣሪያዎች አከራይ ድርጅት አለማድረሱ ተረጋግጧል፡፡ የንብረቱ ዋጋ ከአጓጓዥ ድርጅቱ ተመላሽ እንደሚደረግ የኮርፖሬት አካውንታንት ንዑስ የሥራ ሂደት ባለቤት የገለፁ ቢሆንም ሂሣብ ክፍሉ የሺፒንግ ቁጥር 32699 የተንዳሆ ፕሮጀክት የተረከበበት ጠፍቷል በማለት የወቅቱ ንብረት ያዥ ስለመረከባቸው የውስጥ ማስታወሻ ፈርመው ለዋናው መጋዘን አዲስ አበባ በመላካቸው ዋናው መጋዘን የላኪው ሲሚኒቶ ከተንዳሆ የሚፈልግ በሚል ምዝገባ አካሂዷል፡፡

2.2. በዕቃው ወጪ ማድረጊያ ቁጥር 009797 በ21/07/98 ከቻይና ኩባንያ 60 ኩንታል ሲሚንቶ ተጠይቆና ወጪ እንዲሆን ከተፈቀደ በኋላ ይኸው ተሰርዞና ተፈርሞበት በቁጥር 15 ኩንታል ብቻ ወጪ ሆኖ እያለ በፋይናንስ ክፍል አጠቃላይ ጆርናል ቁጥር 07-97/98-2068 እና በንብረት ክፍል የንብረት መዝገብ ላይ በ21/07/98 60 ኩንታል በወጪ ተይዞ በመገኘቱ 45 ኩንታል ሲሚኒቶ አላአግባብ ወጪ መሆኑ ይታያል፡፡ የቻይናው ኩባንያ ስለተቀበለው የሲሚንቶ መጠን የሚገልጽ ማስረጃ በኦዲቱ በወቅቱ ተጠይቆ አልቀረበም፡፡

ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ ምንም እንኳን ወጪ የሆነው ሲሚንቶ በሌላ የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ ተሠርዞ 15 ኩንታል ተብሎ ቢፃፍም በንብረት መዝገብ ላይ የተቀነው ግን 60 ኩንታል መሆኑንና በቆጠራም ወቅት ትርፍ አለመኖሩንና ሂሣቡንም ያስታረቁ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

2.3. የአርማታ ብረት /deformed bar/ ባለ 28 ሚ.ሜ. የዓመቱ ገቢ ብዛት 241403.40 ኪ.ግራም ሲሆን ወጪ ደግሞ 150907.60 በመሆኑ መገኘት ያለበት ከወጪ ቀሪ 90495.80 ነው፡፡ በሰኔ 30/98 ተገኝቶ የተቆጠረ

ብዛት 90185.76 ሲሆን ልዩነት/ጉድለት/ 310.04 ኪ.ግ ተገኝቷል፡፡የተንዳሆ መስኖ ግድብ ፕሮጀክት ኃላፊልችም ጉድለት መኖሩን ተቀብለዋል፡፡

2.4. ከዋናው ዕቃ ግምጃ ቤት አዲስ አበባ በዕቃ ማስተላለፊያ ሰነድ ቁጥር 07589 በ16/03/98 የፕሮጀክቱ ንብረት ያዥ የተረከበው 240 ኩንታል ኦፒሲ ሲሚንቶ የፋይናንስ ክፍሉ ፕሮጀክቱ በተረከበው መጠን የመዘገበ ሲሆን የንብረት ክፍል መዝገብ ላይ ግን 250 ኩንታል ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ ሆኖም የበጀት ዓመቱ የስቶክ ካርድ እና ቆጠራ ልዩነት ያለማሳየቱን በሚጣራበት ወቅት ተገንዝበናል፡፡ በንብረት ምዝገባ ላይ የታየው የአመዘጋገቅ ስህተት እንደሚስተካከል ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

3. የ1999 በጀት ዓመት ሲሚንቶ በፕሮጀክቱ የንብረት መቆጣጠሪያ ካርድ ላይ ገቢና ወጪ ስለመመዝገቡ ማጣራት ሲደረግ፣

በንብረት ወጪ ማዘዣ ደረሰኝ ቁጥር 121094 በ07/09/99 ብዛት 200 ኩንታል በንብረት ወጪ ማዘዣ ደረሰኝ ቁጥር 121288 በ18/09/99 ብዛት 600 ኩንታል በድምሩ ብዛት 800 በስቶክ ካርድ ላይ በወጪ ሳይመዘገብ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ ግን የተመዘገበውና በቆጠራ የተገኘው ሲገናዘብ ልዩነት አልተገኘም፡፡ የዘመኑ የሲሚንቶ ወጪ በ800 ኩንታል በማነስ ይታያል፡፡

4. በ2001 በጀት ዓመት ከተንዳሆ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ለስኳር ፋብሪካ መጠጥ ውኃ ፕሮጀክት ባለ 8 ሚ.ሜ. የአርማታ ብረት በአቶ ዓለማየሁ ሽፈራው በተሰብሳቢ የመለያ ቁጥር 02503 በውኃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ቁጥር 10625 በ16/06/2001 ወጪ ተደርጐ ዕቃው ለፋብሪካው ፕሮጀክት አልደረሰም፡፡ በድርጅቱ ሠራተኛ በአቶ ዓለማየሁ ሽፈራው ላይ ብዛት 711kg (ብር 7727.86) በዕዳነት ተመዝግቦ ቢገኝም ንብረቱ እስከ አሁን ያልተመለሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

## መደምደሚያ፣

በዚህ ሪፖርት በተገለፀው ሥራችን መሠረት ከላይ ከተገለፁት ግኝቶች በስተቀር የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ውጤታማ አልነበረም ለማለት የሚያስችል ነገር አላጋጠመንም፡፡

# በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን በአገር አቀፍ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም ለድሬዳዋ ገጠር ከተሞች ለሚከናወነው የኤሌክትሪክ ማስፋፊያ ስራ ከህንድና ከሌሌች ውጭ አገራት ተገዝተው ድሬዳዋ UEAP ስቶር የተራገፉ ትራንስፎርመሮች እና አሉሚኒየሞችን በተመለከ የተከናወነ የልዩ ኦዲት ውጤት

1. በUEAP አገር አቀፍ ኤሌክትሪክ አቅርቦት ፕሮግራም ፕሮጀክት ለድሬደዋ ገጠር ከተሞች ለሚከናወነው የኤሌክትሪክ ማስፋፊያ ስራ ከህንድና ከሌሎች ውጭ አገራት በከፍተኛ ገንዘብ ተገዝተው ድሬደዋ UEAP እስቶር የተራገፉ የተለያዩ ትራንስፎርመሮች እና አሉሙኒየም ከስፔሲፊኬሽን ከግዥ ጨረታ ስርአት ውጭ የተገዛና የጥራት ደረጃቸው ሳይረጋገጥ ወደ ስቶር በመግባቱ 336 ትራንስፎርመሮች እና AAAC 50mm ብዛት 340 እንዲሁም AAAC 50mm ብዛት 6 ድራም አሉሙኒየሞች ለስራ ለማዋል ተሞክሮ ትራንስፎርመሮቹ በተደጋጋሚ ግዜ ጥገና ቢደረግም በቴክኒክ ችግር እንዲሁም አልሙኒየሞች በመሰባበራቸው በስራ ላይ ማዋል ያለመቻሉ እና የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ለብክነት መዳረጉ በሚል ለኮሚሽኑ ጥቆማ መቅረቡ ተገልጿል፡፡ በዚሁ ጥቆማ መሠረት ኮሚሽኑ ምርመራውን በማጣራት ላይ የሚገኙ በመሆኑ የግዥ ስርአትና የጥራት ደረጃቸውን ከፋይናንስ ህግ ከቴክኒክ አንፃር በባለሞያ ተመርምሮ ውጤቱ እንዲገለፅ በደብዳቤ ቁጥር ድሬ 1266/07/03 በ11/01/2003 የፌደራል ስነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን መስሪያ ቤታችንን በጠየቀው ጥያቄ መሰረት የተከናወነ ልዩ ኦዲት ነው፡፡

### 1.1 የኦዲቱ አላማ

2. የኦዲቱ ዓላማ ከላይ ቁጥሩ እና ቀኑ በተጠቀሰው ደብዳቤ የፌደራል የስነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን መስሪያ ቤታችንን በጠየቀው ጥያቄ መሰረት ለድሬደዋ ገጠር ከተሞች ተገዝተው ድሬደዋ ስቶር የተራገፉ የተለያዩ ትራንስፎርመሮች እና አሉሚኒየሞች በግዥ ስርአት መሰረት የተገዙና የጥራት ደረጃቸው በተገቢው ባለሙያ ተረጋግጦ ወደ ስቶር መግባታቸውን በማጣራት ኮሚሽኑ እያከናወነ ላለው የማጣራት ሥራ የሚረዳ ሙያዊ አስተያየት ለመስጠት ነው፡፡

### 1.2 የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

3. የኦዲቱ የሚሸፍነው በኮንትራት ቁጥር 33.20/98/2000 አሜንድመንት ቁጥር 33.20/139/2000 ተገዝተው ድሬደዋ UEAP እቃ ግምጃ ቤት ከመስከረም 2002 እስከ ጥር 2002 ዓ.ም ገቢ የተደረጉ 342 የዲስትርቢውሽን ትራንስፎርመሮች እና በኮንትራት ቁጥር 33.20/10/2000 ተገዝተው የካቲት 2001 እስከ ሀምሌ 2001 ዓ.ም ገቢ የተደረጉ AAAC 50ሚ.ሜ2 እና 95ሚ.ሜ2 6 ድራም ሽቦዎች ግዥን በተመለከተ የተከናወኑ ስራዎች ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው ግዥው የተፈፀመበትን የጨረታ ሰነድ፣ ፋይናንሻልና ቴክኒካል ግምገማ ሪፖርት፣ የውል ስምምነት እና ገዥና አቅራቢ በግዥው ዙሪያ የተፃፃፉዋቸው ደብዳቤዎችና ሰነዶችን በመገምገም፣ በግዥና በንብረት መረካከብ ዙሪያ ላሉ ሰራተኞች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ በቦታው በአካል ተገኝተው ንብረቶቹ ያሉበትን ሁኔታ በማየትና ፎቶግራፍ በማስደገፍ ነው፡፡

### 1.3 በኦዲቱ ወቅት የተገኙ ግኝቶች

<u>የዲስትሪቢውሽን ትራንስፎርመሮችን በተመለከተ</u>

4. ትንስፎርመሮቹ የሚገኙት ድሬዳዋ ከተማ ውስጥ ልዩ ስሙ ሳቢያን በሚባል የምስራቅና ሶማሌ ሪጂኖች ዩኤአፕ ዕቃ ግምጃ ቤት ሲሆን፣ በኦዲት ወቅት ቦታው ተገኝተን ባየነውና የፕሮጀክቱ ሠራተኞች በቃለ-መጠይቅ ባረጋገጡልን መሰረት 289 ትራንስፎርመሮች አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡
5. ችግሩን ለማስተካከል ከአቅራቢ ድርጅቱ የተላኩ ባለሙያዎች ከጥር 17/2002 ዓ.ም ጀምሮ ሶስት ጊዜ ድሬዳዋ ዩኤአፕ ዕቃ ግምጃ ቤት በመገኘት በመጀመሪያ ዘይት በመሙላት በሁለተኛው ጊዜ ደግሞ የውጭ አካላቸውን ቀለም በመቀባትና አንዳንድ አካላቸውን በመበየድ ለማስተካከል ሙከራ ያደረጉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እኛም በአካል ተገኝተን ባየናቸው ጊዜ ከላይ የተገለፀው ለመደረጉ የሚያሳዩ ጠቋሚ ነገሮች በትራንስፎርመሮች አካል ላይ ተመልክተናል ፡፡



ስዕል 1. በውጪ አካሉ ላይ ቀለም የመቀባት እና መበየድ የተደረገለት
የዲስትሪቢውሽን ትራንስፎርመር

6. ከዚህ ሌላ በኦዲት ወቅት የተገነዘብነው ከነዚህ ትራንስፎርመሮች ጋር አብረው ተገዝተው ሻሸመኔ ዩኤአፐ ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢ ከተደረጉት ውስጥ 6ቱ ለጊዜው እንዲያገለግሉ ተብለው ድሬዳዋ የተላኩ ቢሆንም ትራንስፎርመሮቹ አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ መሆኑን ነው፡፡ ይህም ከአቅራቢ ድርጅቱ ተገዝተው በተለያዩ ቦታዎች የተከፋፈሉት ትራንስፎርመሮች ተመሣሣይ ችግር ያለባቸው መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡





ስዕል 2. ይሰራሉ ተብለው ከሻሸመኔ ወደ ድሬዳዋ የተወሰዱ የዲስትሪቢውሽን ትራንስፎርመሮች በከፊል

7. ችግሮች ሊፈጠሩ የቻሉት ትራንስፎርመሮቹ በውል ስምምነት በተገለጸው ስፔስፊኬሽን መሰረት እየተመረቱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አቅራቢው ድርጅት አገር ሄደው ጥራቱን ያረጋገጡ ባለሙያዎች ትራንስፎርመሮቹ አገር ውስጥ ሲገቡ ከንብረት ተረካቢው ጋር አብረው ከዚህ በፊት አቅራቢው ለናሙና ካሣያቸው ጋር አንድ አይነት መሆናቸው ሳይረጋገጥ ገቢ በመደረጋቸው ነው፡፡

8. ለተፈጠረው ችግር አቅራቢው ድርጅት በውሉ መሰረት የማስተካከል ሥራ ሊሠራ ቢሞክርም ለኦዲት እስከተደረሰበት ጊዜ ድረስ ችግሩ ያልተስተካከለ በመሆኑ እቃዎቹ ያለስራ በመቀመጣቸው በፕሮግራሙ መሠረት መሰራት የነበረባቸው ስራዎች ላይ የጊዜ መጓተት አስከትሏል፡፡

<u>የአልሙኒየም ኤሌክትሪክ ሽቦዎችን በተመለከተ</u>

9. ሽቦዎቹ የሚገኙት በድሬዳዋ ከተማ ልዩ ስሙ ሳቢያን በተባለ የምስራቅና ሶማሌ ሪጂኖች ዩኤአፕ ዕቃ ግምጃ ቤት ሲሆን ተገዝተው ገቢ የተደረጉት አብዛኛቹ ሽቦዎቹ የተጠቀለሉበት የእንጨት ድራም የተሰባበረ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ከማስረጃዎች እንዳገኘነው እና ከኃላፊዎች በተገለፀልን መሠረት የመጠቅለያ እንጨቶቹ ከተሰበሩ ሽቦዎቹን በጥቅም ላይ ማዋል እንደማይቻል ነው ፡፡



ስዕል 3. የተሰባበሩ የሽቦ መጠቅለያ የእንጨት ድራሞች

10. አቅራቢ ድርጅቱ የተፈጠረውን ችግር ለመቅረፍ የተወሰኑትን ሽቦዎች በሌላ የብረት መጠቅለያ ድራም መጠቅለላቸውን በኦዲት ወቅት ተገንዝበናል፡፡ ይህንንም በተመለከተ ከኮርፖሬሽኑ ሰራተኞቹ ጋር ባደረግነው ውይይትና ቃለ መጠይቅም ኮርፖሬሽኑ ከዚህ በፊት የዚህ አይነት ችግር ገጥሞት እንደማያውቅ ተገልጾልናል፡፡





ስዕል 4. በብረት ድራም ለመጠቅለል የተደረገባቸው

ስዕል 5. በትክክል በፋብሪካው ሙከራ ሙከራ የተጠቀለለ

11. ይህ ሁኔታም ሊፈጥር የቻለው ሽቦዎቹ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ርክክብ ሲፈጸም በውል ስምምነቱ ላይ በተጠቀሰው ዓይነት እና በስፔስፊኬሽኑ መሠረት መሆኑ በአቅራቢ ድርጅት አገር ሄደው የጥራት ፍተሻ ያደረጉ ባለሞያዎች ንብረቶቹ ለፕሮግራሙ ገቢ በሚደረጉበት ወቅት በቦታው ተገኝተው ድርጅቱ ካሳያቸው ናሙና ጋር አንድ መሆናቸው ባለመረጋገጡ ነው፡፡ ለተፈጠረውም ችግር አቅራቢው ድርጅት በውል ስምምነቱ ላይ በተገለጸው መሠረት የተጎዳውን የእንጨት ድራም እንዲያስተካክል የተገለጸ ቢሆንም ለኦዲቱ እስከደረስንበት ጊዜ ድረስ ሙሉ በሙሉ ያልተስተካከለ በመሆኑ ሽቦዎቹ አገልግሎት ላይ ሊውሉ አልቻሉም፡፡ በዚህም ምክንያት በፕሮግራም በተያዙት ሥራዎች ላይ የጊዜ መጓተት አስከትሏል፡፡

12. ከዚህ በተጨማሪ በድሬዳዋ ዕቃ ግምጃ ቤት አፓር ኢንዳስትሪስ ሊሚትድ ከተባለ አቅራቢ ድርጅት ተገዝተው ድሬዳዋ ዕቃ ግምጃ ቤት ገቢ ከተደረጉ ሁለት ዓይነት የኤኤኤሲ 50 ሚ.ሜ$^2$ እና 95 ሚ.ሜ$^2$ ሽቦዎች ውስጥ ኤኤኤሲ 50 ሚሚ$^2$ ሽቦ ከእቃ ግምጃ ቤት ወጪ ስለማይደረግ አላግባብ በእቃ ግምጃ ቤት የተከማቸ መሆኑን የእቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው አረጋግጠውልናል፡፡ በብዛት ተገዝቶ በግቢው ውስጥ ተከማችተው ያሉትም የዚህ ዓይነት ሽቦዎች መሆናቸውን በአካል በቦታው ተገኝተን አረጋግጠናል፡፡ ይህም የሚያመለክተው ግዥው በፍላጎት ላይ ያልተመሰረተ መሆኑን ነው ፡፡



ስዕል 6. ያለአገልግሎት ተከማችተው የተቀመጡ የኤኤኤሲ 50 ሚ.ሚ$^2$ ሽቦዎች

13. በአጠቃላይ በነዚህ ትራንስፎርመሮች እና ሽቦዎች የግዥ አፈፃፀም ሲታይ የጨረታ አወጣጡ የግዥ ደንብን ተከትሎ የተከናወነ ቢሆንም ንብረቶቹ ወደ ድርጅቱ ገቢ በተደረጉበት ወቅት አቅራቢው ድርጅት በጨረታው ላይ ለመወዳደር ባቀረበው ናሙና እና በቀረበው ስፔስፊኬሽን መሠረት የተላኩ መሆኑ እና የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ መሆናቸው አቅራቢው ድርጅት አገር ሄደው የጥራት ፍተሻ ባደረጉ ባለሙያዎች ተረጋግጦ ገቢ የሚደረግበት ሥርዓት ባለመዘርገቱ እና ጥራታቸው ተረጋግጦ ገቢ ባለመደረጋቸው ነው፡፡ ይህም የአሠራር ሥርዓት ጥራት ያለው ግዥ ለመፈፀም ወሳኝ በመሆኑ ለወደፊቱ የአሠራር ሥርናቱ ሊዘረጋ ይገባል፡፡

**AUDIT OF THE MINISTRY OF WOMEN, CHILDREN AND YOUTH AFFAIR'S**
**FORMER WOMEN FUEL WOOD CARRIERS ASSOCIATION PROJECTS**
**INDEPENDENT AUDITORS' REPORT**
**FOR THE PERIOD JULY 8, 2009 TO JULY 7, 2010**

We have audited the accompanying consolidated financial statements of the Former Women Fuel Wood Carriers Association projects, set out on pages 5 that have been prepared under the accounting policy set out on pages 6-7 for the period July 8, 2009 to July 7, 2010.

**Respective Responsibilities of Management and Auditors:**

The management of the Ministry of Women's Affairs is responsible for the preparation of the consolidated statement of sources and uses, and Balance sheet. It is our responsibility to form an independent opinion on these statements and express our opinion based on our audit.

**Basis of opinion:**

We conducted our audit in accordance with Generally Accepted Auditing Standards. The audit includes examination, on a test basis, of evidence relevant to the amounts and disclosures in the financial statements. It also includes assessment of the significant estimated and judgments made by the management in the preparation of the financial statement, and of whether the accounting policies are appropriate to the program's circumstances, consistently applied and adequately disclosed.

We planned and performed our audit so as to obtain all the information and explanations considered necessary in order to provide us with sufficient evidence to give reasonable assurance that the financial statement is free form material misstatement, whether caused by fraud or

irregularity or error. In forming our opinion, we also evaluated the overall adequacy of the presentation of information in the financial statements.

Based on our audit the following unallowable costs and non-compliance were noted:

1. As per the procurement guidelines under IBRD loans and IDA credit issued October, 2006 (revision) page 30, under 3-5 procurement based on shopping should be made on comparison of price quotations obtained from a minimum of three suppliers or contractors, to assure competitive prices, and an appropriate method for procuring readily available off-the shelf goods or standard specification commodities of small value or simple civil works of small value. However, the procurement of different properties at different projects for Birr 24,491.00 were made without comparing price quotations obtained from several suppliers. As a result, we could not assure whether the associations follows sound commercial practices including comparison of price quotations obtained from a minimum of three suppliers when spending the grant to the purpose of the program.

**2.** The letters of the contract agreement does not include about the taxi and annual leave paid from the grant. However, Ethiopian Birr, 600 at Addis Ababa City FWFCA was made for annual leave charged to salary and also at Mekelle total Birr 13,085 is paid for the taxi purpose from the grant. This type of expense affects the proper use of Grant and reduces the availability of Grant for the actual program activity.

3. As per Ethiopian financial law costs incurred should be supported with adequate documentation. However, the payment of Birr 116,200.54 was made without appropriate supporting documents such as invoice, GRN, authorized training participants lists and attendance sheets.

   As a result, we could not determine whether FWFCA used the fund according to the stated purpose of the program.

4. Each FWFCA project should conduct a cash count at the closing date of each fiscal year and prepare monthly bank reconciliation in order to substantiate the amount of cash on hand and at bank reported on the balance sheet at the end of the period. However, there is no yearend

cash count except at Tigray and Bahirdar and no monthly bank reconciliation at all location except Diredawa and Tigray to verify the existence of cash on hand and cash at bank as at July 7, 2010. Therefore, the reported amount on the Balance Sheet has not been supported with cash reports. This shows that adequate internal control over the existence of cash was not maintained across all cities.

In our opinion, except as discussed on paragraph, 1-4, the accompanying consolidated financial statements when read together with notes, set out on pages 5 to 7 thereon give true and fair view of the state of the program's affairs as at July 7, 2010 and of the results of its operations for the year then ended in conformity with Generally Accepted Accounting Principles.

**AUDIT OF THE MINISTRY OF WOMEN'S AFFAIRS FORMER WOMEN FUEL WOOD CARRIERS ASSOCIATION PROJECTS**

**MANAGEMENT LETTER ON THE AUDIT OF THE CONSOLDATED ACCOUNT.**

**FOR THE PERIOD JULY 8, 2009 TO JULY 7, 2010**

In the course of our audit of the consolidated accounts of the Ministry of Women's Affairs-Former Women Fuel Wood Carriers Association Projects for the yarer ended 7 July 2010: we noted certain weaknesses in the audit of the consolidated accounts and internal control system which we hereby list below together with our recommendation, for your consideration and corrective actions as appropriate matters raised in this letter are only those, which come to our notice during the conduct of our audit. As a result, our comments on systems, internal controls, programs or procedures are not exhaustive.

## Findings

As per the procurement guidelines under IBRD loans and IDA credit issued October, 2006 (revision) page 30, under 3-5 procurement based on shopping should be made on comparing price quotations obtained from several suppliers or from several contractors, with a minimum of three, to assure competitive prices, and is an appropriate method for procuring readily available off-the shelf goods or standard specification commodities of small value or simple civil works of small value. However, the procurement of different properties at:-

| | |
|---|---|
| Arbaminch | 5,634.00 |
| Addis Ababa | 7,470.00 |
| Mekelle | 1,747.00 |
| Harrar | 9,640.00 |

Total Ethiopian Birr 24,491.00

Were made without comparing price quotations obtained from several suppliers. As a result we would not assure whether the associations follows sound commercial practices including comparing price quotations obtained from several suppliers, with a minimum of three when spending the grant to the purpose of the program.

**Recommendation No. 1**

The Association should follow the World Bank procurement guidelines and Ethiopian Government procurement regulation in order to obtain reasonable prices, quality and quantity. In addition to that, the Ministry of Women Children and Youth Affairs should ensure whether the management of FWFCA projects has adequate understanding of procurement guidelines, agreement terms and applicable regulations.

**Management Response**

Accepted

**Findings**

The letters of contract agreement are nothing to say about the provident fund taxi and annual leave paid from the grant. However, Ethiopian Birr, 600 at Addis Ababa City FWFCA was made for annual leave changed in to salary and also at Mekelle total Birr 13,085 is paid for the taxi purpose from the grant.

This shows that adequate internal control over payments was not maintained in the period. This type of expense affects the proper use of Grant and reduces the availability of Grant for the actual program activity.

**Recommendation No. 2**

Each city FWFCA should comply with agreements terms, applicable laws and regulations.

**Management Response**

Accepted

## Findings

As per Ethiopian financial law costs incurred should supported with adequate documentation. However, the payment at:-

| | |
|---|---|
| Bahradar | 13,520.30 |
| Arbaminch | 28,330.00 |
| Dessie | 18,002.24 |
| Adama | 2,707.00 |
| Mekelle | 53,641.00 |
| Total | 116,200.54 |

Were made without appropriate supporting documents such as invoice, GRN authorized training participants lists and attendance sheets.

As a result, we could not determine whether FWFCA used the fund according to the stated purpose of the program.

## Recommendation No. 3

Each city FWFCA take proper action by issuing the good receiving notes for the items purchased.

## Recommendation No. 4

The Ministry design appropriate procedure to support training payments with authorized participant lists and attendance sheets.

## Recommendation No. 5

The Ministry ensures that associations have adequate understanding of guidelines, agreement terms and applicable regulations.

## Management Response

Accepted

## Findings

Each FWFCA projects should conduct a cash count at the closing date of each fiscal year and prepare monthly bank reconciliation in order to substantiate the amount of cash on hand and at bank reported on the balance sheet at the period ends. However, there is no yearend cash count except Tigray and Bahirdar and no monthly bank reconciliation at all location except Diredawa and Tigray to verify the existence of cash on hand and cash at bank at July 7, 2010. Therefore, the reported amount on the Balance Sheet has not supported with cash reports. This shows that adequate internal control over the existence of cash was not maintained across all cities.

## Recommendation No. 6

Each FWFCA projects should form a committee need to the period end and that committee should conduct a cash count at the closing date of each fiscal year and produce a cash count reports and also each FWFCA project account should prepare monthly bank reconciliation in order to support the reported cash figures on the balance sheet at period end.

## Management Response

Accepted

## AUDIT OF THE MINISTRY OF WOMEN, CHILDREN AND YOUTH AFFAIR'S FORMER WOMEN FUEL WOOD CARRIERS ASSOCIATION PROJECTS AGREEMENT NUMBER
## TF 054213

### LIST OF ACRONYMS

| | |
|---|---|
| FWFCA | FORMER WOMEN FUEL WOOD CARRIERS ASSOCIATION |
| GAAP | GENERALLY ACCEPTED ACCOUNTING PRINCIPLES |
| GFDRE | GOVERNMENT OF FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA |
| IDA | INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION |
| MOWCYA | MINISTRY OF WOMEN, CHILDREN AND YOUTH AFFAIRS |
| OFAG | OFFICE OF THE FEDERAL AUDITOR GENERAL |
| USD | UNITED STATES DOLLAR |
| IBRD | INTERNATIONAL BANK FOR RECONSTRUCTION AND DEVELOPMENT |